# ምዕራፍ ፪

## ሥርዓተ ንግሥ፡
## በቤተ ክርስቲያን የመፈጸሙ ምሥጢር፡፡

የቀድሞው አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ዘውድ በጫኑ ጊዜ፡ ያ፡ ቅብዓታቸው፡ "የሰዎች ነውን? ወይስ የእግዚአብሔር?" ማለትም፡ "ከሰማይ ነበርን? ወይስ ከሰዎች ፈቃድ የተገኘ?" ሲሉ፡ እርስዎ ጠይቀዋል፡፡

ኢትዮጵያ፡ ካሏት ቅዱሳት ሥርዓታት መካከል፡ አንዱ የኾነው፡ የዚህ ትውፊት፡ ዓይነተኛ መለያ ስለኾኑት መሠረታውያን ባሕርያት፡ ፈጽመው ያልተረዱ፡ ወይም፡ የተረዱ ከመሰለዎት፡ በተሳሳተ መልክ የተረዱ ኾነው እንደሚታዩ፡ ከጽሑፍዎ ኃይለ ቃልና ከጥቅሶችዎ አቀራረብ፡ በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

## ኢትዮጵያ፡
## ስለአምላክነትና
## ስለ"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"
## ስትፋረድ!

በደብዳቤዎ ውስጥ ያመለከቷቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች በሙሉ፡ ነቢያት፡ የትንቢታቸው አማናዊ ፍጻሜ ስለኾነው፡ ስለአንዱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የተናገሩዋቸው፡ የመለኮታዊው ተስፋ ቃሎች መኾናቸውን፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፥ ዘውድ የጫኑት፡ ወንዶቹም፥ ሴቶቹም፥ የቀድሞው አጼ ኃይለ ሥላሴና በሕይወት የሚገኙት ቤተሰቦቻቸው ጭምር እንደምናምን፡ ከኹሉ አስቀድሞ ሊያውቁ ይገባዎታል፡፡

በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ የተቀመጠ፡ አንድም፡ የእግዚአብሔር ተጠሪ የኾነ፡ ኢትዮጵያዊ መሪ፡ ራሳቸው አጼ ኃይለ ሥላሴ ሳይቀሩ፡ ከትሕትና በቀር፡ በየትኛውም ዓይነት አገላለጥ፡ "አምላክ ነኝ!" ወይም "አምልኩኝ!" ያለ ከቶ የለም፡፡ ኢትዮጵያውያንም፡ በዜና መዋዕላቸው ውስጥ፡ አጼዎቻቸውን ወይም ንግሥቶቻቸውን፡ እንኳንስ "አማልክት ናቸው" ብለው ሊያምኑባቸውና ሊያመልኳቸው ቀርቶ፡ ወደዚያ ደረጃ በሚያመራ ግምት ያዩበትን አዝማሚያ የሚያመለክት የጊዜ ፍንጭ እንኳ ጨርሶ የለም፡፡

አምላክነትንና *"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚለውን የቅዱሳት መጻሕፍት መለኮታዊ ጥቅስ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ካልኾነ በቀር፥ በዙፋን ላይ ለተቀመጠም ኾነ ላልተቀመጠ፥ ለሌላ፡ ለማናቸውም ሰብአዊ ፍጡር መስጠት፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብን ቃል እንደመናገር፡ ወይም በእግዚአብሔር ላይ ታላቅ ክህደትን እንደመፈጸም ይቆጠራል፡፡

በዚህ መሠረት፡ በደብዳቤዎ ውስጥ ከጻፏቸው ኃይለ ቃላት መካከል፡ ስለአጼ ኃይለ ሥላሴ አምላክነት፡ ያለዎትን እምነት በመግለጽ ካሠፈሩት አሳብዎ ደርሼ፡ ዐረፍተ ነገሩን በማነብበት ጊዜ፡ ኢትዮጵያዊ እንደመኾኔ፡ የበረቀብኝ ድንገተኛ ስሜት፡ ታላቅ ድንጋጤ ነበር፡፡

የዓለሙ መፋረጃ!

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚፈጸመው ሥርዓተ ንግሥ፡ በቋሚነት የሚካኼድ መደበኛ ሥርዓት እንጂ፡ በየአጋጣሚው የሚለዋወጥ አይደለም፤ ይህም፡ በቅኔ ማኅሌቱና በቤተ መቅደሱ የሚከናወኑትን ጸሎታትና ምሥጢራት፥ የሚመቱ ማረጋገጫና ማኅተም የኾኑትን ንዋያተ ቅድሳት፥ በአዋጅ የሚነገሩትን፡ የቃል ኪዳኑን መሐላዎችና እንዲሁም፡ ከብሉያትና ከሐዲሳት ቅዱሳት መጻሕፍት፡ ስለበዓሉ እየተጠቀሱ የሚደገሙትን ምንባቦች ያጠቃልላል፤ ባጭር ቃል፡ በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ ለሚቀመጡ ኹሉ፡ የሚፈጸመው ሥርዓተ ንግሥ፡ በመሠረቱ አንድ ዓይነት ነው።

ለአጼ ኃይለ ሥላሴ የተፈጸመውም ሥርዓተ ንግሥ፡ ይኸው ሥርዓት እንጂ፡ ከዚሁ ከመደበኛው ሥርዓት ፍጹም ልዩ፡ ወይም መሰል የሌለው የሚያደርገው፡ አንዳችም ባሕርይ ወይም ግብር የለውም። ምናልባት፡ የተለየ የሚያደርገው ቢኖር፡ ከተለመደው መሰናዶ በላይ፡ ለበዓሉ ተጨማሪ ድምቀትን ለመስጠት ሲባል፡ ዘመናዊው የባዕዳን ሥልጣኔ የሰፈነበት መስሎ እንዲታይ በማለት፡ ለዚያ ጊዜ የተፈለገው፡ አዳዲስ ዝግጅት የታከለበትና ቁጥራቸው ከቀድሞው ይልቅ በርከት ያለ፡ የውጭ የክብር እንግዶች ተጋብዘው የተካፈሉበት መኾኑ ብቻ ነበር።

ከአጼ ኃይለ ሥላሴ የቀደሙትና የእግዚአብሔር ፈቃድ ኾኖ፡ ወደፊት የሚተኩ አጼዎች ወይም ንግሥቶች ቢኖሩ፡ እነርሱ ጭምር፡ ቅዱሱን ቅብዓት ተቀብተው፡ ዘውድ የደፉ በመኾናቸው፡ የእነርሱም ሰውነት፡ እንደእርሳቸው፡ እኩል የተቀደሰ ነው፤ ፀሐይና ጨረቃ ብርሃናቸው በሰማይ መታየቱ እስከቀጠለም ድረስ፡ በምድር ላይ፡ የዘለዓለማዊው ንጉሥ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ እና የዘለዓለማዊቷ ንግሥት፡ የድንግል ማርያም ተጠሪ አገልጋይነታቸው፡ እንደእርሳቸው፡ በእኩልነት ዕውቅናን ያገኘና የሚያገኝ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ የባሕርይ ገንዘቡ ከኾነው አምላክነትና "ምእ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" ከሚለው መለኮታዊ ቃለ ማኅተም በቀር፡ እርስዎ፡ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ ያጸደቁላቸው ማዕርጋትና ሥልጣናት ኹሉ፡ ለእነርሱ፡ ሳለፉትም የተሰጣቸው ነበር፤ ለመጪዎቹም የሚሰጣቸው ይኾናል። እንደዚሁ ኹሉ፡ እርስዎ፡ በዚያ በተቀባ ሰውነት ላይ እጁን ለማንሣት እስከመድፈር የደረሰ ማንም ሰው ቢኖር፡ ጽኑ የኾነ የቅጣት ፍርድ እንደሚፈጸምበት በመግለጽ፡ ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከቀድሞው የ፲፱፻፳፭ ዓ. ም. የኢትዮጵያ ጽሑፍ ሕገ መንግሥት እየጠቀሱ ያመለከቷቸው ኃይለ ቃሎች፡ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ ብቻ ሳይኾን፡ ከእርሳቸው ለቀደሙትና እርሳቸውን ለሚተኩት፡ ለሌሎቹ ኹሉ አጼዎችና ንግሥቶች ጭምር፡ በተመሳሳይ መልክ፡ ይጸናሉ።

እንደእርስዎ የግምት አስተሳሰብ፡ ሥርዓተ ንግሡና በእርሱ የሚገኘው ሥልጣን፡ ለአምላክነት የሚያበቃ መሥፈሪያ እንዲኾን ተደንግጎ ቢኾን ኖሮ፡ እኒያ፡ ዘውድ ጭነው በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ የተቀመጡት ኹሉ፡ ከአማልክትነት ደረጃ እንደደረሱ በተቈጠሩ ነበር። አለዚያ፡ ይህን፡ ታላቅ የኾነ፡ የመጨረሻ ሰማያዊ ልዕልና፡ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ ብቻ ለማቀዳጀት መሞከር፡ አድላዊነት ከመኾኑ ጋር፡ እርስበርሱ የሚቃረን፡ ተጻራሪ ድርጊትን የሚፈጥር፡ እንጉል አስተሳሰብ ይኾናል። እንዲህ ከኾነ ደግሞ፡ የወደፊቶቹ ኣጋሮች እንዴት ሊኾኑ ነው?

ከመጪው የኢትዮጵያ ትውልድ መካከል፡ ለንስሓ የሚያበቃ ሃይማኖትና ምግባር ያለው፡ የተገኘ እንደኾነ፥ ለእርሱም፡ ከዚህ ብቅዓቱ የተነሣ፡ የእግዚአብሔር ሥርዓተ መንግሥት፡ በእውነት እንዲካኼድ ሊያደርግ የሚችል፡ የዘውድ አስተዳደር ተመልሶ የተቋቋመለት እንደኾነ፡ በዚያን ጊዜ፡ በተከታታይ፡ በዙፋኑ ላይ እንዲቀመጡ ለሚሠየሙት፡ ምን ዓይነት ሥርዓትና መመሪያ ሊኖራቸው ነው? ሊ...ካሁን የነበረው፡ ሥርዓተ ንግሥ፡ መጽናቱ እንዲቀጥል የተደረገ እንደኾነ፡ ታዲያ፡ እኒያ፡ በዚሁ ሥርዓት የሚሠየሙት አጼዎች ወይም ንግሥቶች፡ እንዳማልከት ሊታዩ ነውን? ምናልባት፡ ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ይልቅ፡ በበለጠ ገናና የኾነ አጼ የተነሣ እንደኾነስ? በዘመኑ የሚኖረው ትውልድ፡ እርሱን ምኔ ነው ሊል ነው? ከአጼነቱ በላይ፡ ሌላ ክርስቶስ ያደርገዋልን? ወይስ ከክርስቶስ የላቀ ክርስቶስ?

ታዲያ፡ እንዲህ፡ እንደእርስዎ አስተሳሰብ ከኾነ፡ በዚህ፡ በማያቋርጥ ይዘት የሚካኼደው፡ ይህ፡ በተከታታይ፡ ሰዎችን ለአምላክነት የማብቃት ሥርዓቱና ውጤቱ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለተናገረው መለኮታዊ ትንቢት፡ የፍጻሜ መልስ መኾኑ ነው" ብለን ልንተረጕመው አይደለምን? መለኮታዊው መሪያችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ስለዳግመኛ አመጣጡና ስለዓለሙ መጨረሻ፡ የዘመኑ ምልክት ምን እንደኾነ፡ ደቀ መዛሙርቱ፡ ለብቻቸው ኾነው በጠየቁት ጊዜ፡ የመለሰላቸው ቃል እንዲህ የሚል ነበር፡-

*"ማንም እንዳያስታችሁ፡ ተጠንቀቁ! ብዙዎች፡ 'እኔ ክርስቶስ ነኝ' እያሉ፡ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ። ...በዚያን ጊዜ፡ ማንም፡ 'እነሆ ክርስቶስ፡ ከዚህ አለ' ወይም 'ከዚያ አለ' ቢላችሁ፡ አትመኑ! ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና። ቢቻላቸውስ፡ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ፡ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ። እነሆ አስቀድሜ ነገርኋችሁ! እንግዴህ፡ 'እነሆ በበረሃ ነው' ቢሏችሁ፡ አትውጡ! 'እነሆ በእልፍኝ ነው' ቢሏችሁ፡ አትመኑ! መብረቅ፡ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከምዕራብ እንደሚታይ፡ የሰው ልጅ [የእኔ] መምጣት፡ እንዲሁ ይኾናልና።" "...በእኔ ከሚያምኑ፡ ከእነዚህ፡ ከታናናሾቹ፡ አንዱን የሚያሰናክል ኹሉ፡ የወፍጮ ድንጋይ፡ በአንገቱ ታሥሮ፡ ወደጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር።"*[፲፭]

ለአጼ ኃይለ ሥላሴም ኾነ፡ ወይም፡ ከእርሳቸው ለቀደሙት አጼዎችና ንግሥታት፡ ለእያንዳንዳቸው የሚፈጸመው ሥርዓተ ንግሥ፥ በሰውነታቸውም ላይ የሚያርፈው ቅብዓ መንግሥት፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥና በእግዚአብሔር መንበረ ታቦት ፊትለፊት፡ በይፋና በአዋጅ የሚከናወነው ለምንድር ነው?

ከምክንያቶቹ መካከል፡ አንዱ መሠረታዊውና እዚህ ላይ፡ አግባብነት ያለው ኾኖ፡ ሊገለጽ የሚገባው፡ ባጭር ቃል፡ ከዚህ የሚከተለው ይኾናል፡- *ለአጼነት ወይም ለንግሥትነት ተሠይመው የቀረቡት፡ እንያ ኢትዮጵያውያን ወይም ኢትዮጵያውያት፡ ብቸኛ ተግባራቸውና የሕይወታቸው ቀዳሚ ግዳጅ፡ ቅዱሱ ኪዳን፡ በተሟላ ይዘታ ተከብሮ፡ ለመልካም ፍሬያማነት እንዲበቃ በማድረግ፡ ኢየሱስ ክርስቶስንና ድንግል ማርያምን ብቻ፡ ፍጹም በኾነ እውነተኛ ታማኝነት፥ ታዛዥነትና መሥዋዕትነት የሚያገለግሉ መኾናቸውን፡ ለእየራሳቸው፥ ለእግዚአብሔርና ለኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፡ ያለአንዳች ጥርጥርና ውልውል ለማረጋገጥ ነው።* ይህንኑም፡ ራሱ ሥርዓቱ ይመሰክራል።

የዓለሙ መፋረጃ!

እንግዴህ: ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ: "አጼ" ተብለው: በቤተ ክርስቲያን በተከናወነው ሥርዓተ ንግሣቸው ላይ: "ሥዩመ እግዚአብሔር" (የእግዚአብሔር ሹም) እና የእርሱ ዋና አገልጋይ መኾናቸውን ራሳቸው በመመስከርና በማረጋገጥ: ቅዱሱን ዘውድ ተቀዳጅተው÷ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም: በመቅደሳዊ ዙፋናቸው በተቀመጡበት አደባባይም ፊት ቆመው: የሰጡት ቃለ መሐላና የገቡት ቃል ኪዳን: ይህ: ከላይ: የተጠቀሰውን የተቀደሰ ዓላማና ተግባር ያጠቃለለው ነበር::

ያ: አጼ ኃይለ ሥላሴ የሰጡት ቃለ መሐላና የገቡት ቃል ኪዳን የተፈጸመው: ለእኛ ሲል: ሰው ኾኖ: የካህናት አለቃ÷ የነገሥታት ንጉሥ÷ ድል አድራጊው: የይሁዳ አንበሳ *(ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ)*÷ የዳዊት ሥርና ልጅ የተባለው: ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ እና ቅድስት እናቱ÷ አገራችንና ንግሥታችን ድንግል ማርያም ፊት መኾኑ: በቀላል የማይታይ÷ ነገር ግን የመጨረሻው ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ታላቅ ጉዳይ መኾኑን እዚህ ላይ በብርቱ ማጤን ያስፈልጋል::

*"ገገ"* ወይም *"የይሁዳ አንበሳ"* የሚለው የስያሜ ጥቅስ የሚያመለክተው: በራእየ ዮሐንስ: ምዕራፍ ፭÷ ቁጥር ፭ ላይ በግልጽ እንደተተረጐመው: በቀጥታ ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ መኾኑ: በፍጹም አያጠራጥርም፤ አያጠያይቅምም:: ስለዚህ: ማንም: ሌላ ክርስቶስን አይፈልግ! ወይም ሌላ ክርስቶስን ሊፈለስፍ አይሞክር! ክርስቶስ: አንድ ነው! እርሱም: ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው: ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው::

ኢየሱስ ክርስቶስ: ለኢትዮጵያውያን: ከትስብእቱ (ሰው ከመኾኑ) በፊትም ኾነ በኋላ: ንጉሣቸው ነው:: ስሙ: በብሉዩ ኪዳን: "እግዚአብሔር" ይባላል፤ ("እግዚአብሔር" ስለሚለው: ስለቃሉ የስያሜ ትርጉም: ገጽ ፷፰ ይመለከቷል)፤ በአዲሱ ኪዳን ደግሞ: "ኢየሱስ ቅቡዕ": ወይም "ኢየሱስ መሢሕ": ወይም "ኢየሱስ ክርስቶስ" ከሚለው መጠሪያው ጋር: "እግዚአብሔር ወልድ"÷ "ወልደ እግዚአብሔር"÷ "የእግዚአብሔር ልጅ" "ቃል"÷ "ቃለ እግዚአብሔር"÷ "የእግዚአብሔር ቃል" በሚሉ ስሞች ይጠራል:: ሰባቱን ቅዱሳት ኪዳናት ድልድይ በማድረግ: በመጀመሪያ: በሕያውት ነፍስ አማካይነት÷ ቀጥሎ: በጽላተ ኪዳኑ አማካይነት÷ በመጨረሻም: በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት: እርሱ: ኢየሱስ ክርስቶስ: ካህኑ ንጉሥ÷ ቅድስት ድንግል ማርያምም: እናቲቱ ንግሥት ኾነው: በእኛ በኢትዮጵያውያን ላይ: እነሆ ለዘለዓለም ነግሠው ኖረዋል፤ ወደፊትም ይኖራሉ::

መለኮታዊው ንጉሥና ንግሥት እናቱ: ከታማኞች ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው መካከል: በብቅዓታቸው: በእነርሱ ዘንድ: ተገቢውን ሞገስ ከማግኘት የደረሱትን ኢትዮጵያዊ ወይም ኢትዮጵያዊት: በእንደራሴነትና በዋና አገልጋይነት መርጠውና ሠይመው÷ በቅዱሱ ቅብዓት አክብረውና ቅዱሱን ዘውድ አቀዳጅተው: በትረ ሥልጣናቸውን: ከታላቅ አደራ ጋር ይሰጧቸዋል:: በምድር ላይ ያለችውን የመለኮታዊት መንግሥታቸውንም አያያዝ÷ አስተዳደርና አካሄድ: እንዲህ አድርገው: በበላይነት ይመለከታሉ፤ ይቆጣጠራሉ፤ ይመራሉ:: ከዚህ የተነሣ: "ሥዩመ እግዚአብሔር" ወይም "ሐጼ" (እግዚአብሔር አጭቶ የሾመው) እና "እቴጌ" ወይም "ንግሥት" የሚለው የማዕርግ ቃል: ለዘውድ እንደራሴዎችና ባለአደራዎች: ከመጠሪያ ስማቸው የማይነጠል: የመታወቂያቸው አካል ኾኖ ኖርዋል::

*“ምአ ኣንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ”* የሚለው ትንቢታዊና ዘለዓለማዊ የማዕርግ ስም፡ ባለቤትነቱ፡ በማያወላውል እርግጠኛነት፡ የአንዱ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መኾኑ የታመነበት ኹኖ ሣለ፡ አሁን፡ ይህንኑ ባለቤትነት፡ እርስዎ፡ በዘመናችን፡ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ አሳልፈው ሊሰጡ ሲሞክሩ በማየት፡ የዓይን ምስክሮች ከመኾናችን በቀር፡ ይህ መለኮታዊ ቃለ ማኅተም፡ “ሥዩመ እግዚአብሔር” ተብለው ከተቀቡት ኢትዮጵያውያን “አጼዎች” መካከል፡ ለአንዳቸውም፡ እንደተሰጠ የሚያስመስል የአስተሳሰብ አዝማሚያ እንኳ መኖሩ የታመነበት ጊዜ ጨርሶ የለም።

በቀጥታ አነጋገር፡ ወይም በተዘዋዋሪ አገላለጽ፡ *“ምአ ኣንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ”*፡ “ራሳቸው አጼ ኃይለ ሥላሴ ናቸው!” ማለትዎ ከኾነ፡ የእግዚአብሔርን እውነት፡ ከጊዜው እውነታ ጋር ለማቃረን፡ ወይም ለማወሳሰብ የሞከሩ ይመስላል። ዳሩ ግን፡ *የእግዚአብሔር እውነትና* የጊዜ እውነታ፡ ኹለት ገጽታ ያላት፡ ያቺው፡ አንዲቷ የእውነት ህላዌ ስለኾነች፡ ይህ ሙከራዎ ሊሳካ የሚችል አይደለም።

“የክፋት ኃይልና የሐሰት ምንጭ የኾነውን፡ ሰይጣን የተባለውን ዲያብሎስን፥ እንዲሁም፡ በእርሱ ጠንቅ፡ የሰው ልጆች፡ በራሳቸው ላይ ያመጧቸውን፡ የኃጢአት ቀንበርንና የሞት ዕዳን፡ ኹሉንም ድል ያደረገ በመኾኑ፡ *ምአ ኣንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ፡* ኢየሱስ ክርስቶስ ነው” ብላ፡ *የእግዚአብሔር እውነት ታበሥራለች፤ ትመሰክራለች፤ ታረጋግጣለችም።* ይህም ማለት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከጥንት ጀምሮ፡ የሰውን ልጆች፡ ከፈጣሪያቸው የለዩዋቸውን፡ እኒያን፡ የዘርና የዘለዓለም ጠላቶቻቸውን፡ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ፡ በድል አድራጊነት አስወግዶ፡ መላውን የሰው ትውልድ፡ በቤዛነት ስላዳነ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ በሰብአዊ አእምሮ በሚታሰብ ወይም በማይታሰብ፡ በማናቸውም ፍጡር ወይም በምንም ነገር፡ እንደገና ጥቃት ሊደርስበት ወይም ሊሸነፍ ከቶ አይችልም ማለት ነው። እንዲያውም፡ ከዚህ መድኅንነቱ የተነሣ፡ በእርሱ ያመኑት እንኳ ሳይቀሩ፡ እነዚህን ጠላቶች፡ ድል ለማድረግ እንዲችሉ፡ ኃይሉንና ሥልጣኑን ሰጥቷቸዋል። እርሱ ራሱም፡ እነሆ ሳለፉት ኹለት ሺህ ዓመታት ያህል፡ በምድርና በሰማይ፡ አሸናፊ ኹኖ ኖርዋል፤ አሁንም እየኖረ ነው፤ ወደፊትም ለዘለዓለም ይኖራል። እስከዚህ፡ *የእግዚአብሔር እውነት፡* በዚህ ረገድ የሰጠችው ሓተታ ነው።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ፡ የጊዜ እውነታ፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የምትሰጠው ሓተታ ይቀርባል። ይኸውም፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ራሳቸው ያቋቋሙት የጦር ኃይሎች ድርጅት፡ በዓመፅ በፈጠረው፡ ደርግ በተባለ፡ ጨካኝ መቅጫ ቡድን፡ ከዙፋናቸው መውረዳቸው፥ መይያዛቸው፥ መታሠራቸው፥ መንገላታታቸውና በመጨረሻም መገደላቸው፡ በዓለሙ ኹሉ ሳይቀር የታወቀ መኾኑን የሚያስረዳው ነው። ይህም፡ እንኳንስ በእርሳቸው የሥልጣን ክልልና ጥበቃ ውስጥ የሚገኙትን ቤተሰቦቻቸውንና አገልጋዮቻቸውን ሊያድኗቸው ቀርቶ፡ ራሳቸውን እንኳ፡ ሙታን ከኾኑት ከእኒያ ደካሞች ወታደሮች እጅ ማትረፍ አቅቷቸው፡ እጃቸውን ሰጥተው፡ ከቁጥጥራቸው ሥር እንደወደቁና እንደተሸነፉ ተረጋግጧል።

## የዓለሙ መፋረጃ!

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀል ላይ በደረሰበት፡ በመከራው፥ በደሙ መፍሰስና በሞቱ ምክንያት፡ ለድል አድራጊው *የይሁዳ አንበሳ፡* የባሕርይ ገንዘቦቹ ይኹኑ ዘንድ፡ ከተሰጡት፡ ከብዙዎቹ ሥልጣናት መካከል፡ ራሱንና ሌሎችን ሊያድን የሚችልባቸው ኃይላት፡ የሚገኙ ሲኾኑ፡ እኒህ ኹለት ችሎታዎች፡ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ ሳይሠሩ እንደቀሩ፡ ይኸው፡ ኹላችንም፡ የዓይን ምስክሮች ነን፡፡

ባለቃል ኪዳኑን፡ ማለትም፡ ተዋዋዩን፡ መከታና ጋሻ ኾኖ፡ ተከላክሎ እንደሚያድን፡ ፍጹም የታመነውና የተረጋገጠው፡ መለኮታዊው ዋስትና እንኳ፡ በዘመናቸው፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ በተፈጸመው የክህደት ዓመፅና የጥፋት ርኵሰት ምክንያት፡ በግል ሳይቀር፡ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ ተነፍጓቸው፡ ያው ሳያድናቸው ቀረ፡፡

እንግዴህ፡ እርስዎ እንደገመቱት፡ *"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚለው መለኮታዊ ቃል፡ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ የተሰጠ ከኾነ፡ ይህን የመሰለው መሸነፍ፥ እንግልትና አሟሟት፡ በእርሳቸው ላይ ሊደርስ ይችላል ብሎ ማሰቡ እንኳ ያስኬዳልን? ፈጽሞ አያስኬድም፡፡ አለዚያ፡ ይህንኑ ቁምነገር በሚመለከት፡ በወንጌላዊው ዮሐንስ አማካይነት የተላለፈልን፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ እንደማይታመንና እንደማይጸና ኾኖ እንዲቆጠር ያደርገዋል፡፡

ይህ ያመለከትኩት የእግዚአብሔር ቃል፡ በግእዙ የሚለው እንዲህ ነው፤- *"ወብዙኃን እለ በከዩ፤ ወአነሂ ምስሌሆሙ፤ እስመ አልቦ ዘተረክበ፡ ዘይደልዎ ይክሥታ ለይእቲ መጽሐፍ፤ ወይርአያ፡፡ ወይቤለኒ አሐዱ እምውስተ እልክቱ ሊቃናት፡- 'ኢትብኪ! ናሁ ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዘእምውስተ ሥርዉ ለዳዊት፡ ከመ ይፍትሖ ለይእቲ መጽሐፍ፥ ወለማኅተሚሃ!"* ይህ፡ በኢትዮጵያኛ ሲተረጐም፡ *"መጽሐፉን ሊዘረጋ ወይም ሊመለከተው የሚገባው ማንም ስላልተገኘ፡ እጅግ አለቀስሁ፡፡ ከሊቃናቱ መካከል አንዱ፡- 'አታልቅስ! እነሆ፡ መጽሐፉን ይዘረጋ ዘንድ፥ ሰባቱንም ማኅተም ይፈታ ዘንድ፡ የዳዊት ሥር፡ እርሱም ከይሁዳ ነገድ የኾነው* ፲፰ *አንበሳ፡ ድል ነሥቷል' አለኝ፡፡"* ማለት ነው፡፡

እንግዴህ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ለሕያው እግዚአብሔር ሳይኾን፡ ለመዋቲ ሰብአዊ ፍጡር የተወሰነውንና በሞተ ሥጋ የሚያበቃውን ጽዋ ለመቀበል የተፈጠሩ፡ ዕሩቅ ብእሲ እንጂ፡ "አምላክ" አለመኾናቸውን፥ እንዲሁም፡ *"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚለው፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የተሰጠው መለኮታዊ ስያሜ፡ በምንም ዓይነት መንገድ፡ ለእርሳቸው ሊኾን የማይችል መኾኑን፡ እነሆ፡ *የእግዚአብሔር እውነት* በገለጸችው፡ በጊዜው እውነታ ተመስክሩዋል፡፡ ይህም ምስክርነት፤ የእርስዎን የፈጠራ አስተሳሰብ፡ ሐሰተኛነቱንና ከንቱነቱን በበለጠ በማረጋገጥ፡ ለመጨረሻው ደይን ዳርጎታል፡፡ ደግሞስ፡ ይህንኑ፡ *"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚለው መለኮታዊ ቃል፡ አጼ ኃይለ ሥላሴን ለመሰለ እሩቅ ብእሲ (ለሰብአዊ ፍጡር) መስጠት፡ ምን ያህል አደገኛ እንደኾነ፡ ይኸው፡ በዚሁ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴና በሥራቸው ላይ በደረሰው የጥፋት ፍጻሜ፡ በግልጽ ታየ አይደለምን? በግዘፍስ ተረጋገጠ አይደለምን? ይኸውም፡ ሥጋ ለባሽ ከኾነው፡ ከሰው ስሕተትና በደል ስለማይጠፋ፡ ይህ መለኮታዊ ቃል፡ ለሰው በመሰጠቱ ምክንያት፡ በማንም ፍጡር፥ በምንም መንገድ፡ ሊደፈር የማይታሰበው የመለኮት ኹለንተናዊ ፍጹምነት ሊነካ አይደለምን?

በዚህ መሠረት: *"ምአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚለውን መለኮታዊ ስያሜ: ለአጼ ኃይለ ሥላሴም ኾነ ወይም ለሌላ ለማነኛውም ሰብአዊ ፍጡር መስጠት: በእግዚአብሔር ላይ ታላቅ ኃጢአትን መፈጸም፥ ይኸውም: በእርሱ ላይ የስድብ ቃልን ማሰማት መኾኑን: እውነተኞች ኢትዮጵያውያን: ወይም እውነተኞች ክርስቲያኖች: በሃይማኖት ይመሰክራሉ::

## "ሥዩመ/ሥይምተ እግዚአብሔር" ተብሎ: ለአጼነትና ለንግሥትነት የመብቃት ምሥጢር::

ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊትና በኋላ: በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ ተቀምጠው የነበሩት: አጼዎችና ንግሥቶች ኹሉ: እያንዳንዳቸው: በነፍስ ወከፍ: ይታዩ የነበሩት: የእግዚአብሔር መንግሥት ተጠሪዎች፥ ቀዳሚ አገልጋዮችና የአገልጋዮቿ ዋና አለቆች እንደኾኑ ተደርጎ ነበር፤ ማለትም: ልክ: አዳምና ሔዋን፥ ኖኅና ሚስቱ፥ መልከ ጼዴቅ፥ አብርሃምና ሣራ ወይም ኬጡራ፥ ሙሴና ኢትዮጵያዊት ሚስቱ ሲጳራ፥ ዳዊትና ቤትሳባ፥ ሰሎሞንና ማክዳ: እንዲሁም: ንግሥት ሕንደኬን የመሰሉት እንደነበሩት ማለት ነው::

ለእኒያ: ለተመረጡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት: በቤተ ክርስቲያን የተከናወነው: የቅብዓትና የንግሥ ሥርዓት: በሰማይና በምድር: እውነተኛው ንጉሥና እውነተኛዋ ንግሥት ኾነው: ሥጋዊዉንና መንፈሳዊዉን ዓለማት: ለዘለዓለም ለሚያስተዳድሩት: ለኢየሱስ ክርስቶስና ለድንግል ማርያም እንደራሴዎች በመኾን: የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማገልገል: በመለኮታዊው ፈቃድ ተመርጠው፥ "ሥዩመ እግዚአብሔር" ወይም "ሥይምተ እግዚአብሔር" ተብለውም ለመሾማቸው: መገለጫና ማረጋገጫ ምልክት ነበር::

በዚህ መልክ: በዘመነ ብሉይ ኪዳን ኾነ: ወይም በዘመነ ሐዲስ ኪዳን: ለዚህ ቅብዓ መንግሥት ከበቁት አጼዎችም ኾኑ: ከንግሥታቱ መካከል: ራሱን: "አምላክ ነኝ!"፥ ወይም: "ነኝና: አምልኩኝ!" ያለ፥ ወይም: "ከዚህ ሰማያዊ ልዕልና ደርሰዋልና: እናምልክዎ!" ተብሎ: ይህን የመሰለውን ከንቱ ውዳሴ የተቀበለ: አንድ እንኳ አይገኝም:: በመንፈሳዊው ገድል በኩል ያላቸው ብቅዓት ታውቆ: ከዚህ ማዕርግ የደረሱ: ከመካከላቸው: አንዳንዶች ቢኖሩ እንኳ: እነርሱም ቢኾኑ: የሚሰጣቸው የመጨረሻው ደረጃ: "ቅድስና": ማለትም: "ቅዱስ" የመባልን ክብር እንጂ: አምላክነትን አልነበረም:: ያንንም እንኳ የሚያገኙት: በሕይወተ ሥጋ እያሉ ሳይኾን: በሕይወተ ነፍስ: ከዚህ ዓለም ተለይተው: ወደዘለዓለማዊው ዕረፍት ከተሻገሩ በኋላ ነበር:: ለዚህም: በአዲስ ኪዳኑ ዘመነ ምሕረት: በቀዳሚውና በመካከለኛው መዋዕላት የነበሩትን: ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን አጼዎች: ካሌብንና ላሊበላን: በምሳሌነት መጥቀሱ ይበቃል::

ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት: በሕጋዊ አልጋ ወራሽነት: በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ: ለመቀመጥ ከሚያበቁት: ዓበይት መሥፈሪያዎች መካከል: ወሳኝ የኾነው: አንደኛው የባለመብትነት ይዞታ: ከዚህ የሚከተለው እንደነበረ ይታወቃል::

የዓለሙ መፋረጃ!

ይኸውም፡ ፆ፡ ግለሰብ፡ ንግሥተ ሳባ ወይም ንግሥተ አዜብ በሚል ገናና ስያሜ የምትታወቀው፡ ድንግሊቱ ኢትዮጵያዊት፡ ንግሥት ማክዳ፡ ከዳዊትና ከቤትሳባ ልጅ፡ ከእስራኤላዊው ንጉሥ፡ ከሰሎሞን፡ በቅዱሱ ኪዳን ኃይልና በረከት ከወለደችው፡ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር፡ በትውልድ አወራረድና በሥጋ ዘር ሐረግ ረገድ ያለውን፡ ቀጥተኛ ግንኙነት ማረጋገጥ ነበር:: የቅዱሱ ኪዳን፡ የትንቢትና የተስፋ ቃል ፍጻሜ የኾነው፡ የመጨረሻው ዘለዓለማዊ ንጉሥ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሰውነት ተወልዶ፥ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶና ዓርጎ፡ በመንፈስ ቅዱስ ከተገለጸ በኋላ ግን፡ ፆ፡ የሥጋ ዘርና ልደት ያስገኘው የነበረው፡ የአሮጌው ኪዳን አልጋ ወራሽነት መብት አበቃ! በእርሱም ሥፍራ፡ ዘለዓለማዊ በኾነው በአዲሱ ኪዳን፡ መንፈሳዊ ዘርና ልደት ላይ የተመሠረተው፡ የአልጋ ወራሽነት መብት ተተካ!

ይህ አዲስ ሥርዓት፡ በተግባር ላይ የዋለው፡ ስለትስብእት፡ ማለትም፡ እግዚአብሔር ሰው ስለመኾኑ፡ ለረዥም ዘመናት፡ በታላቅ ጽናት ሲነገርና በተስፋ ሲጠበቅ የኖረው፡ መለኮታዊው ትንቢት ደርሶ በመፈጸሙ ሲኾን፡ በዚህ አዲስ ሥርዓት ደግሞ፡ እንግዲህ ወዲህ፡ ወራሽ ልጅ የመተካቱ መንገድ የሚከናወነው፡ እንደቀድሞው፡ በሥጋዊ ሥርዓተ ጋብቻ፡ ትዳር በመመሥረት አለመኾኑ፡ በገሃድና በይፋ ተረጋግጦ ሊታወቅ ችሏል::

እግዚአብሔር ወልድ፡ ሰው ኾኖ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የፈጸመው ቤዛነትና መሥዋዕትነት፡ ለሰው ልጆች፡ ከሥጋ ልደት ቀጥሎ፡ ኹለተኛ የተባለውን፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ የመወለድን ሥልጣንና መብት አቀዳጀ! በዚህም፡ አዲሱ፡ መለኮታዊው ቃል ኪዳን ታውጆ፡ በሥራ ላይ ዋለ! እግዚአብሔር፡ ከዳዊት ጋር ያደረገው፡ አሮጌው መለኮታዊ ቃል ኪዳን፡፣ በአቋሙና በአፈጻጸሙ ረገድ፡ የነበረው ሥጋዊ ባሕርይ፡ እነሆ፡ በአምላካዊው ጸጋ፡ ወደመንፈሳዊነት ተለውጦ፡ ለእያንዳንዱ እውነተኛ ኢትዮጵያዊና ለእያንዳንዷ እውነተኛ ኢትዮጵያዊት፡ ሕጋዊ የእግዚአብሔር ልጅ የመኾንን ሥልጣን አጐናጸፈ! ከዚህ የተነሣ፡ ለዚህ ክብር የበቃው እያንዳንዱ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ/ት፡ በሦስቱ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የአገልግሎት ቤቶች፡ ታላላቅ መናብርት ላይ ብቻ ሳይኾን፡ "ሥዩመ/ሥይምተ እግዚአብሔር"፡ ማለትም፡ "እግዚአብሔር መርጦ የሾመው/የሾማት" የሚል ትርጉም ያለውን፡ "አጼ"፥ "ንግሥት" ወይም "እቴጌ" በሚለው የማዕርግ ስም፡ ዘውድ በመጫን፡ ወንዱም፥ ሴቷም፡ በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ ሳይቀር ለመቀመጥ በሚያስችለው ምርጫና ሢመት ውስጥ ይካፈሉ ዘንድ፡ ኹለቱም፡ ባለመብት ኾኑ!

ከእግዚአብሔር፡ ልጅነትን በማስጠት፡ ያልጋ ወራሽነትን መብት የሚያጐናጽፈውን፡ አዲሱን መንፈሳዊ ልደት ያስገኘው፡ ይህ፡ የአዲስ ኪዳኑ መለኮታዊ ሥርዓት፡ በሥራ ላይ እንዲውል በመደረጉ፡ "ሥዩመ/ሥይምተ እግዚአብሔር" ለሚያሰኘው የጸጋ ማዕርግ መብቃታቸው ለተረጋገጠላቸው ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ቅብዓ መንግሥትን ተቀብተው፡ ዘውድ በመጫን፡ እንደየጸታቸው፡ የአጼነትን ወይም የንግሥትነትን ክብር አቀዳጅቷቸዋል! ለዚህም፡ ጥቂት ቀደም ባለው ዘመን፡ በስመ ጥርነት የሚታወቁትንና "የአባረረ" ለማለት፡ "ዘአጕየየ" ወይም በአጭር ቃል፡ "ዘጕዬ" የሚል ስያሜ የተሰጣቸውን፡ እነቅዱስ ላሊበላ የሚገኙባቸውን አጼዎች፥ በቅርቡም፡ ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስን፥ አጼ ዮሐንስ ፬ኛንና ንግሥት ዘውዲቱን የመሰሉትን፡ በምሳሌነት መጥቀሱ ይበቃል::

ይህን አርእስተ ጉዳይ በሚመለከት፡ በመዝሙራቱ ላይ የተጻፉትን፡ የብሉዩን ኪዳን ጥቅሶች፡ መልእክታቸውን፡ በትክክል ለመረዳት፥ ትርጓሜያቸውንም፡ በግልጽ አውቆ፡ ለሌላው ለማሳወቅ፡ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ከሠፈሩት፡ ከአዲሱ ኪዳን ጥቅሶች ጋር አያይዞ መመልከትና ከእነርሱ የሚገኘውን ማብራሪያ፡ በመንፈስ ቅዱስ እውነት አመዛዝኖ መቀበል ያስፈልጋል።

በመጀመሪያ፡ በመዝሙራቱ፡- *"ከመረጥሁት ጋር፡ ቃል ኪዳኔን አደረግሁ፤ ለባሪያዬም ለዳዊት፡ 'ዘርህን፡ ለዘለዓለም አዘጋጃለሁ! ዙፋንህንም፡ ለልጅ ልጅ እመሠርታለሁ!' ብዬ ማልሁ። ...ዘሩንም፡ ለዓለምና ለዘለዓለም፥ ዙፋኑንም፡ እንደሰማይ ዘመን አደርጋለሁ። ልጆቹ ግን፡ ሕጌን ቢተዉ፥ በፍርዴም ባይኼዱ፥ ሥርዓቴንም ቢያረክሱ፥ ትእዛዜንም ባይጠብቁ፡ ኃጢአታቸውን፡ በበትር፥ በደላቸውንም፡ በመቅሠፍት እጐበኛታለሁ። ምሕረቴን ግን፡ ከእርሱ አላርቅም፤ በእውነቴም አልበድልም፤ ኪዳኔንም አላረክስም፤ ከከንፈሬም የወጣውን አልለውጥም። ዳዊትን እንዳልዋሸው፡ አንድ ጊዜ፡ በቅዱስነቴ ማልሁ። ዘሩ፡ ለዘለዓለም፥ ዙፋኑም በፊቴ፡ እንደፀሓይ ይኖራል፥ ለዘለዓለም፡ እንደጨረቃ ይጸናል፤ ምስክርነቱ፡ በሰማይ የታመነ ነው።"* የሚለው፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ የዳዊት ልጅ ከኾነው፡ ከእስራኤላዊው ንጉሥ ሰሎሞንና ከኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ ልጅ፡ ከቀዳማዊ ምኒልክ ከተገኘችው፡ ከድንግል ማርያም በተወለደው፥ "የዳዊት ልጅ" እየተባለም በመጠራት፡ በዘለዓለማዊው ዙፋን[፲፯] ላይ ተቀምጦ፡ ለዘለዓለም በነገሠው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጽሟል።

በዚህ ጥቅስ ውስጥ እንደሚነበበው፡ እግዚአብሔር፡ ለዳዊትና ለዘሩ፡ የሰጠው፡ ይህ፡ የዘለዓለም ቃል ኪዳን፡ እንዲህ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ የተፈጸመ ሲኾን፡ "ለዘሩ" የሚለው ቃል፡ እስከክርስቶስ ልደት ድረስ ላሉትና በሥጋ የትውልድ ሐረግ፡ ከዳዊት ለተወለዱት፥ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ላሉት ደግሞ፡ ከእርሱ፡ ከዳዊት ልጅ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመንፈስ ቅዱስ ለተወለዱትና ለሚወለዱት መኾኑ ግልጽ ነው። በዚህና በሌላው የመዝሙራቱ ቃል፡ *"...እግዚአብሔር፡ ከዓለም አስቀድሞ፡ ንጉሥ ነው፤ በምድርም መካከል፡ መድኃኒትን አደረገ! ...ለኢትዮጵያ ሰዎችም፡ ምግባቸውን ሰጠሃቸው።"* የተባለው፡ እርሱ ራሱ፡ እግዚአብሔር፡ በዚህ ረገድ ያደረገው ቸርነት፡ እንዲህ በሚለው፡ በወንጌላዊው ዮሐንስ የማብራሪያ ጥቅሶች፡ ተፍታትቶ ተተርጕሟል። *"በመጀመሪያው፡ ቃል ነበረ፤ ቃልም፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም፡ እግዚአብሔር ነበረ። ...ያም ቃል ሰው ኾነ! ...ለሰው ኹሉ የሚያበራው፡ እውነተኛው ብርሃን፡ ወደዓለም ይመጣ ነበር። በዓለም ነበረ፤ ዓለሙም በእርሱ ኾነ! ዓለሙም አላወቀውም። የእርሱ ወደኾነው መጣ፤ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ኹሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት፡ ለእነርሱ፡ የእግዚአብሔር ልጆች ይኾኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው። እነርሱም፡ ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ፡ ከደም፡ ወይም ከሥጋ ፈቃድ፡ ወይም ከወንድ ፈቃድ[፲፰] አልተወለዱም።"*

አዎን! ይህ፡ መለኮታዊ ቃል ነው፡ እያንዳንዱን እውነተኛ ኢትዮጵያዊና እያንዳንዷን እውነተኛ ኢትዮጵያዊት፡ ለአጼነትና ለንግሥትነት የሚያበቃውን፡ መንፈሳዊዉን የእግዚአብሔር ልጅነት፡ ሊያቀዳጃቸው የቻለው!

\+ + +

# ምዕራፍ ፫

## ተወቃሹ ማነው?

ለእርስዎ (ለአቶ ናፍታሊን) ቀደም ብሎ፡ ከእኔ ተልኮልዎ ባገኙት ዕትም ውስጥ፡ ስለእግዚአብሔር እውነት በሰፊው በሚያብራራውና በሚያትተው መልእክት የተገለጸውን ፍሬነገር፡ አተኩሮ ለመመልከትና በማስተዋል ለማመዛዘን፥ በመጨረሻም በትክክል ለመረዳት ያቃተዎ ያለምክንያት አይደለም፤ በሥጋ ሞት ስለተለዩን፡ ስለአጼ ኃይለ ሥላሴ አምላክነት፡ እርስዎና እርስዎን የመሰሉት፡ "ራስተፈሪያውያን" የፈጠራችሁት መላምት፡ ምናልባት፡ በእርስዎ ላይ "እስከመጠናወትና እስከድንዛዜ ያደረሰ፡ ጽኑ አባዜን ያሳደረብዎ በመኾኑ ነው" ብሎ መገመት ይቻላል:: አዎን! እርስዎ፡ በአጠቃላይ፡ የመልእክቱን ዋና ዓላማ የሳቱትና ከሌሎቹ ብዙዎች ቁምነገሮች መካከል፡ ከዚህ በታች ተብራርቶ እንደቀረበው፡ በእኔ በኩል፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በሕይወት ሣሉም ኾነ ከዕረፍታቸው በኋላ፡ ለተቀባው ግርማዊ ሰውነታቸው የነበረኝንና አሁንም ያለኝን እጅግ ከፍተኛ አክብሮት፡ ለመገንዘብ የተሣነዎ፡ ለዚህ መኾኑ ጥርጥር የለበትም:: ይህም፡ እንደሚከተለው ነው:-

### አጼ ኃይለ ሥላሴ፡<br>የተቀቡ "ሥዩመ እግዚአብሔር" ናቸው::

በመልእክቱ ውስጥ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ እና የድንግል ማርያም ተጠሪና ዋና አገልጋይ በመኾን፡ በመለኮታዊቷ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት መሠረት፡ "ሥዩመ እግዚአብሔር" ተብለው፡ በተገቢው ቅዱስ ሥርዓት የተቀቡ በመኾናቸው፡ ለእኔ ሕጋዊ አጼዬና መሪዬ መኾናቸውን፡ በሃይማኖት ከማረጋገጤ ጋር፡ ሌላውም በዚህ መልክ እውቅና ሰጥቶ እንዲቀበላቸው አድርጌአለሁ::

እኔ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው በኢትዮጵያ፡ በኹሉም የአገልግሎት ዘርፎቿ ውስጥ ተመድቤ፡ እስከዚች ቀን ድረስ፡ የፈጸምኩትንና ወደፊትም፡ እስከመጨረሻዋ የስንብቴ ዕለት ድረስ የምቀጥለውን፡ ይህን ተግባሬንና ግዳጄን፡ በሙሉ የኢትዮጵያዊነት መብት ለማካሄድ የበቃሁት፥ ያንንም፡ የመንፈስ ቅዱስ የኾነውን የሕዝብ ምርጫ፥ የክህነት ሀብትና የምልክና ሹመት፡ በመለኮታዊው ጸጋ የተቀበልኩት፡ የቀድሞውን እጨጌ ባስልዮስን ጨምሮ፡ በዘመናቸው በነበሩት፡ በሦስቱ የቅዱሱ ኪዳን የአገልግሎት ቤቶች ተጠሪዎች አቅራቢነት፡ በእርሳቸው፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ የአጼነት ሥልጣን እንደነበረ፡ ራሴ፡ በሙሉ ልብ ተገንዝቤ፡ ለሌላውም፡ በገሃድ አሳውቄአለሁ:: ይህም፡ በዚሁ መልእክት ውስጥ፡ አግባብ በኾነው ሥፍራ ላይ፡ በግልጽ ተብራርቶ ታትሟል::

ስለዚህ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በእርግጥ፡ ከኹለቱ ሀብታት፡ ማለትም፡ የባሕርይ ገንዘብነታቸው፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ከኾኑት፡ ከአምላክነትና *"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* ከሚለው ስያሜ በቀር፡ በእኔ፡ በኢትዮጵያዊው ዘንድ፡ ለአጼው ሰውነት የተገቡትን ጸጋዎች ኹሉ አጠቃልለው የያዙ ነበሩ።

አዎን! ጃንሆይን፡ በሕይወተ ሥጋ ሣሉ፡ በአካል አውቃቸው ነበር። ያ እውቀቴ ግን፡ በታላቁ ግርማዊ መንበራቸው አካባቢ ባለው ክልል ብቻ የተወሰነ እንጂ፡ ከዚህ አልፎ፡ ቤተ ሰቦቻቸውና የቅርብ ምሥጢረኞቻቸው እስከሚያውቁት፡ እስከግላዊና ገመናዊ ሕይወታቸው የሚዘልቅ አልነበረም። ያም እንኳ ቢኾን፡ በእርሳቸው አመራር ጊዜ በነበረችው መለኮታዊት መንግሥት ውስጥ፡ ለአገልግሎት የተመደብኩት፡ ገና በወጣትነት ዕድሜ ሣለሁ ሲኾን፡ እርሱም፡ በዝቅተኛ ደረጃና በጀማሪ መልክ ስለነበር፡ ከጃንሆይ ጋር የነበረኝ ግንኙነትና አግባብ፡ ይህን ያህል ቅርበት ያለው ነበረ ለማለት ያዳግተኛል። አብዛኛውን ጊዜ፡ በእርሳቸው አካባቢ ለመገኘት ዕድል ይኖረኝ የነበረው፡ አስፈላጊ የኾነ ምክንያታዊ ሥርዓት ሲኖር ብቻ ነበር። ከዚያ በተረፈ፡ ከእርሳቸው ጋር በይፋና በግል፡ ቀጥታ የኾነ ግንኙነት አደርግባቸው የነበሩት አጋጣሚዎች፡ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው፡ በሦስቱም የቅዱሱ ኪዳን መንግሥት የአገልግሎት ዘርፎች ውስጥ በሹመት ተመድቤባቸው በነበሩት የኃላፊነት ቦታዎች ምክንያት፡ ለሥራ ጉዳይ የምቀርብባቸው ጊዜያት ነበሩ።

እንግዴህ፡ በዚህ ረገድ፡ እኔ ባወቅሁት መጠን፥ ከዚህም ጋር፡ ኹኔታዎችን ለማጤን የሚያስችለኝ፡ የአእምሮዬ ኃይል እስከፈቀደልኝ ድረስ እንዳስተዋልኩት፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በቃል ወይም በድርጊት፥ በይፋ ንግግራቸው ኾነ በሌላ መልክ፡ እንኳንስ፡ "አምላክ ነኝ" ሊሉ ቀርቶ፡ መስለው ለመታየት እንኳ፡ ፈጽመው ያልሞከሩ ሰው እንደነበሩ እመሰክርላቸዋለሁ። ኢትዮጵያውያን ዜጎቻቸው፡ አፍአዊ ከኾነውና በገሃድ ያዩት ከነበረው ምግባራቸው የተነሣ፡ እርሳቸውን፡ ይመለከቷቸው የነበረው፡ በቅዱሱ ኪዳን ተዋህዶ ሃይማኖት ጸንተው፡ ሥርዓቶቹን የሚያከብሩና ቤተ ክርስቲያንን የሚያዘወትሩ፥ "ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሰው የኾነው የእግዚአብሔር ልጅ መኾኑን፥ *፡ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ፡* የተባለውና የንጉሦች ንጉሥ የኾነውም እርሱ መኾኑን አምነው፡ አምልኮአቸውን ለእርሱ የሚፈጽሙ፡ መልካም ምእመን እንደኾኑ አድርገው ነበረ። እስከዚህ ድረስ የማውቅ መኾኔን፡ በማያወላውል ምስክርነት አረጋግጣለሁ። በሕሊናቸው ውስጥ የነበረውንና በግል ሕይወታቸው ምን ያደርጉ እንደነበረ የሚያውቁት ግን፡ ከእግዚአብሔር በቀር፡ ምናልባት፡ የቅርብ ረዳቶቻቸው፥ በተለይም፡ ቤተሰቦቻቸው ብቻ ይመስሉኛል።

ምንም እንኳ፡ የነገሩ ኹኔታ አስገድዶኝ፡ ቅዱሱን ኪዳን በሚመለከት፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ የሥልጣን ዘመን፡ የተፈጸሙትን ጉድለቶችና ድክመቶች፡ ከዚህ ቀጥሎ፡ በዝርዝር የምገልጻቸው ቢኾንም፥ በእኒህ ምክንያት ስለደረሱት በደሎች፡ ፈጣሪያቸው፡ በዕድሜያቸው ማብቂያ ላይ፡ በመለኮታዊ ዳኝነቱና ቸርነቱ፡ በደርግ እሥር ቤት እንዲያሳልፉት ባደረገው፡ የንስሓ ሱባዔ አማካይነት፡ ይቅር እንዳላቸው፡ በጸሎት እየተማመንሁ፡ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፡ ለእኔ፥ ወይም በእኔ ዘንድ፡ በእውነት "ሥዩመ እግዚአብሔር" ተብለው በመቀባት፡ በተገቢው ሥርዓተ ንግሥ፡ ለታላቁ ማዕርግ የበቁ፡ የዘለዓለም አጼዬ ኾነው ይኖራሉ።

እነሆ: እርስዎ ግን: "አጼ ኃይለ ሥላሴ: 'የይሁዳ አንበሳ' ሊባሉ የሚገባቸው: አምላክ ናቸው" የሚለውን መላምትዎን እንድቀበል: በደብዳቤዎ ውስጥ: መሞከር ብቻ ሳይኾን: ከላይ እንደታተተው: እርሳቸውን: በግል፥ በግንባር የማውቃቸውን እኔን: ሊያሳምኑኝ እስከመድፈር ስለደረሱ: ይህ ሙከራዎና ድፍረትዎ: እኔን: እጅግ አስገርሞኛል::

ለዚህ: እጅግ አሳዛኝ ሙከራዎና ድፍረትዎ መነሻ የኾነው መላምትዎ: በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት መሠረታዊ አቋም ላይ የተነጣጠረ: ፍጹም ሐሳዊነትና ጽኑ ርኵሰት በመኾኑ: ለመጨረሻው የፍዳ ኩነኔ ሊዳረግ የተገባው ድርጊት ኾኗል::

የአጼ ኃይለ ሥላሴን የተከበረ ሰውነት: "ለመንካት"፥ ኹለንተናዊ አቋማቸውን: "ለማቃወስ" እና በኅውን ገጸ ባሕርያቸውን "ለማጉደፍ" ስል: ተጻፍሬ እንደጻፍኩ አድርገው በመገመት: በአእምሮዎ: አስቀድመው ያውጠነጠኑትና በደብዳቤዎ አግዝፈው ያሠፈሩት: ያ: የተሳሳተ አስተሳሰብዎ: በዚህ የምስክርነት ቃሌ: ተንኖ እንደሚጠፋና የደፈረሰ ሕሊናዎን እንደሚያጠራልዎ ተስፋ አደርጋለሁ::

እንግዲህ: በደብዳቤዎ ውስጥ: አጼ ኃይለ ሥላሴን በሚመለከት: ስላነሡዋቸው ጥያቄዎች: ለማብራራት በምሞክርበት ጊዜ: ትኵረቴ ወይም ጭንቀቴ: በምንም ዓይነት መልኩ: ወደግል ሰብእናቸው: ወይም ሕይወታቸው ያዘነበለ ሳይኾን: "ለቅዱሱ ኪዳን: በመሐላ የገቡትን: የቃል ኪዳን ግዳጃቸውን: በተግባር ፈጽመዋል ወይ?" በሚለው ላይ ብቻ የተወሰነ ኾኖ: ለዚህ የቁምነገር ጥያቄ: ውልውል በሌለባት: በእግዚአብሔር እውነት: ተገቢውን መልስ ለመስጠት መኾኑን: እስካሁን ባነበቡት መጠን የተረዱት ይመስለኛል::

## ከ"አጼነቱ" ክብርና ሥልጣን ጋር ያለው ተጠያቂነት::

በዚህ ትውልድ ዘመን: በኢትዮጵያ ላይ ከደረሱት ጥፋቶችና በደሎች መካከል: አጼ ኃይለ ሥላሴ: "አንዳቸውንም ኾነ ኹሉንም አልፈጸሙም" በማለት: ከዚህ ተጠያቂነት: እርሳቸውን: ፍጹም ንጹሕና ነጻ ለማድረግ: በእርስዎ በኩል: በግንፍል ቀናዒነት የሚያካኺዱትን ጥረትዎን: በአንክሮ እመለከታለሁ:: ከእርስዎ ጋር: ቃል ለቃል ካደረግናቸው የአሳብ ልውውጦች መካከል: በአንዳቸው ጊዜ: ይህን አቋምዎን: ራስዎ በግል እንደገለጹልኝና እርሱንም ከመጨረሻው ግብ ለማድረስ: ወደፊት በቆራጥነት የሚታገሉበት መኾንዎን እንዳስታወቁኝ ትዝ ይልዎት ይኾናል:: ዳሩ ግን: ይህን የጀብደኝነት ስሕተት ለመፈጸም ማሰብዎ: የእግዚአብሔርን ጥበብና ዳኝነት: ለጥያቄ በማቅረብ: ማስተሐቀርዎ ነውና: በዚህ ረገድ: ራስዎን: በሌላ ሃይማኖታዊ ውስብስብ ውስጥ አስገብተው: በባሰ የሕሊና ችግር እንዳይዋጡ: እዚህ ላይ: ባለብኝ የኃላፊነት ግዳጅ: ደግሜ ላሳስብዎና ላስጠነቅቅዎ እወድዳለሁ::

በዚህ ዓለምና በምንኖረው የሕይወተ ሥጋ ዘመናችን: በእውን የሚኾነው ማናቸውም ነገር: የእውነት ፍሬና ማስረጃ ኾኖ: እውነታ ይባላል:: ከላይ: ቀደም ብዬ: የገለጽኩትን በመድገም: ይህ እውነታ: የእግዚአብሔር እውነት ግዙፍ መገለጫ ነው::

# ኢትዮጵያ:

እኔ: በኢትዮጵያዊነቴ የማምነው: እንዲህ ሲኾን: እርስዎስ: በዚህ ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ ያምናሉ? እንዲህ ከኾነ: በዘመናችን ስለታየው እውነታ: ማለትም: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ: በኢትዮጵያ ስለደረሰውና እየደረሰ ስላለው ጠቅላላ ኹኔታ: በእርስዎ በኩል: "ያስረዱ!" ቢባሉ: እንዴት ብለው ነው: የሚያስረዱት? እንደእርስዎ አስተሳሰብ: ጥረትዎ ተሳክቶ: "አጼ ኃይለ ሥላሴ: ከማናቸውም በደል ነጻ ናቸው" ቢባል: ታዲያ: በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ ስለደረሰውና እየደረሰ ስላለው የጊዜው ችግር: ተጠያቂው ማን ሊኾን ነው?

ተወቃሹ: እርሳቸው መሥርተው ያዋቀሩት: ያ ቤተ ምልክና ነው? ወይስ: የእርሳቸው ትሑት አገልጋይ የኾነችው ቤተ ክህነት ናት? ወይስ: እርሳቸው ዘርተው ያሳደጉት: የዚያ ትውልድ ቤተ ሕዝብ ነው? እርግጥ: እነዚህ ቤቶች: እያንዳንዳቸው: በየክፍላቸውና ኹሉም: በኅብረት፥ እኛ: እያንዳንዳችን ጭምር: በተጠያቂነቱም ኾነ በተወቃሽነቱ: ድርሻ አለን:: ነገር ግን: የቅዱሱ ኪዳን ባለአደራ ስለኾነችው: ኢትዮጵያ: በአጠቃላይ: ተጠያቂው ማነው? ለዚህማ: "ተጠያቂውም፥ ተወቃሹም: እግዚአብሔር ነው" ሊሉኝ: እርስዎ ይደፍሩ ይኾን? ምናልባት: ደፍረው ይህን የሚሉኝ ከኾነ: ጠያቂውንና ወቃሹን: ተጠያቂና ተወቃሽ ስላደረጉት: በመሠረቱ: "መጠየቅና መወቀስ የለም፤ አይኖርምም!" በሚለው ውሳኔ: ነገሩ ይቆማል::

እስቲ: ይሰሙኝ እንደኾነ: የኾነውን ልንገርዎ! በዚያ የወጣትነት ዕድሜዬ: "በወታደሮች ተይዤና ከሰባት ዓመታት በላይ ለኾነ ጊዜ ተግዤ: በእሥር ቤት እቆያለሁ" የሚል: "የምናልባት" አሳብ እንኳ: በሕልሜም፥ በእውኔም ከቶ አልነበረም:: ያ ኹኔታ: በእኔ ላይ ከመድረሱ አስቀድሞ: ለእርሱ የከፈልኩትን ዋጋ የሚመጥን በደል ፈጽሜአለሁ ብዬ: በሕሊናዬ የሚሰማኝ ወቀሳም፥ ጸጸትም ጨርሶ አልነበረብኝም:: ነገር ግን: ያ: ያላለምሁትና ያላሰብሁት ነገር: በእኔ ላይ ደርሶ ተፈጸመ! አዎን፥ አጼ ኃይለ ሥላሴ: በሕይወት እያሉና ከዙፋናቸው ሥልጣን ሳይነሡ ኾነ!

"እግዚአብሔር የለም" በሚል የጋርዮሽ ርእዮተዓለም የሚመራውና እኔን ጨምሮ: የቀድሞውን መንግሥት ባለሥልጣኖች ያሠረው: "ደርግ" የተባለው የጦር ኃይሎች አምባገነን ቡድን: ተቋቁሞ: ሥራ የጀመረው: አጼ ኃይለ ሥላሴ: ገና በሥልጣን ላይ ሣሉ ነበረ:: ምሕረት የሌለውን ሰይፉን: ጠቅላይ አዛዡ ወደነበሩት: ወደራሳቸው: አዙሮ: ከዙፋናቸው እስኪያወርዳቸውና ለእሥር እስኪያበቃቸው ድረስ: "ደርግ": የውጥንና የአሰሳ ተግባሮቹን በሙሉ ያካሄድ የነበረው፥ መንግሥታዊ አዋጆቹንም ኹሉ በይፋ ያስተላልፍ የነበረው: በአጼ ኃይለ ሥላሴ ስምና ፈቃድ ነበር::

የእኔን እሥራት በሚመለከት: በአጼ ኃይለ ሥላሴ ፈቃድ: የመንግሥታዊው ፈሊጥ ውሳኔ በተሰጠ ጊዜ፥ ከዚያም: የመያገሮው ሥልጣን: ለአስፈጻሚው ክፍል በተላለፈ ጊዜና ይህንኑ የእሥራቱን ትእዛዝ ለማስከበር: ከባድ የጦር መሣርያ የታጠቀ ወታደራዊ ኃይል: በብረት ለበስ ተሽከርካሪ ታጅቦ: በታይታ መልክ: ወደመኖርያ ቤቴ በተላከ ጊዜ: ሠፍኖ የነበረው: የጊዜው: የኢትዮጵያ መንግሥት ኹኔታ: ይህን የሚመስል ነበር::

## የዓለሙ መፋረጃ!

እንግዴህ: እንዲህ በመኾኑ: “ይህን ለምን አደረግህ?” ወይም “ይህ: በእኔ ላይ እንዲደርስ: ስለምን ፈቀድህ?” ብዬ: ፈጣሪዬን ልጠይቅ ነውን? ወይስ: እግዚአብሔርን፥ ወይም ሰዎችን በመውቀስ፥ ወይም: ልዩ ልዩ ምክንያቶችን በመደርደር: “እኔ ንጹሕ ነኝ” ብዬ: ራሴን: ከተጠያቂነት ነጻ ላደርግ ነውን? አይደለም! እንደኢትዮጵያዊነቴ: ከቅዱሱ ኪዳን የተነሣ: ለፈጣሪዬ የገባሁት ግዳጅ: ከኹሉ አስቀድሞ: ራሴን መውቀስ፥ ኃጢአተኝነቴን ማመን፥ “የተሰጠኝ ቅጣት የሚገባኝ ነው” ብዬ መቀበልና ንስሓ መግባት፥ በመጨረሻም: አዎን፥ በእርግጥ: አምላካዊ ምሕረቱን መማፀን ነው:: ከዚህ ቀጥሎም: *ለእውነታው: ማለትም: ከዓቅም በላይ የኾነው ኃይል፥ ወይም መለኮታዊው ድርጊት፥ ወይም አምላካዊው ዳኝነት* በሚሉ ልዩ ልዩ አጠራሮች ለምትታወቀው: *ለእግዚአብሔር እውነት:* ኹለንተናዬን: ምንጊዜም ማስገዛት ነው:: ይህም: ትላንት: ኾኗል፤ ዛሬ: እየኾነ ነው፤ ነገም: እንዲሁ ይኾናል::

በእነዚህ ኹሉ: የግል: የፈተናና የመከራ ጊዜያት: የማያቋርጥ ምንጭ ኾኖ: መንፈሳዊውን ኃይልና ብርታት: ያበረከትልኝ የነበረው፥ ዛሬም እያበረከተልኝ ያለውና ወደፊትም “ያበረክትልኛል” ብዬ የምተማመነው: እጅግ በተሣሠረ ፍቅር የተዋጥኩበት: ቅዱሱ ኪዳን መኾኑን: እዚህ ላይ ስገልጽ: ደስ ይለኛል:: ስለዚህ ነበር: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ: እስከዛሬ ድረስ: ያ ኹሉ: የፈተና ማዕበልና የመከራ እሳት: ሕይወቴን አጥለቅልቆ እያማታውና አቅልጦ እያነጠረው ሣለ: በውስጤ ይሰማኝ የነበረው ሰላምና ደስታ: በፍጹምነትና በጥልቅነት ሲመሰጥ፥ በውጭ ደግሞ: አፍአዊው አካሌ: ተቃራኒውን ኃይል: በግዘፍ ጽናትና ትእግሥት ተቋቁሞ: ህልውናዬ ሊቀጥል የቻለው::

፤እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት: የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታቸውን በሚመለከት: ይህን በመሰለው ባሕርያዊ አቋም ጸንተው እንደሚኖሩና እንዲኖሩ: ተስፋ ከማድረጌ ጋር: ጸሎቴም ነው:: ደግሞስ: እስካሁን እየተቀበልን ያሳለፍነው ፈተናና መከራ ኹሉ: በቅዱሱ ኪዳን አምላካችን ፊት: በፍጹም ንስሓ ወድቀን፥ በጉልበታችን ተንበርክከንና በግንባራችን ተደፍተን: የምሕረት ይቅርታን እንድንጠይቀው ሊያደርገን የሚበቃ አይኾንምን? እንግዴህ: እኛ: እያንዳንዳችን: ይህን ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ግዳጅ እስካልፈጸምን ድረስ፥ ወይም ካልፈጸምን በቀር: አሁን ከምንገኝበት ኹኔታችን: “የተሻለ ነው” የሚባል አንዳችም ለውጥ ሊመጣ እንደማይችል ልንገነዘብ ይገባል::

ታዲያ: በአሁኑ ጊዜ: የአጼ ኃይለ ሥላሴን ቤተሰብና ተወላጆች ጨምሮ: በግልም ኾነ በሕዝብ ደረጃ: እየቀጠለ የሚታየው: የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን አሳዛኝ ኹናቴ: በመሻሻል ፈንታ: እየባሰ የሄደው ስለምን ይመስለናል? ወይስ: እንደርስዎ: አጻጻፍ: የኢትዮጵያ ሕዝብ: “በምድረ በዳ ውስጥ የመኖር” ዕድሉ ለምን የሚቀጥል ኾነ?

ለዚህ የተሳሳተ አስተያየትዎ: በብርቱ ኃይለ ቃል ምላሹን: እንደሚከተለው እሰጣለሁ:- ኢትዮጵያውያን: “በምድረ በዳ ውስጥ የመኖር” መራራ ዕድል ተቀባዮች የኾኑት: እርስዎ: በደብዳቤዎ መዝጊያ ላይ: በወቀሳ መንፈስ ባሠፈሩት አስተያየትዎ እንደገለጹት: “ያመፁ ሕዝቦች እንደመኾናቸው”: በአጼ ኃይለ ሥላሴ አመራር: “የቀረበላቸውን መልካሙን በረከት: እምነው መቀበልንና በይፋ ማሳወቅን” እምቢ በማለታቸው፥ የእርሳቸውንም “የጥበብ ቃሎች ሰምተው ባለመፈጸማቸው” አይደለም::

እንዲያውም፡ ለዚህ፡ ትክክለኛ መልስ ኾኖ የሚቀርበው ምክንያት፡ ራሱ፡ የዚሁ፡ የውቅስ አስተያየትዎ፡ ተቃራኒ አጻፋው ኾኖ ይገኛል፤ ይኸውም፡ የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን፡ ባሁኑ ጊዜ፡ እንደእርስዎ አባባል፡ "በምድረ በዳ ውስጥ የመኖር" መራራ ዕድል ተቀባዮች የኾኑት፡ ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ፡ ሰብአዊ አእምሮ ያመነጫቸውን፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴን "የብልሃት ቃላት" ሰምተው በመከተል፡ በመለኮታውያን የዘውድ መሪዎቻቸው፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ላይ በማመፃቸው መኾኑን፡ እውነተኛው ሃይማኖታዊው ሕሊና ይገነዘበዋል፤ እንዲያውም፡ የዚህ ዓመፃቸው መንሥዔ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ አመራር፡ ለሰዎች ቃል ኪዳናት ቅድሚያና እውቅና ሰጥተው፡ በእነርሱ በመታመን፡ ከአምላካቸው እግዚአብሔር ጋር፡ በመሐላ የተጋቡትን ቅዱሱን ኪዳን በክህደት ማፍረሳቸው ኾኖ መገኘቱን፡ እርስዎ ሊያውቁት ይገባል።

## "ድፍረት!"፡ የትኛው ዓይነት?

በዚህ ጽሑፍ አማካይነት፡ እስከዚህ ተጉዘው፡ በደረሱበት የመረዳት ደረጃ፡ አሁን፡ ራስዎን፡ ለተስተካከለ ቀና አመለካከት እንዳበቁ በማመን፡ ከዚህ ቀጥሎ ለሚቀርብልዎ የዳኝነት ጥያቄ፡ የሚሰጡት ምላሽ፡ ምን ዓይነት እንደኾነ፡ እስቲ እንመልከት! የምንነጋገርበትን አርእስተ ጉዳይ በሚመለከት፡ በእግዚአብሔር ላይ የተፈጸመ፡ ታላቅ ኃጢአት ኾኖ የሚቆጠረውን የስድብ ቃል፡ ገሃድ በኾነ ድፍረት የተናገረና ለዚህም ጥፋቱ፡ ፍትሐዊዉን የመለኮት ቅጣት ሊቀበል የሚገባው ማን ይመስልዎታል? ዕሩቅ ብእሲ የኾኑትን፡ አጼ ኃይለ ሥላሴን፡ አምላክ ለማድረግና *"ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚለውን መለኮታዊ ቃል፡ ለእርሳቸው ለመስጠት፡ በድፍረት እየሞከሩ ያሉት፡ እርስዎ ነዎት? ወይስ፡ ዘለዓለማዊው ካህን ንጉሥና ሰው የኾነው የእግዚአብሔር ቃል፥ እንዲሁም፡ "ከይሁዳ ነገድና የዳዊት ሥር የኾነው፥ ድልም የነሣው አንበሳ"፡ ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑን በማረጋገጥ፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ያዋጅ ቃሏን ያሰማችውን፡ የእግዚአብሔርን እውነት፡ መልእክቷን፡ በትክክል ያስተጋባሁት እኔ?

ኧረ ለመኾኑ፡ ማንም "ሊነካው" የማይፈቀድለት፥ አለዚያ፡ የነካው፡ መንካቱ፡ እንደልዩ "ድፍረት" ተቆጥሮ፡ ለጽኑ ቅጣት የሚዳርገው መኾኑ የተነገረለትና መለኮታዊ ቅድስና ያለው፡ የማነኛቸው አካል ነው? የኢየሱስ ክርስቶስ? ወይስ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ? ራሱን፡ "ድፍረት" የሚለውን፡ የምንነጋገርበትን ቃል፡ አሉታዊ ትርጓሜውን ወስደን፡ ብንጠቀምበት፡ ማነኛችን ነን የደፈርን? እርስዎ? ወይስ እኔ? በዚያ አተረጓጉም ከተወሰደማ፡ ስለድፍረቱ፡ ማነኛችን ነን፡ ጽኑ የኾነውን ቅጣት መቀበል የሚገባን? እርስዎ? ወይስ እኔ?

ይህንኑ፡ "ድፍረት" የሚለውን ቃል፡ በአዎንታዊ ትርጓሜው ወስደን ብንጠቀምበት፡ እንኳንስ የእግዚአብሔር ስለኾነችው እውነት ቀርቶ፡ ቀላል መስላ ስለምትታየው፡ ስለተራዪቱ የእውነት ቅንጣት እንኳ ቢኾን፡ በዚህ፡ "የሠለጠነ" በሚባለው ዘመናዊ ኅብረተሰብ መካከል፡ በገሃድ ለመናገርና ለመመስከር፡ በሚበቃው መጠን፡ እጅግ ደፋሮች ኾነን መገኘት እንደሚገባን አያውቁምን?

የዓለሙ መፋረጃ!

አሁን ባለንበት ኹኔታችን፡ በዚህ ተፃራሪና ክፉ በኾነው ዓለም ውስጥ፡ ስለእግዚአብሔር እውነት፡ ጮክ ብለን፥ አሰምተን ለመናገር፡ ከእኛ፡ ምን ያህል፡ የጋለ ድፍረት ወይም ቆራጥ የኾነ ጀግንነት ይፈለግብናል? ለዚህም፡ ቀደም ብሎ፡ ከእኔ፡ በጽሑፍ ለተሠነዘረው የድፍረት አገላለጽ፡ እርስዎ፡ በደብዳቤዎ የሰጡት፡ የከረረ ምላሽ፡ ራሱ፡ በቂ ማስረጃ መኾኑን መመልከት ይበቃል።

በቅዱሱ ኪዳን የተመሠረተችው፡ አገሬ ኢትዮጵያ፡ ለምትመራባት *የእግዚአብሔር እውነት*፡ የገባሁትን የቃል ኪዳን ግዳጅ ለመፈጸም፡ በምጥርበት ጊዜ፡ ምን ዓይነት ችግር እንደሚገጥመኝ፡ ቀደም አድርጌ፡ ገና በልጅነት ዕድሜዬ ሣለሁ እንኳ፡ ይታወቀኝ ነበር። አዎን! ስለእግዚአብሔር እውነት፡ የምስክር ቃላቸውን፡ በድፍረት የሚያሰሙ ኹሉ፡ ከየራሳቸው ኅብረተሰብ ዘንድ ሳይቀር፡ የሚጠብቃቸው ዕድል ቢኖር፡ መዋረድ፥ መጠላትና ከማኅበራዊ ኑሮ መገለል፥ እንዲሁም፡ መሰደድና እስከመስቀል ሕማም በሚያደርስ፡ በማናቸውም ዓይነት መከራ መፈተን መኾኑ፡ የተረጋገጠ ነው።

በዚህ ረገድ፡ *የእግዚአብሔር እውነት*፡ ኢትዮጵያን በሚመለከት፡ ስለምትናገረው ቃል፡ ለሰጠሁት ምስክርነት፡ እርስዎ የጻፉልኝ ተፃራሪ መልስ፡ ይህን ያህል የሚያስደንቀኝ ኾኖ አላገኘሁትም። ምክንያቱም፡ የተከታዮቹን፡ የመንፈስ ኃይል እያጠናከረ የሚያበረታታቸውና ለዘወትር ሳይለይ የሚመራቸው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የራሱን ሕማማተ መስቀል፡ አርአያ አድርጎ እያቀረበ፡ ከላይ የተጠቀሱት የመከራ ዓይነቶች ሳይደርሱ እንደማይቀሩ፡ በትንቢታዊ ቃሉ፡ አስቀድሞ በሚበቃ ስላስጠነቀቃቸው ነው። ስለዚህ፡ የእርሱ የኾኑት ወገኖቹ፡ እኒያን በመሰሉ ገድሎች፡ በሚጠመዱባቸው ጊዜያት፡ በቅዱሱ ኪዳን ለተገለጸችው፡ ለእግዚአብሔር እውነት፡ የገቡትን የቃል ኪዳን ግዳጃቸውን፡ ከግብ ለማድረስ፡ እስከመጨረሻው የጸኑ ኾነው ይገኙ ዘንድ፡ እነዚያ የጌታ ቃላትና ምግባሮቹ፥ መንፈሱም፡ እያስታወሱ ያጽናኗቸዋል።

\+ \+ \+

# ምዕራፍ ፬

## የመጨረሻው አጼ፡
## አሳዛኝ ፍጻሜ እና ጦሱ!!!

ስለእግዚአብሔር እውነት፡ ቀደም ብዬ፡ አግባብ ላላቸው ተቀባዮች ባደረስኩት መልእክት ውስጥ፡ ከቅዱሱ ኪዳን ሥርዓቶች ጋር በተያያዘ መልካቸው፡ ከአጼዎቻችን መካከል፡ ጥቂቶቹ፡ ያደረጓቸው አንዳንድ በጎ ምግባራት ወይም ስሕተቶች፥ ያሳዩዋቸው፡ መልካም ባሕርያት ወይም ድክመቶች፥ የፈጸሟቸው፡ የታማኝነት ወይም የክህደት ድርጊቶች፡ በመጠኑም ቢኾን፡ ተጠቅሰው እንደነበር ይታወሳል። እርስዎ፡ ለዚሁ መልእክት የሰጡት ምላሽ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ ሥራዎች፡ የእግዚአብሔር በኾነችው፡ የእውነት መንፈሳዊ መነጽር፡ እንደገና፡ በቅርብ እንዲታዩና በጥልቀት እንዲመረመሩ ስላደረገ፡ የመልእክቱ ዓላማ፡ በዚህ መልኩ፡ በእርግጥ፡ ከግቡ ደርሷል ማለት ይቻላል።

ስለዚህ፡ እስቲ፡ ለጥቂት አፍታም ቢኾን፡ ራስዎን ለአስተዋይነት ያብቁና፡ *እውነታውን* አመዛዝነው ለመመልከት ይሞክሩ! ለዚህም፡ በቅድሚያ፡ መንፈሳዊ ዓይንዎን ሊከፍቱ ይገባል። ከዚያ፡ እኔን በሚጨምረው፡ በዚህ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ትውልድ፥ በቤተሰባቸውና በራሳቸው ሰውነት ላይ ሳይቀር፡ የደረሰውንና እየደረሰ ያለውን ኹኔታ ይዩ! ታዲያ፡ ይህ ኹሉ የኾነውና እየኾነ ያለው፡ "ከቶ ለምንድር ነው?" ብለው አልጠየቁም ኖርዋል? የዚህ ኹሉ ችግር፡ መነሻ ምክንያት፡ ማንም አብራርቶ ሊያስረዳው የማያስፈልግ፡ በራሱ ግልጽ ኾኖ የሚናገር፡ በቂ አይደለምን? ለዚህም፡ የሚከተለውን ማብራሪያ ይመለከቷል፦

## ኢትዮጵያ፡
## ስለቅዱሱ ኪዳንዋ ስትፋረድ!

እንዲያውቁት የምፈልገው፥ አጥብቄና አረጋግጬም ልነግርዎ የሚገባኝ፡ አንድ ነገር አለ፤ ይኸውም፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴን ቤተሰብና ተወላጆች ጨምሮ፡ የዛሬዪቱን ኢትዮጵያና ሕዝቧን፡ በያሉበት፡ እያጥለቀለቀ ለቀጠለው፡ ለዚህ ኹሉ ማዕበላዊ ሁከትና መከራ፡ ዓቢይ የኾነው፡ እውነተኛ ምክንያት፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ፡ በሥውር የተካኼደውና የተፈጸመው ኑፋቄና ክህደት መኾኑን ነው። ይህም፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን፡ ለአያሌ ሺህ ዓመታት፡ መንፈሳዊ ቅንዓት በተመላው ጽኑ ፍቅር ጠብቀው ባቆዩት፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸው ውስጥ፡ ተከብረው የሚገኙትን፡ መለኮታውያን ሥርዓቶች በመሻርና ምልክቶቹን በማርከስ፡ በተለያዩ ዘዴዎች የተካኼዱትን የድፍረት ድርጊቶች፡ ያጠቃልላል። ከዚህ የተነሣ፡ እነሆ፡ መለኮታዊውን የእሳት ነበልባል የተረከሰው፡ ያ፡ ማንም፡ በምንም ጥበብና ኃይል ሊቋቋመውና ሊመልሰው ያልቻለው፡ የመርገሙ ቁጣ መጣ!

## የዓለሙ መፋረጃ!

ይልቁንም: ወደተነሣንበት አርእስተ ጉዳይ ስናተኩር: አጼ ኃይለ ሥላሴን: ለአምላክነት ደረጃ ለማብቃት ያቀዳችሁት ከንቱ ዓላማና ይህንኑ ዓላማችሁን: ከመጨረሻው ግብ አድርሳችሁ: እውቅናን ለማስገኘት ስትሉ: የምታደርጉት ሐሳዊ ሙከራ: ከላይ ከተጠቀሱት: ከኑፋቄውና ከክህደቱ ከሥተቶች መካከል: ጣምራ ጥረታችሁ ኾኖ እናገኘዋለን:: ይህም: የኢየሱስ ክርስቶስ: የባሕርይ ገንዘቡ ኾኖ: ለእርሱ ብቻ የተሰጠውን: *"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚለውን መለኮታዊ ቃል: በምንም ዓይነት አተረጓጐም ቢኾን: ወደእርሳቸው ሰውነት "እናዛውር!" ብላችሁ የምታካሂዱት ፍሬቢስ ትግላችሁ ነው::

በሃይማኖታችን መሠረት ላይ ጽኑ ቀውስን ሊያስከትል የሚችለውን: ይህን የመሰለውን ኑፋቄ: ራሳቸው: አጼ ኃይለ ሥላሴ: በሥልጣን በነበሩበት ጊዜም ኾነ: ዛሬ በሕይወት ያሉት ቤተሰቦቻቸው: ነገሩን እያወቁ: እንዳላወቁ ኾነው ከመታየት፥ ቸል ከማለትና ከማግለል በቀር: በማያዳግም ቃል: በአደባባይ: በይፋ ሳይቃወሙትና ሳያስተሓቅሩት በመቅረታቸው: ይህ አሳዛኝ ኹኔታ: እየተባባሰና እየተጠናከረ ሊኼድ ችሏል::

የአሁኑ ትውልድ: የዕድለቢስነት ጽዋው ኾኖ: ማንነቱን ከሚያሳውቀው: ከቅዱሱ ኪዳን ማሕፀን ጋር የተያያዘው እትብቱ ተቋርጦ: በዚህ ድንቍርና እንዲያድግ: በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አመራርና አስተዳደር ሥር: ኾን ተብሎ: የተፈረደበት ሰለባ በመኾኑ: *"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚለው አምላካዊ ቃልና ምልክት የተሰጠው: ለእውነተኛው ብቸኛ ባለቤት: ለኢየሱስ ክርስቶስ ሳይኾን: "ለአጼ ኃይለ ሥላሴ ነው" ብሎ እንዲያምን ተገደደ::

ይህ ኹሉ ሊደርስ የቻለው: ያለበቂ ምክንያት አልነበረም፤ ከዚህ አስቀድሞ: ታይቶ በማይታወቅ ረቂቅ ብልሃት: ተካሂዶ የተፈጸመው: ከላይ የተወሳው መሠረታዊ ቀውስ ሳያንስ: የአገሪቱ ሥርዓተ ትምህርት: በሥጋዊው እምነት ላይ ተመሥርቶ እንዲዘጋጅና ከዚህ የተነሣ: ኢትዮጵያዊዉ ወጣት: አእምሮው: በምዕራባውያን ፍልስፍና ብቻ: በከፍተኛ ፍጥነትና ኃይል እየተወቀረ እንዲታነጽ ተደረገ! ይህም አልበቃ ብሎ: የመንግሥቱ የሃይማኖት ትምህርት: በተጠና ዘዴ: በመላው የአገሪቱ ትምህርት ቤቶች ውስጥ እንዳይሰጥ ታገደ! በዚህ ረገድ: ምን ዓይነት ትውልድ ተፈጠረ? ከሥሩ እንደተበጠሰ ሐረግ: ወይም ከምንጩ እንደተቋረጠ ፈሳሽ: ወይም ከተዘራው መልካም ዘር ተለይቶ እንደበቀለ ባዕድ ቡቃያ: ማንነቱን የማያውቅ፥ ፀረ ኢትዮጵያዊ፥ በተለይም: አባቶቹና እናቶቹ በፍቅር ከተሠዉለት: ከቅዱሱ ኪዳን ጋር በተያያዘው: በማናቸውም ቅርሱ ላይ: ፍጹም ጥላቻና የከረረ ተቃውሞ ያለው ትውልድ!

እነሆም: የመከሩ ወራት በደረሰ ጊዜ: አጼ ኃይለ ሥላሴ: ለአያሌ አሥርተ ዓመታት: "መልካም ዘርን ዘርቼበታለሁ" ብለው: ስለፍሬያማነቱ በሙሉ ልብ ተማምነውበት ወደነበረው እርሻቸው: አጫጆች ተላኩ:: ነገር ግን: አጫጆቹ: ከእርሻው ሲደርሱ: ኹሉን ተስፋ የሚያስቆርጥ እንግዳ ትርኢት ገጠማቸው! አዎን፥ ያሳዝናል! መከሩ: እንክርዳድ ኾኖ ተገኘ! መቼም: ገበሬ: የሚያጭደው የዘራውን ነው፤ የሚበቅለው: ያው የተዘራው ነውና! ምንም ቢኾን: ያልተዘራው አይበቅልም::

ይህን: የደረሰውን አሳዛኝ ፍጻሜ አስቀድመው ተናግረው የነበሩት እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን: በተለይ: ለአጼ ኃይለ ሥላሴና ለባለሥልጣኖቻቸው: ያለማቋረጥ የሰጡት ማስጠንቀቂያ: በንቀት ቸል እየተባለባቸው ያሳለፉትን የጭንቀት ዘመናቸውን በማስታወስ: ንጹሕ ስንዴን በተዘራው መልካም እርሻ መካከል: በቅሉ ኋለተገኘው እንክርዳድ: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: በወንጌል የተናገረው: ያ ምሳሌ መፈጸሙን ያረጋገጡት: በዚያ ወቅት ነበር:: ከእርሱ: ማንም ሊያመልጥ የማይቻለው: የጥፋቱ ዋጋ የሚከፈልበት፥ ማለትም: ቅዱሱን ኪዳን ስለመካድና ስለማርከስ የተፈጸመው የዓመፅ ኃጢአት: ያስከተለው መለኮታዊ ቅጣት[፲፱] የሚፈጸምበት ቀን: በመጨረሻ መድረሱንም አስተዋሉ!

አጼ ኃይለ ሥላሴ: አገራቸውን: ለኤውሮጳውያን ሥልጣኔ ለማብቃት ከነበራቸው: እጅግ ከተመሠጠው ጽኑ ምኞታቸው የተነሣ: ወሰን ባልነበረው የአባትነት ፍቅር ኲትኲተው ያሳደጓቸው: በእንክርዳድ የተመሰሉትና የዚህ ትውልድ ፍሬዎች የኾኑት ልጆች: በዚያ: የመከራ ወራት በተጀመረበት ሰሞን: የፈጸሙትን እስቲ እንመልከት!

የእግዚአብሔር መንግሥት ለኾነችው ኢትዮጵያ: በሕያው ምልክትነታቸውና በገናና መሪነታቸው: በዓለም ላይ: ታላቅ ሞገስ የነበራቸውን: እኒያን: በሥራ ብዛትና በዕድሜ መግፋት ምክንያት: ዐቅማቸው የደከመውን: አረጋዊ አባታቸውን: ይዘው: ከዙፋናቸው በማውረድ፥ እስከማሠርና በመጨረሻም እስከመግደል ደረሱ!

ያን የመሰለ ተወዳጅነት፥ እውቅናና ክብር የነበራቸው አጼ ኃይለ ሥላሴ: ከዚያ: ከወደቁበት አዘቅት የሚያወጣቸውና ከተያዙበት ወጥመድ የሚያስለቅቃቸው: አንድም ረዳት፥ ወገን ሳያገኙ ቀሩ! የቅዱሱ ኪዳን አፍ በመኾን: ስለእግዚአብሔር እውነት: አስፈላጊውን ቃል መናገር ይገባቸው የነበሩት፥ ከምንኵስናው ቆብ ጀምሮ: እስከኤጲስ ቆጶስነት ደረጃና እስከመጨረሻው የሢመት ማዕርጋቸው: በእግዚአብሔር ፊትና በአጼ ኃይለ ሥላሴ ፊት እየቀረቡ: ስለታማኝነታቸውና ምንጊዜም ሳይከዷቸው: በተደጋጋሚ የመሐላ ቃል ኪዳን የፈጸሙት ጳጳሳት፥ በተለይም የቤተ ክህነቱ ተጠሪ የነበሩት: እጨጌ ቴዎፍሎስ፥ እንዲሁም: እንደመንታ: የአንድ እናት ጡት ጠብተው: አብሮአቸው ያደጉ ከመኾናቸው የተነሣ: እንደወንድማቸውና ጓደኛቸው የሚቆጠሩት: ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ እንኳ: የእነዚህ ዓመፀኞች ልጆች ተባባሪ በመኾን: አሳልፈው ከመስጠት በቀር: ለትድግናቸው (ሊያድኗቸው) አልደረሱላቸውም::

ምሥጢራዊ ከኾነው: አሟሟታቸው በፊትና በኋላ: ተከታትሎ የደረሰው ኹሉ: እጅግ የሚያሠቅቅ በመኾኑ: ያንን: ወደኋላ መለስ ብሎ ማሰቡና ማስታወሱ እንኳ: አእምሮን: በጽኑ የኀዘን ፍላፃ ጠልቆ የሚነካና ሊቋቋሙት የሚከብድ: መራራ ትዝታን የሚያስከትል ኾኖ ይገኛል:: ይኹን እንጂ: ድርጊቱን ለማጠቃለል: እንደርሳቸው ተይዘው ከታሠሩት መካከል: በሰላማዊውና በጠሩ ክፍላት: በአዛውንትነትም ኾነ በጉብልነት ዕድሜ: በፍጹም ታማኝነትና መሥዋዕትነት ያገለገሏቸው አማካሪዎቻቸውና ምሉካኖቻቸው፥ ሹሞቻቸውና መኰንኖቻቸው: አብዛኞዎቹ: ያለፍትሕ: በተፋጠነ ውሳኔ: በጭካኔና በግፍ መገደላቸውን: ባጭር አውስቶ ማለፉ ብቻ ይበቃል::

## የዓለሙ መፋረጃ!

ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን: ምንጊዜም: ያለቅዱሱ ኪዳን: ምንም ዓይነት ትክክለኛ ዳኝነት ወይም የፍትሕ ርትዕ ሥርዓት: ሊገኝላቸው ከቶ አይችልም፤ ቀድሞም አልነበራቸውም፤ ዛሬም የላቸውም፤ ወደፊትም አይኖራቸውም:: ይህ እውነት: በኢትዮጵያውያን ዘንድ: ከልብ ሊታወቅ የሚገባው ቁምነገር ነው:: ቅዱሱ ኪዳን ከመሻሩ የተነሣ: ይህች የቅዱሱ ኪዳን አገር: እንደትንቢቱ ቃል: እነሆ: ከማንነታቸው መሠረት በተናወጹ: በራሷ እንክርዳድ ልጆች አረመኔያዊ እጅ: የራሷ የቃል ኪዳን ሕዝብ ተደምስሶ እስከመጥፋት በሚደርስ ጭካኔ፥ የደም ጐርፍ የሚወርድባትና የእርስበርስ የበቀል ጦርነት የሚካሄድባት ምድር ኾነች!

በጽሑፍ የታወጀውን ሕገ መንግሥት፥ ከእርሱ እየሠረፁ የወጡትንም: መላዎቹን የአስተዳደር አቋሞችና የሥራ አውታሮች ጨምሮ: ለሥነ መንግሥት አመራር፥ ለትምህርት ሥርጭት፥ ለህብት ልማት፥ ለማኅበራዊ ኑሮ ዕድገትና ለጦር ኃይሉች ዝግጅት: አስፈላጊዎች ናቸው ተብለው የተጣሉትን መሠረቶችና የቆሙትን መዋቅሮች: ከነዘርፋቸው በመዘርጋት ረገድ: አጼ ኃይለ ሥላሴ: ለሃምሳ ዓመታት ያህል የደከሙበት: ያ ኹሉ የተቀነባበረ ብሔራዊ ግንባታ: ከእርሳቸው በኋላ: አንድ አንድ እያለ ፈራርሶ ወዳደቀ!

ስለምን ይህ ኹሉ ደረሰ? በመድረሱስ: ለምን ያስገርማል? በአጼ ኃይለ ሥላሴ ይመራ የነበረው ትውልድ: በቅዱሱ ኪዳን ዋስትና ከተረጋገጠውና የእግዚአብሔር እውነት ከምታበረክተው አጠቃላይ ጥበቃ ይልቅ: "የለም፥ የክፋት ሥር ነቀል ርእዮተ ዓለም: ሥልጣን አግኝቶ ቢያይል ይሻላል!" ብሎ: ምርጫውን ወደዚያ ሥጋዊ ፍልስፍና ማድረጉን በግብሩ አላሳየምን? ያ ትውልድ: ራሱን: "እግዚአብሔር የለም" እስከማለት ከሚያደርስ: የመጨረሻ የውድቀት አዘቅት አዋርዶ: ያን የመሰለውን ርእዮተ ዓለም በቀላሉ ለመቀበል የተዘጋጀና የተመቻቸ ሰብአዊ ሰሌዳ ኾኖ እንዲገኝ መደረጉን: አሌ የሚል አስተዋይ ተመልካች ይኖራልን? ሊኖር አይችልም፤ ምክንያቱም: በዛሬው ዘመን: በሕይወት ቆሞ የሚንቀሳቀሰው: እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር: በትውልዱ የተደረገውንና በጊዜው የኾነውን ኹሉ: ራሱ: በአባልነቱ ጭምር: የዓይን ምስክር ኾኖ: ያየው ስለኾነ ነው!

ከአጼ ኃይለ ሥላሴ የፍጻሜ ዘመን በኋላ: ይኸው: በዓይናችን ፊት: በአገር ደረጃ: እየቀጠለ የሚታየው: ታላቅ የጥፋት አወዳደቅ: ጌታ: በወንጌል የተናገረው: ከዚህ የሚከተለው ቃሉ: ሊታበል ከማይታሰብ ብቅዓት ደርሶ መፈጸሙን: በማያጠራጥር መንገድ ያረጋግጥልናል:: "ይህን ቃሌን ሰምቶ: የሚያደርገው ኹሉ: ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ: ብልህ ሰውን ይመስላል:: ዝናብም ወረደ፤ ጐርፍም መጣ፤ ነፋስም ነፈሰ፤ ያንም ቤት ገፋው! ነገር ግን: ያ ቤት: በዓለት ላይ ስለተመሠረተ: አልወደቀም:: ይህን ቃሌን ሰምቶ: የማያደርገው ኹሉ: ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል:: ዝናብም ወረደ፤ ጐርፍም መጣ፤ ነፋስም ነፈሰ፤ ያንም ቤት መታው! ወደቀም! አወዳደቁም ታላቅ ኾነ!"[II]

አጼ ኃይለ ሥላሴ ያፈሩት ትውልድ ግን: ራሱን: እንዴ: ለጥፋት ፍዳ ዳርጓልና: ኢትዮጵያዊነትን ሳስገኘው: ለቅዱሱ ኪዳን: መሠረቱም፥ ዘውዱም የኾነው: እርሱ: ኢየሱስ ክርስቶስ ለተናገራቸው: ለእነዚህ መለኮታውያን ቃላት የሰጠው ግምት: በንቀት ሰምቶ ከማለፍ በቀር: በቁም ነገር ማዳመጥን እንኳ አልነበረም::

የእግዚአብሔር ቃል የኾነው፡ እርሱ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን፡ ስለራሳችን ዘለዓለማዊ ደኅንነት ስንል፡ የቃል ኪዳን ግዳጃችንን ከመፈጸም፡ ብዙ ስንፍና እንዳያጠቃን፡ እኛን የቅዱሱን ኪዳን ልጆቹን፡ በተለያየ መንገድና ባልተቋረጠ ይዘት፡ ከማሳሰብና ከማስጠንቀቅ የቦዘነበት ጊዜ አልነበረም።

## የገድል ተሳታፊነት፥ ገና በልጅነት።

እኔም፡ በዚያ ዘመን የተገኘሁ፡ የትውልዱ፡ አንዱ አባል እንደመኾኔ መጠን፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ የሚገኝበትን አሳሳቢ ኹኔታ በመመልከት፡ ከመንፈሳዊ ቅንዓት የተነሣ፡ በሕሊናዬ ውስጥ የሁከትና የሥጋት ስሜት ሊያድርብኝ የጀመረው፡ ገና በአሥራዎቹ ዓመታት ዕድሜዬ ውስጥ፡ በትምህርት ቤት ሣለሁ ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ በኢትዮጵያዊነቴ፡ እስከዛሬ ድረስ፡ በሙሉ ልቤ ተጠምጄበት ለምገኝበት፡ ለዚሁ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ሕያው ውርስ ጥበቃ፡ ራሴንና ጊዜዬን፥ እውቀቴንና ጉልበቴን፥ ያለችኝን አነስተኛ ጥሪት ሳይቀር በማቅረብ፡ ይህንኑ የተቀደሰ ዓላማ በበለጠ ለማሳወቅና ለማስፋፋት የሚረዱ፡ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችንና ተግባሮችን በመወጠንና በማካኼድ፥ በእነርሱም ውስጥ በመሳተፍ፡ በዚያን ጊዜ አስፈላጊ መስሎ የታየኝን አገልግሎት ቀጠልሁ።

ከእነዚህ እንቅስቃሴዎችና ተግባሮች መካከል፡ በመድረክ ላይ የቀረቡት ተውኔቶች፥ በጦማራተ ሕዝብ (gazzetta) ላይ የወጡት መጣጥፎች፥ ሊመጣ ስላለው አደጋ በማስጠንቀቅና መፍትሔ ሊኾኑ የሚችሉ አሳቦችን በማከል፡ በደብዳቤ ቤት በኩል፡ ለባለሥልጣኖች፡ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ ሳይቀር፡ የተላለፉት ግልጽ ማሳሰቢያዎች፡ ሊጠቀሱ የሚገባቸው ጥቂቶቹ ናቸው። የእነርሱንም አርእስት፡ ለማውሳት፡ እስከ ፲፰ ዓመቴ ድረስ ባለው ዕድሜዬ ውስጥ፡ በዓፀደ ቤተ ክርስቲያንና በአደባባይ፡ "ሕፃኑ መከረኛ ሰማዕት"፥ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤትና በወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ማኅበር አዳራሾች፡ "እየው ያን መከራ! የደስታ ጮራ!" የተባሉት፡ ለሕዝብ የታዩት ተውኔቶቼ፥ "ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊ"፥ "አዲስ ዘመን ለወጣት ትውልድ"፥ "የአንክሮ ጥሪት" በሚሉ አርእስት፡ በጦማራተ ሕዝብ፡ በተለይም፡ በ"ዛሬዪቱ ኢትዮጵያ" ዓምዶች ላይ በተከታታይ ይወጡ የነበሩት ድርሰቶቼ፥ ቀጥሎም፡ "ምናሴ! የመከራዬ ደስታ፡ ዓለምን ረታ!" የሚል ርእስ ያለው፡ በአሁኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ የደረሰውንና እየደረሰ ያለውን ኹኔታ፡ በትንቢት መልክ አስቀምጦ የተገኘው መጽሓፌ፡ ሊጠቀሱ ይቻላል።

## ስለመጪው መከራ የተናገረው መጽሓፍ፡ በራሱ የደረሰበት መከራ!

በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ ሊመጣ ስላለው መከራ የተናገረው ይኸው፡ "ምናሴ! የመከራዬ ደስታ፡ ዓለምን ረታ!" የሚል ርእስ ያለው፡ መጽሓፌ፡ ራሱ የደረሰበትን መከራ፡ እስቲ፡ ጥቂት ላውጋችሁ! ይኸውም፡ ገና በትምህርት ቤት ሣለሁ፡ በ፲፰ ዓመቴ የደረስኩትን ይህን መጽሓፍ፡ ለኅትመት ለማብቃት ያደረግኹትንና ከዚያ በኋላ የኾነውን ኹሉ የሚመለከት ነው።

## የዓለሙ መፋረጃ!

በዚያ የልጅነትና የተማሪነት ዕድሜዬ: ገንዘብ ስላልነበረኝ: እንደድርሰቱ ኹሉ: ማንም ሳይነግረኝና ማንንም ሳላማክር: እግዚአብሔር ብቻ ባሳሰበኝና በመራኝ: "ያሳትሙልኝ እንደኾነ: እስቲ ለጃንሆይ ላመልከት!" ብዬ: አጼ ኃይለ ሥላሴን ለመለመን: በየዕለቱ: ከትምህርት ገበታ በምለቀቅበት ጊዜ: ከምማርበት: ከዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተነሥቼ: ሮጬ: በቀድሞው: የገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ግቢ (በዛሬው: የአዲስ አበባ መካነ አእምሮ University) ውስጥ ወደሚገኘው የእልፍኝ አስከልካይ ጽሕፈት ቤት: ለደጅ ጥናት እየተመላለስኩ ከቆየሁ በኋላ: ተራ ደርሶኝ: ከግርማዊነታቸው ፊት ቀረብኩ::

እዚያም: ማመልከቻዬ ባጭር ቃል ከተገለጸ በኋላ: "በቅድሚያ ድርሰቱ: ተመርምሮ ይቅረብ!" ተብሎ ታዘዘ! ትእዛዙም: መርማሪው አካል ወደሚገኝበት: ወደማስታወቂያ ምልክና (Ministere) እንዲተላለፍልኝ ለማስታወስ: እንደተለመደው: ወደጽሕፈት ምልክና: ጥቂት እንደተመላለስኩ: ማዘዣው: ለባለአድራሻው መተላለፉ ተነገረኝና ደጅ ጥናቴን ወደመርማሪዎቹ መልሼ: እነርሱን ደግሞ: በልጅነት ችኩልነቴ: እየተመላለስኩ: እወተውት ጀመር:: በዚህ መልክ: ወራትን አሳልፌ: በመጨረሻ: የእነርሱ ምርመራ አብቅቶ: ድርሰቱን ከሚደግፍ አስተያየት ጋር: የመጽሐፉ ረቂቅ: ምርመራውን ወደዘዘው መሥሪያ ቤት የተመለሰ መኾኑ ተገለጸልኝ: ደጅ ጥናቴን: በዚያው በእልፍኝ አስከልካይ በኩል ቀጠልኩ:: ተስፋ ባለመቁረጥ: ብዙ ከደከምኩ በኋላ: ከመጽሐፌ ጋር ለኹለተኛ ጊዜ ከጃንሆይ ፊት ቀረብኩና: በኹለት ሺህ ብዛት: "በመንግሥት ኪሣራ ይታተምለት!" ተብሎ ታዘዘልኝ:: እኔም ደስ ብሎኝ: እጅ ነሥቼ ወጣሁ::

ፍላጎቴ ስለተፈጸመልኝ: ከዚያ በኋላ ያደረግሁት ድካም እጅግም አልታወቀኝም:: የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት: መጽሐፉን: በኹለት ሺህ ብዛት እንዲያትም: ከጽሕፈት ምልክና ትእዛዙ ሲተላለፍለት፥ የገንዘብ ምልክና ደግሞ: ገንዘቡን እንዲከፍል: የትእዛዙ ግልባጭ እንዲደርሰው ተደረገ:: የገንዘብ ምልክናም: የትእዛዙ ግልባጭ እንደደረሰው: በትእዛዙ መሠረት ይከፍለው ዘንድ: የማተሚያው ዋጋ ምን ያህል እንደኾነ: እንዲያስታውቀው: ለብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት: ደብዳቤ ጻፈለት:: ማተሚያ ቤቱም: ግምቱ: አምስት ሺህ ብር ያህል መኾኑን: ለገንዘብ ምልክና አስቀድሞ ካስታወቀ በኋላ: የድካሙን ዋጋ ለማግኘት: የመጽሐፉን የኅትመት ሥራ ያጣድፍ ጀመር:: እኔም: ከትምህርቴና ከጥናቴ ውጪ የምትተርፈኝን የመዓልት ጊዜ: አብዛኛውን የማሳልፈው: በማተሚያ ቤቱ: ከፊደል ለቃሚዎቹ ጋር ኾነ! ቀን የተለቀመውን ወስጄ: ሌሊት: እርማት ሳደርግ አድርና ለማግሥቱ እየሰጠኋቸው: በዚህ ዓይነት: አዲስ አበባ: ቂርቆስ ቀበሌ ከሚገኘው ከወላጆቼ ቤት ዘወትር እየተመላለስኩ: የመጽሐፉ የኅትመት ሥራ: ከብዙ ወራት በኋላ ተጠናቀቀ!

እኔም: በመጽሐፉ: የውጭና የውስጥ ገበታዎች ላይ: ደመቅ ባሉ ፊደላት: "ይህ መጽሐፍ: በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መልካም ፈቃድና እርዳታ ታተመ" የሚል ቃል እንዲጻፍበት አደረግሁ:: ስለመጽሐፉ መታተም: ከጽሕፈት ምልክና የተላለፈውን: የመጀመሪያውን ትእዛዝ በሚያውቁት ዘንድ: "ይህ ቃል ተገቢ ነው" እንደሚሉ ጥርጥር የለውም::

ማተሚያ ቤቱ፡ ሥራው እንደተጠናቀቀለት፡ ወዲያው፡ ቀደም ብሎ፡ ከጽሕፈት ምልክናና በዚያ መነሻነት፡ ከገንዘብ ምልክና በደረሰው ጥያቄ መሠረት፡ መጽሐፉን ያተመበትን ዋጋ ይከፍለው ዘንድ፡ ቀደም ብሎ ያስታወቀውን ልኩን ጠቅሶ ጻፈለት። ገንዘቡን ለመረከብ የሚጠባበቀው ማተሚያ ቤት ግን፡ የደረሰው ምላሽ፡ ይህ አልነበረም! ፈጽሞ ያልጠበቀው ሌላ ኾነ! እርሱም፡ "ከምን የወጪ አርእስት እንደምከፍልህ እንደታዘዘ አሳውቀኝ" የሚል ነበር። በዚህ፡ የመጻጻፍ ውዝግብ ተጀመረ! ማተሚያ ቤቱ፡ "እኔ የታዘዝኩትን ሥራ ሠርቻለሁ፤ ገንዘቡ፡ ከየት እንደሚከፈል የማወቁ ወይም የመጠየቁ ተግባር ያንተ ነው" የሚል ተገቢ መልስ ሲሰጥ፡ የገንዘብ ምልክናው ደግሞ መልሶ፡ "ገንዘብህን ማግኘት ከፈለግህ፡ በጻፍኩልህ መሠረት፡ ራስህ ጠይቀህ አስታውቀኝ፥ ወይም እንዲያስታውቁኝ አድርግ እንጂ፡ በእኔ በኩል፡ ከዚህ አልፌ የማደርገው፡ ምንም ነገር የለም" በሚል መልክ ቁርጥ የኾነውን መልስ ሰጠው። ማተሚያ ቤቱ፡ በዚህ አዝኖ፡ በቃልና በጽሑፍ ከቀጠለው ውዝግብ በኋላ፡ ሌላ አማራጭ መንገድ በማጣቱ፡ ግድ ኾኖበት፡ አቤቱታውን ወደጽሕፈት ምልክና አቀረበ።

ይህ ውዝግብ፡ አሁን፡ ከወራት ወደዓመታት ተሸጋገረ። ጉዳዩ፡ እኔንም ስለሚመለከት፡ በያግጣጫው እከታተለው ነበርና፡ "ውዝግቡን ሊወስነው የሚችለው፡ ትእዛዙን የሰጠው ግርማዊነታቸው ብቻ ነው" በሚል እምነት፡ ችግሩን ገልጬ፡ እንደገና በእልፍኝ አስከልካይ በኩል አቤቱታዬን በጽሑፍ አሰማሁ። ከብዙ ደጅ ጥናት በኋላ፡ ከየሚመለከታቸው ወገኖች፡ ማለትም፡ ከማተሚያ ቤቱም ኾነ፡ ከገንዘቡ ምልክና የተሰጡትን አሳቦች በማቀነባበር፡ የጃንሆይን ፊት፡ ለሦስተኛና በዚህ ጉዳይ ለመጨረሻ ጊዜ ለማየት ተራ አግኝቼ ቀረብኩ፤ በዚህ ጊዜ የሰማሁት፡ መልካም ዜናን ሳይኾን፡ ጆሮዬ ያልጠበቀውን፥ ማተሚያ ቤቱንም ያስደነገጠ፡ አሳዛኝ ውሳኔ ነበር፤ ይኸውም፡ "ደራሲው፡ መጽሐፉን ሸጦ ይከፈል!" የሚል ነበር፤ በልጅነት ትካዜ እንደተዋጥኩ፡ ከዚያ ተመለስኩ።

ማተሚያ ቤቱ፡ ጨርሶ ያልጠበቀውና የበለጠ ያሳዘነው ይህ ትእዛዝ፡ ከጽሕፈት ምልክና፡ በደብዳቤ ላይ ሠፍሮ ሲደርሰው፡ ለመቀበል ስለከበደው፡ መጽሐፉን ያተመው፡ "የማተሚያውን ዋጋ፡ 'የገንዘቡ ምልክና፡ በቀጥታ ከመንግሥት ግምጃ ቤት ይከፍልሃል!' ስለተባልኩና፡ ይህም ውለታ መጀመሪያውኑ፡ የግርማዊ ጃንሆይ ቃል ነው ተብሎ ከጽሕፈት ምልክና በተጻፈልኝ ደብዳቤ ስለተረጋገጠልኝ ነው እንጂ፡ ይህ የአሁኑ ትእዛዝ፡ ቀደም ብሎ ደርሶኝ ቢኾን ኖሮ፡ መጽሐፉን አላትምም ነበር፤ ምክንያቱም፡ መጽሐፉ ይሸጥ አይሸጥ እኔ የት አውቃለሁ፤ ከተሸጠ እንኳ መልካም! ካልተሸጠ ግን፡ ከሥሬ መቅረቴ አይደለም ወይ? በዚህ መልክ ደግሞ፡ የማተሚያ ቤቱ ሥራ እንዴት ሊካሄድ ይችላል? ስለዚህ፡ በመጀመሪያው ትእዛዝ መሠረት፡ የገንዘቡ ምልክና፡ የሠራሁበትን የድካሜን ዋጋ እንዲከፍለኝ እንደገና ይታዘዝልኝ" በሚል መንፈስ፡ የአቤቱታ መልሱን ለጽሕፈት ምልክና ላከ።

እኔም እንደፈረደብኝ፡ የተለመደውን ደጅ ጥናቴን፡ በትእግሥት ቀጥዬ፡ የተገኘው መልስ፡ ማተሚያ ቤቱ፡ ባለፈው ከደረሰው፡ እምብዛም የተለየ ስላልነበረ፡ አሁንም፡ እኔን ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ ማተሚያ ቤቱን ያሳዘነ ኾነ! ቃሉም፡ ባጭሩ፡ "ደራሲው፡ ዋስ ጠርቶ፡ መጽሐፉን ይረከብና፡ ሸጦ ይከፈል!" የሚል ነበር።

## የዓለሙ መፋረጃ!

እኔም፡ የአቤቱታዬን አገጣጫ፡ ወደማተሚያ ቤቱ መልሼ፡ "እንግዲህ፡ ይህን ትእዛዝ ተከትለን ብንፈጽም ይሻላል!" ብዬ ለኃላፊዎቹ ባመለከት፡ እነርሱ፡ በዚያው፡ በቀደመው አቋማቸው በመጽናት፡ "በጉዳዩ፡ እኛ ተነጋግረን፡ መልስ እንሰጥበታለን እንጂ፡ ይህንኛውንም ትእዛዝ ቢኾን፡ ለመቀበል ያዳግተናል! አንተ፡ ውጤቱን፡ አልፎ አልፎ እየተመላለስክ ጠይቅ!" ስላሉኝ፡ ለዓመታት ታሽጎ የተቀመጠውን መጽሓፌን፡ በተቀመጠበት ዕቃ ቤት ትቼ፡ ወደሌላ ተግባሬ ተመለስኩ።

እነርሱም፡ ይህን ብለው፡ በኀዘኔታ መንፈስ፡ በሚያሰናብቱኝ ጊዜ፡ ያ፡ በመጀመሪያ፡ በአንደበታቸው ደግፈውት የነበረው፡ በመጽሓፉ የውጭና የውስጥ ገበታ ላይ፡ በጉልህ ፊደላት የታተመው፡ "ይህ መጽሓፍ፡ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መልካም ፈቃድና እርዳታ ታተመ" የሚለውን ቃል፡ አሁን ደግሞ፡ በየልቦናቸው፡ "ይህ ልጅ፡ ይህን ቃል፡ ምን ሊያደርገው ይኾን? አይሠርዘው፥ አይሠረዝ! አይፍቀው፥ አይፋቅ! አይለውጠው፥ አይለወጥ!" ሳይሉ እንዳልቀሩ ገመትሁ።

ይህ በኾነበት ጊዜ፡ እኔ ከትምህርት ቤት ወጥቼ፡ ወደሥራው ዓለም በመሠማራት፡ በትርጉምና ድርሰት ሙያዬ እንዳገለግል በተፈለግሁበት፡ በማስታወቂያ ምልክና ውስጥ ተቀጥሬ መሥራት ጀምሬ ስለነበር፡ በድርሰት ሙያና በባለሙያዎቹ ደራስያን ላይ ያለው፡ ዝርዝርና አጠቃላይ ችግር፡ እጅግ የጸና መኾኑን፡ በራሴም ላይ በደረሰው ስለተረዳሁት፡ ገና በዚያ የወጣት ዕድሜዬ፡ በቅርብ የማውቃቸውን፡ በተለይም፡ አቶ ጌታቸው አወቀ ከተባለው ጋዜጠኛ ጋር በመመካከር፡ ሌሎቹን ጋዜጠኞችና ደራሲዎች፥ እንዲሁም፡ የድርሰት ፍቅርና አግባብ ያላቸውን ሰዎች፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ በማሰባሰብ፡ "የኢትዮጵያ ድርሰት ማኅበር" የተባለውን ድርጅት፡ በ፲፱፻፶፱ ዓ. ም. አቋቋምን። በ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. ሥራውን፡ ለአቶ መንግሥቱ ለማ አስረክቤ፡ በአኵስም ጽዮን ንቡረ እድነት፡ ወደአኵስም እስከሄድኩበት ቀን ድረስ፡ የማኅበሩ ዋና ጸሓፊ በመኾን፡ የድርሻዬን ግዳጅ ፈጽሜአለሁ።

በአዲስ አበባ፡ የደቡብ ክፍል ሕዝብ ምርጫ፡ በቤተ ሕዝቡ ውስጥ፡ ለሦስት ዓመታት ካገለገልኩ በኋላ፡ የሕግ መምሪያ ብሔራዊ ምክር ቤት አባልነቴን አስረክቤ፡ ለቤተ ክህነቱና ለቤተ ምልክናው አገልግሎት፡ በአኵስም ጽዮን ንቡረ እድነት፡ ወደአኵስም እንድኼድ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ሹመት ታዝዤ፡ ይህንኑ ግዳጄን ለመፈጸም፡ ከአዲስ አበባ በተነሣሁበት ጊዜ፡ "ምናሴ፡ የመከራዬ ደስታ፥ ዓለምን ረታ!" የተባለውንና ከላይ በጠቀስኩት ውዝግብ ምክንያት፡ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡ እነሆ፡ በዚያን ጊዜ፡ ለአሥር ዓመታት፡ በዕቃ ቤት ታሽጎ የተቀመጠውን፡ መከረኛ መጽሓፍ አልዘነጋሁትም።

ከአሥር ዓመታት በኋላ፡ ለአኵሱም ጽዮን ንቡረ እድነት ኾነ፡ ቀደም ብለው ለነበሩት፡ የተለያዩ አገልግሎቶች፡ በየጊዜው ለሹመትና ለሥራ እየተጠራሁ፡ ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ፊት ስቀርብ፡ የዚህኑ መጽሓፌን ጉዳይ ሳነሣባቸውና ጉዳዩን በዝርዝር አስረድቼ፡ ትእዛዙ ተሻሽሎ፡ የመጽሓፉ ዋጋ፡ ለማተሚያ ቤቱ እንዲከፈል ለማድረግ፡ ፈቃዳቸውን ሳገኝ እንደምችል አውቅ ነበር።

ነገር ግን፡ "እውነተኛው ደስታ ተሰምቶኝ 'እግዚአብሔር ይስጥልኝ!' ብዬ እጅ ልነሣ እችል የነበረው፡ ይህ ቸርነት፡ ለዚህ፡ ዛሬ ለሹመትና ለሥልጣን ለበቃው ጉልማሳ ደራሲ ሳይኾን፡ ለዚያ፡ ተስፋ ባለመቍረጥ፡ በደጅ ጥናት ሲዋትት ለነበረው፡ ታናሽ የተማሪ ደራሲ ተደርጎ ቢኾን ነበር!" ከሚለው የእምነት አስተሳሰቤ የተነሣ፡ ይህን ማድረግ ትቼ፡ በቀጥታ ወደማተሚያ ቤቱ ኃላፊዎች ኼድኩ::

ወደእኰሱም የመኼድ ግዴታ የመጣብኝ መኾኑን፡ እነርሱም ያወቁት ስለኾነ፡ ይህንኑ በማስረዳት፡ መጽሐፉን፡ በመጨረሻው ትእዛዝ መሠረት፡ ዋስ ጠርቼ ለመውሰድና ተሽጦ፡ የእነርሱ የማተሚያ ዋጋ፡ በቅድሚያ ለእነርሱ እንዲከፈል አደርግ ዘንድ፡ ፈቃዳቸውን ጠየቅኋቸው:: እነርሱም፡ በዚሁ ስለተስማሙልኝ፡ ዋሴን ጠርቼ፡ መጽሐፉንም፡ ሌላ ሳይኾን፡ "ብርሃን መጽሐፍ መደብር" የተባለው፡ የራሳቸው የሽያጭ ዘርፍ፡ መጽሐፉን፡ ራሱ፡ በቀጥታ፡ ከማተሚያ ቤቱ እየወሰደና እየሸጠ፡ የማሳተሚያው ዋጋ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ፡ የራሱን፡ የድካም ድርሻ እየቀነሰ፡ የቀረውን በሙሉ፡ ለማተሚያ ቤቱ እንዲከፍል፡ የጽሑፍ ስምምነት አድርገን፡ መጽሐፉ፡ ከአሥር ዓመት እሥራቱ ተፈትቶ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ ነጻነቱን አገኘ!

ይኹን እንጂ፡ እንደአርእስቱ፡ መከረኛ የኾነው፡ ይኸው መጽሐፍ፡ ነጻ በወጣ በአምስት ዓመቱ፡ ደራሲው ደግሞ በፋንታው፡ በደርግ ሥልጣን፡ ወደእሥር ቤት ገባ:: ያም ወቅት፡ ሕግና ሥርዓት፡ በክህደትና በዓመፅ የተወገዱበት ስለነበረ፡ "ደራሲው ከታሠረ፡ ስምምነቱም ሊሻር ይገባዋል" በሚል ምክንያት ይመስላል፡ ስለመጽሐፉ፡ ከማተሚያ ቤቱና ከመጽሐፍ መደብሩ ጋር ያደረግነውን ስምምነት፡ በመሻር፡ በእኔና በዋሴ ላይ፡ በፍርድ ቤት ክስ ተመሥርቶ፡ ሳይከፈል የቀረውን፡ የማተሚያ ዋጋ እንድከፍል ተደረገ!

እስካሁን የደረሰውንና አሁንም እየደረሰ ያለውን ኹሉ፡ ዛሬ፡ ወደኋላ መለስ ብዬ ስመለከተው፡ በዚያ መጽሐፍ ላይ፡ ያ ኹሉ በደልና ጥቃት መድረሱ ሊያስገርም፡ ወይም ሊያሳዝን የማይችል መኾኑን፥ የደረሰውም ያለምክንያት እንዳልነበረ ተረዳሁት! ይኸውም፡ ያ ድርሰት፡ ለዚያን ዘመን የማይኾን፥ ከጊዜው አመራር ጋር የማይኼድና የነበረውን የአገዛዝ ዓላማ የሚፃረር ኾኖ በመገኘቱ መኾኑን የሚያረጋግጠው እውነታ ነው::

ያም፡ ለአሥር ዓመታት ተዘግቶበት ኖሮ የተለቀቀው መጽሐፍ፡ ኋላ፡ ደራሲው እኔ፡ ለሃያ አንድ ዓመታት በእሥር፥ በግዞትና በስደት፡ በአገርና በውጭ ቆይቼ፡ በ፲፱፻፹፯ ዓ. ም. ወደአዲስ አበባ ተመልሼ ሣለሁ፡ አንድ ቀን፡ በግል ተሽከርካሪ ሠረገላ ውስጥ ተቀምጬ፡ ነጂውን እየጠበቅሁ ሣለሁ፡ አንድ ተዘዋዋሪ መጽሐፍ ሻጭ፡ መስተዋቱ ዝቅ ብሎ በነበረው፡ በመስኮቱ፡ ራሱን ብቅ አድርጎ፡ ያሉትን መጻሕፍት እያስተዋወቀ ሲያሳየኝ፡ "ምናሴ" የሚለውን መጽሐፍ አውጥቶ፡ "እንኩ! ይህን ደግሞ ይዩት! ፡የመከራዬ ደስታ፥ ዓለምን ረታ!፡ የሚል ንዑስ አርእስት አለው! ቄስ ኤርምያስ ከበደ፡ በ፲፱፻፵፰ ዓ. ም. የደረሱት፡ የቆየ መጽሐፍ ነው!" ብሎ አስተዋወቀኝ::

እኔም፡ ለሃያ ሰባት ዓመታት በመከራ ተለይቼው ከኖርሁት፡ መከረኛው መጽሐፌ ጋር፡ እንደገና ለመተያየትና ለመገናኘት በመብቃቴ፡ እጅግ ደስ ብሎኝ፡ ይህን ያደረገ እግዚአብሔርን አመሰገንሁት! ምስጋናዬ፡ ለዚህ መለኮታዊ ቸርነት ብቻ አልነበረም፤ ነገር ግን፡ መጽሐፉ፡ ተፈርዶበት ከነበረው እሥራትና ተፅዕኖ ነጻ ኾኖ፡ በዚህ መልክ ሳይቀር፡ የመጽሐፉ መልእክት፡ ለአንባቢው ሕዝብ እንዲዳረስ በማድረጉ ጭምር እንጂ!

## ለኃላፊነት አገልግሎቶች መጠራት።

በእኔ በኩል፡ በዓቅሜ፡ ከላይ የገለጽኋቸውን የመሰሉ ተግባሮችን በማካኼድ፡ የኢትዮጵያዊነት ድርሻዬን ከማበርከት በቀር፡ ሌላ የተለየ፡ አንዳችም ዓይነት ፍላጎት ሳይኖረኝ፥ በቅድሚያም እንዳውቅ የተደረገበት፡ አንዳችም ፍንጭ ሳይደርሰኝ፡ በመጨረሻ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው፡ በአገሬ በኢትዮጵያ፡ በሦስቱም ቤቶች የሥራ ዘርፎች ውስጥ፡ በተከታታይ፡ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ እየተመደብኩ እንዳገለግል የተጠራሁ ኾኜ፡ ራሴን አገኘሁት፤ ያም ጊዜ፡ "አብዮት" የተባለው፡ የተጠበቀውና የተፈራው፡ የክህደት ዓመፅ ሊፈነዳ የተቃረበበት፡ ያለቀው ወቅት ነበር።

ከብዙዎች አዛውንት እንደሰማሁት፡ አንድ ኢትዮጵያዊ፡ በእኔ አናሳ ዕድሜ፡ ለእነዚያ የአገልግሎት ቦታዎች ሲመረጥና ሲሾም፡ ምናልባት፡ ያ፡ በአገራችን ዜና መዋዕል፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ደርሶ የታየ ድርጊት ሳይኾን የሚቀር አይመስለኝም። ከዚህ ጋር፡ ቀደም ብዬ ከተቀበልሁት ሥልጣነ ክህነት በቀር፡ እኔን፡ ለእነዚያ፡ ለቅዱሱ ኪዳን፡ የክብር ሹመቶች ሊያበቁ የሚችሉት መሥፈሪያዎች፡ አንዳቸውም፡ በእኔ ዘንድ እንዳልነበሩ እመሰክራለሁ። ያን፡ አጠቃላይ ኹኔታ፡ በበኩሌ የተመለከትሁት፡ ራሴን፡ ለእግዚአብሔር አገልግሎት እንደተጠራሁ እቆጥር ዘንድ፡ ለእኔ ማስረጃ ኾኖ እንደተላከልኝ ምልክት አድርጌ ስለነበር፡ የሹመት ጥሪዎቹን ኹሉ፡ ያለአንዳች ጥያቄ፡ በሙሉ ልብና በጋለ ስሜት ተቀብዬ አገልግሎቴን ቀጠልሁ።

ምንም እንኳ አጋጣሚው፡ ለእኔ፡ አመቺና ተስማሚ ኾኖ ባይገኝ፡ ሊደርስ ካለው ታላቅ የጥፋት ማዕበል፡ ምናልባት በተአምር ተርፎ፡ በሕይወት የመኖሩን ጸጋ የሚታደል ባይታጣ፡ ለዚያ ለሚቀጥለው ትውልድ የሚተላለፉ፡ አንዳንድ የቅዱሱን ኪዳን ቅርሶች ለማዳንና ለማቆየት በሚደረገው የትድግና ትግል ውስጥ፡ እኔም የበኩሌን ድርሻ፡ ባለኝ የመጨረሻ ኃይልና በተቻኮለ ይዘት ማበርከትን ተያያዝኩት።

የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ካቋቋማቸው፡ ከዝቅተኛው መዋዕለ ሕፃናት ጀምረው፡ እስከከፍተኛው መካነ አእምሮ ድረስ ባሉት የትምህርት ተቋሞች፡ እየተማሩና እየሠለጠኑ የወጡት ተማሪዎች፡ ወላጆቻቸውን የማያከብሩ፥ መምህሮቻቸውን የማይከተሉ፥ አለቆቻቸውን የማይፈሩ፥ የአገሪቱን ርእሰ ብሔር፡ አጼውን ሳይቀር የሚዳፈሩ ኾነው በመገኘታቸው፡ ማናቸውንም የዓመፅ እንቅስቃሴ ለመቋቋም እንደማይቻለው፡ ያ መንግሥት፡ የጥፋቱ ማዕበል ከመድረሱ ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ ሲያረጋግጥ፡ የሚኾን መስሎት፡ ቀድሞ ሲለመን፡ "አሻፈረኝ!" ብሎ ንቆት የነበረው፡ ኢትዮጵያዊው ሥርዓተ ትምህርት እንዲዘጋጅለት ፈቃደኛ ኾኖ ሥራው፡ በቤተ ክህነት ሰብሳቢነት ተጀመረ።

ነገር ግን፡ ያ ወቅት፡ ለካ፡ "ጅብ ከኼደ ውሻ ጮኸ!" የተባለውን የመሰለ፡ ዕድሉ ያመለጠበትና ነገሩ ኹሉ ያበቃበት ጊዜ ኖርዋል! መለኮታዊው የቅጣት ፍርድ፡ ለአስፈጻሚው የኃይል ዘርፍ ተላልፎ፡ በሥራ ላይ የመዋሉ ሂደት ተጀምሮ ኖርዋል! አገሪቱንና ሕዝቡን፡ ከዚያ ፍርድ ታድጎ ሊያተርፍ የሚችል፡ ከቶ፡ ምንም ዓይነት መንገድ አልነበረም። ፍርዱም፡ ከላይ ተብራርቶ እንደተገለጸው፥ እስከዛሬ እንደታየውና ዛሬም፡ በገሃድ ሲካሄድ እንደሚታየው፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ እስከዕድሜያቸው መጨረሻ ድረስ፡ በዘመናቸው ደክመው የሠሩት ኹሉ፡ እራሳቸውና የእርሳቸው የኾኑትም ሳይቀሩ፡ ኹሉም፡ ጨርሶ እንዲፈራርስና እንዲወድም ማድረግ ነበር!

ከቅዱሱ ኪዳን የምሕረት ጸጋ የተገኘ፡ ልዩ የኾነ፡ አንድ የትድግና ቸርነት ቢኖር፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ለኾነችው ኢትዮጵያ፡ ከሦስቱ የአገልግሎት ዘርፎች፡ አንዱ በኾነው፡ በቤተ ክህነቱ በኩል፡ እንዲቋቋም የተደረገው፡ የሰበካ ጉባዔ የተባለው የድርጅት መዋቅር ነበር። ያም ወራት፡ ዘለዓለማዊው ዳኛ፡ በቀጠረው መሠረት፡ የቅጣቱን ፍርድ ለመፈጸም፡ ርኅራኄ የሌለውን ሰይፍ የታጠቀው፡ ያ፡ ሥር ነቀል ዓመፅ፡ የሚመጣበት ቀን ከመድረሱ በፊት፡ ጥቂት ቀደም ያለው ጊዜ ነበር። በዚያን ሰዓት፡ ልክ፡ አንድ አስከፊ አደጋ ሊደርስ እንደተቃረበ ታውቆና ተጠብቆ የተከናወነ በሚመስል ይዞታ፡ ይህ የሰበካ ጉባዔ፡ በጥድፊያ ተመሥርቶ፡ አውታሩ፡ በጥቂት ወራት ጊዜ ውስጥ፡ በመላዋ የቅዱሱ ኪዳን ምድር ላይ ተዘረጋ!

ኢትዮጵያን በፍጹም ሊደመስስ መጥቶ ከነበረው የጥፋት ማዕበል ሊያተርፋት የቻለውን፡ የሰበካ ጉባዔ በማቋቋም ረገድ፡ መለኮታዊ ቸርነቱ የተገለጠባትን፡ ያችን የትድግና ተልእኮ፡ ከቀሩት የሥራ ባልደረቦቼ ጋር፡ በተግባር ላይ አውዬ፡ ለፍሬ እንድትበቃ አደርግለት ዘንድ፡ በዚያች ቀውጢ ወራት፡ በቤተ ክህነቱ ዘርፍ፡ ዋና አገልጋዩ እኾን ዘንድ፡ እኔን፡ አንድ ትሑት ኢትዮጵያዊ፡ ለዚያ፡ ለእርሱ የአገልግሎት መሣሪያነት ስለመረጠኝና ትእዛዙን ስላስፈጸመኝ፡ ጌታዬን ኢየሱስ ክርስቶስን፡ ከነእናቱ አመሰግነዋለሁ!

## መፍትሔው፡ ንስሓ ነበር።

የክህደት ዓመፃችን ያስከተለውን የቁጣ ቅጣትና ለንስሓ "እምቢ!" ብሎ፡ በክፋቱ የጸናው ልባችን ያስገኘውን መራራ ፍሬ፥ ባጠቃላይም፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ ለፈጸምነው በደል፡ እየከፈልን ያለነውን ዋጋ፡ እርስዎ (አቶ ናፍታሊ) አይመለከቱምን?

የቃል ኪዳን አምላካችን፡ አጼ ኃይለ ሥላሴና እርሳቸው ያፈሩት ትውልድ፡ ለራሳቸው ደኅንነት ሲሉ፡ ከስሕተት መንገዳቸው ተጸጽተው በመመለስ፡ በቅዱሱ ኪዳን የገቡትን ሥርዓት ጠብቀው ይኖሩ ዘንድ፡ እስከመጨረሻው ድረስ እየተማጸነ መክሩዋቸው ነበር። እነርሱ ግን፡ በአሳብ አንድ ኾነው፥ በግብርም ተባብረው፡ "አሻፈረን!" አሉት፤ አመፁበትም። በዚህም፡ *"ኵሉ ዐረየ፥ ወኅቡረ ዐለወ! አልቦ ዘይገብራ ለሠናይት፥ አልቦ ወኢአሐዱ!"* ማለትም፡ *"ኹሉም በአሳብ አንድ ኾነ! በኅብረትም ዓመፀ! መልካምን ነገረ የሚያደርግ አንድም የለም! አንድ እንኳ!"* የሚለው የነቢዩ ቃል ተፈጸመ።[፻፲፮]

የዓለሙ መፋረጃ!

ቀደም ብሎ እንደተመለከተው: በደብዳቤዎ መዝጊያ ላይ: በአንክሮ መልክ ለሠነዘሩት መጠይቃዊ አስተያየት: የምሰጥዎ መልስ: ይኸውልዎ! እርሱም: "የለም! እርስዎ እንደጠየቁት: በአጼ ኃይለ ሥላሴ ላይ 'ያመፁት' እና 'እርሳቸው የተናገሩዋቸውን የጥበብ ቃላት ሰምተው ሊፈጽሙ' ይገባቸው የነበሩት: ኢትዮጵያውያን ሳይኾኑ: ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉትን: ቅዱሱን ቃል ኪዳን: በክህደት ያፈረሱትና በእርሱ: በፈጣሪያቸው ላይ ያመፁት: ራሳቸው አጼ ኃይለ ሥላሴና እርሳቸው ያፈሩት ትውልድ ናቸው" የሚል ነው:: ይህንንም: ትውልዱ: ከዚህ ግብሩ: በንስሓ ካለመመለሱ የተነሣ: ወይም እስካልተመለሰ ድረስ: ይኸው: የደረሰበትና ለወደፊቱም እንዲቀጥል: ተዳርጎበት የሚገኝበት: የመጨረሻ ውድቀቱ ይመሰክራል! አጼ ኃይለ ሥላሴ ግን: በደርግ እሥር ላይ ሣሉ: ከማረፋቸው በፊት: እግዚአብሔር በሰጣቸው የአንድ ዓመት የንስሓ ዕድሜ ውስጥ: እርሳቸውም: ከፈጣሪያቸው ይቅርታን እንደጠየቁ፥ አምላካቸውም በቃል ኪዳኑ: ይቅር እንዳላቸው: እንተማመናለን::

እውነቱና ትክክሉ ይህ ኾኖ ሣለ፥ ይልቁንም: ጥልቅ በኾነ ጸጸት: ንስሓ ልንገባበት የሚገባ በደል: ከፊታችን ቆሞ እየመሰከረብን እያለ: ከቶ አንዳችም የደረሰ ነገር እንደሌለ በማስመሰል: ያ: አጼ ኃይለ ሥላሴና ትውልዳቸው: በአምላካችን በእግዚአብሔር ላይ ሲያካኼዱ የቆዩት ዓመፅ: በበለጠ እንዲቀጥል ሊያበረታታ ስለሚቃጣው የፈጠራ አስተሳሰብዎ: ያውም ያውም በጽሑፍ አሥፍረው: ዛሬ: እርስዎ: ሊያስረዱኝ ተነሡ! ያውም: ለእኔ: ከዚያ ኹሉ: በግል ከደረሰብኝ: አሠቃቂ መከራ: በቅዱሱ ኪዳን ረድዔትና በረከት: በሕይወት ተርፌ: ከዚህ ጊዜ ለመድረስ ለበቃሁት ሰው:: ሙከራዎ: በዚህ ብቻ ሳይወሰን: እንድቀበለውም: ሊያሳምኑኝ እስከመሞከር ደረሱ! ይገርማል! በዚህ ድርጊትዎ: ለእርስዎና በአስተሳሰብዎ የሚተባበሩዎ ካሉ: ለእነርሱ ጭምር አዝንላችኋለሁ!

አሁንም ቢኾን: ተስፋ አልቆርጥም፤ ይልቁንም: *"ነገር ኹሉ የሚኾነው ለበጎ ነው"* በሚለው እምነት በመጽናት: ጠፍቶ ስለተገኘው ባካና ልጅ: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰጠው ምሳሌ እንደተናገረው: እኛም: ንስሓ ገብተን: ወደእቅፉ ልንመለስ የምንችልበትን ዕድል: ወሰን በሌለው ቸርነቱ አስፍቶ ስላበረከተልን: ለእግዚአብሔር የማቀርበውን ምስጋና እቀጥላለሁ እንጂ::

ስለዚህ: ከአሳዛኙ የቁጣ ማዕበል ተርፈው: በሕይወት ለመቆየት የበቁትን: የአጼ ኃይለ ሥላሴን ቤተሰብ ጨምሮ: ኹላችን ስለሠራነው ኃጢአት ተጸጽተን: በንስሓ: ይቅርታን: ከፈጣሪያችን እንጠይቅ ዘንድ: እያንዳንዳችንን እለምናለሁ:: ከዚህ አስቀድሜ ያልኩትን: እንደገና ልድገመው! አዎን፥ እስካሁን የተቀበልነው ፈተናና መከራ: ከሚበቃ በላይ ኾኖብናል! በግል፥ በቤተሰብና በአገር ደረጃ: እየደረሰብን ያለው የፍዳ ቅጣት: የግትረኛነትና የእምቢተኛነት ተፈጥሮአችንን ወደተሻለ ባሕርይ ሊለውጠው የሚችል፥ እኛንም: ከላይ በተጠቀሰው ምሳሌው: ስለንስሓ ወዳስተማረን፥ የኃጢአትና የክፋት ሥራዎቻችንን ዘወትር ይቅር ወደሚለንና ምንጊዜም በቃል ኪዳኑ ወደታመነው: የሰማዩ አባታችን የፍቅር እቅፍ እንድንመለስ የሚረዳን መኾን አለበት:: III

## ከሰው ብልህነት ይልቅ፡ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይበልጣል፡፡

ከቅዱሱ ኪዳን አምላካችን ይልቅ "እኛ የበለጠ እናውቃለን፤ እንጠበባለን" የሚል እምነት ያለን መስለን ወደምንታይበት የአስተሳሰብ ዝንባሌ፡ ተታልለን እንዳንማረክ እንጠንቀቅ! በአእምሮአችን ተቀርፆ የሚገፋፋንን፥ ሰው ሠራሽ የኾነውንና የሙስና ብልሹነትን የተመላውን፡ ማናቸውንም ዓይነት፡ የሥጋውያን ሥነ መንግሥት ፈሊጥም፡ ከየሕሊናችን እናስወግደው! እኒህን የመሰሉት አዝማሚያዎች፡ የተፃራሪያችን የዲያብሎስ ማጥመጃ ዘዴዎቹ ናቸውና! ስለዚህ፡ ጠፍቶ የተገኘው በደለኛ ልጅ፡ ተጸጽቶ ወደአባቱ እንደተመለሰ፡ እኛም፡ ራሳችንን፡ በንስሓ አዋርደንና ተመልሰን፡ ኹለንተናችንን፡ ለኃያሉ እግዚአብሔር ፈቃድ የበቃን እናድርግ!

የቅዱሱ ኪዳን አምላካችን እውቀት፡ ምሉዕ በኵለሄ (በኹሉ የመላ) ስለኾነ፡ የሚወሰንበት ጽንፍ የሌለው፥ በኹሉ ሥፍራ የመላ ነው፡፡ እርሱ፡ በፍጹም ምሥጢር የተተነፈሰውን ቃል፡ ጠልቆ የማወቅና በድቅድቅ ጨለማ የተፈጸመውን ድርጊት አጉልቶ የማየት ሥልጣን ያለው ብቻ ሳይኾን፡ "ልብ ያሰበውንና ኵላሊት ያመላለሰውን ያውቃል!" እንደሚባለው፡ በአእምሮአችን ውስጥ በረቂቅ የተጻፈውን ጭምር፡ በቀላሉ የማንበብ ችሎታ አለው፡፡ ልናደርግ ያቀድነውን አሳባችንን ሳይቀር፡ አስቀድሞ ያውቀዋል፡፡ ስለዚህ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በምድር ላይ በምናሳልፈው የሕይወት ዘመናችን ኹሉ፡ ከእርሱ ጋር ከሚያስተሣሥረን፡ ከቅዱሱ ኪዳን ክልል ውጭ ለማድረግ የምንሞክረው፡ አንዳችም ነገር ቢኖር፡ ያ ሙከራችን፡ ራሳችንን መልሶ የሚያጠፋን ከመኾኑ በቀር፡ በምንም ዓይነት መንገድ፡ ከቶ ሊሠምር የማይችል፥ ከንቱና ፍሬቢስ ኾኖ የሚቀረው፡ በዚህ ምክንያት መኾኑን ልንገነዘብ ይገባናል፡፡

ያን ያህል የተራቀቀውና የጠለቀው፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ አዋቂነትና ብልህነት እንኳ፡ ከእግዚአብሔር ጥበብ በልጦ ሊገኝ እንዳልቻለ፡ በገዛ ዓይናችን አይተነዋል፤ *"ከሰው ጥበብ ይልቅ፡ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይበልጣል"* የሚለውን የመጽሐፍ ቃል መዘንጋት የለብንም፡፡ ይህን እውነታ ለማረጋገጥ፡ የእኛ፡ የእየራሳችን ሕያው ምስክርነት ይበቃል፡፡ ከቅዱሱ ኪዳን መንፈስ ውጪ መኾኑ የታወቀው፡ ያ ኹሉ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ ምኞት ሳይፈጸምላቸው መቅረቱንም ተመልክተናል፡፡ ይህን እውነታ፡ በበለጠ የሚያጸና፡ አንድ ሌላ፡ የማውቀውን የተጨበጠ ማስረጃ ላቅርብ!

## ኢትዮጵያ፡ እጨጌ ቴዎፍሎስን ስትፋረድ!

እጨጌ ቴዎፍሎስ፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብና በተለይም፡ በግል፡ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ሊፈጽሙት ይገባቸው ከነበረው የቃል ኪዳን ግዴታ በላይ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሥርዓት፡ በፈቃዳቸው ከተቀበሉት የተጠሪነትና የኃላፊነት ሥልጣን የተነሣ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስና ለእናቱ ድንግል ማርያም፡ ሊኖራቸው ስለሚገባው ፍጹም ታማኝነት፡ የማነኛውንም ሰው ማንነት፡ እንደወርቅ አንጥሮ፥ አጥርቶና አግዝፎ ያወጣው፡ ይህ የፈተና እሳት የተንበለበለበት ዘመን እስኪመጣ ድረስ፡ ከእራሴ ጀምሮ "የሚጠራጠራቸው ሰው ይኖራል!" ብዬ አላስብም፡፡

የዓለሙ መፋረጃ!

ነገር ግን፡ እንደሌላው ኹሉ፡ እሳቸው ጭምር፡ ታማኝ ኾነው አለመገኘታቸውን፡ ራሳቸው በፈጸሙት ድርጊት፡ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ምልክናና ቤተ ክህነት ቀርቶ፡ ዓለም በሙሉ፡ በትዝብትና በመደነቅ ተመልክቶታል። ይህን የመሰለውን የክህደት ተግባር፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ ትውልድ ያፈራቸው ሌሎቹ ባለሥልጣኖችና በይበልጥም፡ ራሱ ዓመፀኛው ደርግ፡ በገሃድ ፈጽመው ስለታየ፡ እነርሱ፡ "ሥጋውያን በመኾናቸውና ባለማወቃቸው ነው" በሚል ምክንያት፡ ምናልባት፡ አስተያየት ሊደረግላቸው ይቻል ይኾናል። እርሳቸው፡ አባ ቴዎፍሎስ ግን፡ መንፈሳዊነታቸውን በይፋ የገለጹ መኾናቸው ብቻ ሳይኾን፡ በምንኵስና ቆባቸውም ስላተሙት፡ አድራጎታቸው፡ ሊታመን ያዳገተ፥ እንደእንግዳ ነገር ታይቶ፡ ኹሉንም ግራ የሚያጋባ ኾነ! "ኹሉንም" ስል፡ በግብር፡ እርሳቸውን ከሚመስሏቸው በቀር፡ እውነተኞች ኢትዮጵያውያንንና እውነተኞች ባዕዳንን ተመልካቾች ማለቴ ነው። ምክንያቱም፡ ምንኵስና ማለት ምን እንደኾነ፡ በኹሉ ዘንድ፡ በገሃድ የታወቀ የሕይወት ሥርዓት ሲኾን፡ እርሳቸውም፡ ቃል ኪዳን ገብተው በፈጸሙት፡ በዚህ፡ የምንኵስና ሥርዓት መሠረት፡ ሕይወታቸውን፡ በፈቃዳቸው፡ በሞት ሠውተው፡ ሰውነታቸውን፡ የእግዚአብሔርን እውነት በማሰብ፥ በመናገርና በማድረግ፡ ኹለንተናቸውን፡ የፈጣሪያቸው "የእውነቱ መገለጫ መሣሪያና አገልጋይ አደርጋለሁ!" ብለው፡ ራሳቸውን፡ ለእርሱ መስጠታቸውን፡ በይፋ አረጋግጠው፡ ለቤተ ሕዝቡ ያስታወቁ በመኾናቸው ነው።

ከዚህም በላይ፡ በኢትዮጵያዊነታቸው፡ "እጨጌ" ተብለው፡ ያን ከፍተኛ ሥልጣን፡ በመሐላ ቃልና በጽሑፍ ኪዳን በተቀበሉበት ጊዜ፡ ያ፡ በራሳቸው ላይ የደፉት፡ የተንቈጠቈጠ ዘውድ፥ ያ፡ የተቀመጡበት፡ በቅርጽ ሥራዎች ተሸለመ መንበር፥ ያ፡ የተጎናጸፉት፡ በሙካሽ ጥልፎች የተጌጠ ልብሰ ተክህኖ፥ ያ፡ ያንዠረገገቱት፡ በዕንቍና በከበሩ ድንጋዮች የተሠራ ያንገት ጌጣጌጥ፥ ያ፡ በግራ እጃቸው የተያዘው፡ የብር አርዌ ብርት፥ ያ፡ በቀኝ እጃቸው የጨበጡት የወርቅ መስቀል፡ እነዚህ ኹሉ ትጥቆች፡ የምን ምልክቶች ኾነው የቀረቡ ኖረዋል? ሥጋውያን ገገሮች፡ ለመወደስና ለመፈራት ሲሉ፡ እንደሚጐናጸፉትና እንደሚቀዳጁት "አርዕድ! አንቀጥቅጥ!" እንደሚባለው ልብሰ መንግሥት ኾኖ እንዲያገለግል ኖርዋልን? አይደለም! ታዲያ ለምን ኖርዋል?

እኒያ የአባ ቴዎፍሎስ የሚመት ትጥቆች፡ በኹለት እጆቹ፡ የብረት ችንካሮችን ጨብጦ፡ ደም በለበሰ ዕርቃን ሥጋው፡ የእሾህ አክሊል ዘውዱን ተቀዳጅቶ፡ ሮማውያንና አይሁድ ባዘጋጁለት፡ ዙፋን መስቀሉ ላይ፡ ተጋድሞ፥ ቀኝ ጎኑን፡ በጦር ተወግቶና የመጨረሻው የፋሲካ በግ ኾኖ ታርዶ፡ በመሥዋዕትነትና በቤዛነት የሞተው፡ መሪያቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ያስገኘውን ድል የሚያስታውሱ እኮ ናቸው! መልካሙ እረኛ እሱ፡ "እኔ፡ እንዲህ ኾኜ፡ ከነጣቂው ተኩላና ከአውሬው ዘንዶ ያዳንኳቸውን፡ ጠቦቶቼንና በጎቼን፥ በጠቅላላ መንጎቼን፡ አንተም እንዲህ ኾነህ ጠብቅልኝ!" ብሎ የሰጠውን ጥብቅ አደራ እንደገና በይፋ የሚያረጋግጡ ናቸው እኮ! እነዚያ ትጥቆች፡ ይህን የመሰለውን ታላቅ መልእክት ለማስተላለፍ የሚለበሱ እንጂ፡ ዓለማውያን ተሿሚዎች፥ ወይም፡ የእርሳቸው ተተኪዎች የኾኑት፡ የዛሬዎቹ "እጨጌዎች" ሲያደርጉ እንደሚታዩት፡ በየበዓላቱና ሕዝብ በሚሰበሰብባቸው አደባባዮች ላይ፡ በግርማ ሞገስ ለመታየትና ምድራዊዉን ክብር ለማግኘት፥ ተድላ ደስታውንም ለመፈጸም አይደለም።

በዚህ ረገድ፡ የቤተ ክህነቱ ተጠሪና መሪ እንደመኾናቸው፡ አንድ ዓይነት፡ አሳሳቢና አደገኛ ኹኔታ መምጣቱ ሲከሠት፡ ለቤተ ክህነቱ፥ ለቤተ ሕዝቡና ለቤተ ምልክናው፡ በጊዜው፡ ተገቢውን ትምህርትና እውቀት መስጠት፥ ሲያስፈልግም፡ ምክርና ተግሣፅን ማበርከት፥ "አንሰማም!" ሲሉ፡ ወይም ነጣቂው ተኲላ፡ ከመንጋው መካከል መግባቱን ሲያውቁ፡ ከእርሱ እንዲጠበቁ፡ ማስጠንቀቅ፥ በመጨረሻ፡ "በንስሓ አንመለስም!" ሲሉ ማውገዝ፥ ከተኲላው በኋላ፡ አውሬው ዘንዶ፡ ገፍቶ ከመጣ ደግሞ፡ ከመንጎቻቸው ፊት ኾነው፡ ዘንዶውን፡ እስከሞት ድረስ መቋቋም፡ የመልካም እረኝነት (ጠባቂነት) ተግባራቸውን እንደፈጸሙ የሚያስቈጥራቸው፡ ተተኪ ወይም አማራጭ የሌለው ግዴታቸው ነበር።

እንግዴህ፡ ይህ አቋም፡ ከማናቸውም ካህን፡ ሕጋዊ ኾነ መነኲስ፡ ወይም ጳጳስ ወይም እጨጌ የሚጠበቅ መኾኑ፡ በኹሉም ዘንድ ሊታወቅ ይገባል።

አባ ቴዎፍሎስ፡ ይህን ሥርዓት ሳይጠብቁ፥ ወይም ግዳጃቸውን ሳይፈጽሙ ለምን ቀሩ? በእርሳቸው ዘንድ፡ "እግዚአብሔር የለም! ቢኖርም፡ አያየኝም! ቢያየኝም፡ ምንም አያደርገኝም!" የሚል የስንፍና አስተሳሰብ ነበራቸውን? ይህን ደግሞ፡ እንኳንስ፡ "ይኾናል" ለማለት፡ "ይኾናል" ብሎ መገመቱ እንኳ ይከብዳል፤ ምክንያቱም፡ ከላይ እንደታተተው፡ ማንነታቸው፡ በሚያስተማምን መልክ ተረጋግጦ፡ በይፋ የታወቀ ስለኾነ ነው። ታዲያ፡ ሌላ ምን ምክንያት አለ? ካለስ፡ እርሱ ምንድር ነው? ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚኾነውን ቃል፡ የእርሳቸው ምሥጢረኛ ሰው ካለ፡ እርሱ፡ ሊነግረን ይችል ይኾናል። በእኔ በኩል ግን፡ ግልጽ በነበረው የሥራ ግንኙነታችን አማካይነት ከማውቀውና እዚህ ላይ ከማቀርበው በቀር፡ ሌላ የማውቀው፡ የተለየ ምክንያት ስለሌለ፡ ያንኑ እገልጻለሁ፤ ይህም፡ ልብ ያሰበውንና ኵላሊት ያመላለሰውን የሚያውቅ፡ እውነተኛው ዳኛ፡ በከሃሊነቱ፡ ገሃድ ያደረገው ድርጊት ነው።

እጨጌ ቴዎፍሎስ፡ ደርግ፡ ሥራውን ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ፡ ከዚሁ፡ ወታደራዊ ቡድን ጋር የነበራቸው ግንኙነት፡ በተለይ እልፍለቃ (Colonel) አጥናፉ አባተ በተባለው፡ የደርጉ ምክትል ሊቀ መንበር ምክንያት፡ እጅግ የተቀራረበ እንደነበረ በግልጽ ይሰማ ነበር። አጼ ኃይለ ሥላሴና እጨጌ ቴዎፍሎስ፡ ኹለቱም፡ በእግዚአብሔር እጅ ወድቀው፡ መጨረሻቸው ስለታወቀ፡ ከዚያ ፍጻሜ ባደረሳቸው፡ በየግል ሥራቸው ሲመዘኑ፡ የእጨጌ ቴዎፍሎስ ብልህነትና ረቂቅ አካኼድ፡ ምናልባት፡ ጥልቅ ከኾነው መንፈሳዊ እውቀታቸው የተነሣ፡ ከአጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ቢበልጥ እንጂ፡ የማያንስ መኾኑ ይታያል። ለዚያ የሥልጣን መንበር ያበቃቸው፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ መኾኑ ቀርቶ፡ ብልህነታቸውና ረቂቅ አካኼዳቸው እንደኾነ፡ ሳያምኑ እንዳልቀሩ፥ ከዚያ ውድቀት ያደረሳቸውም፡ "እንዲህ ነኝ" ብለው በራሳቸው የተመኩበት፡ ያን የመሰለው እምነታቸውና አስተሳሰባቸው ሳይኾን እንዳልቀረ፡ ፍጻሜአቸው ራሱ፡ በሚበቃ መስክሩአል። አድራጎታቸው ኹሉ፡ ለራሳቸውና በራሳቸው ያቀዱት፡ አንዳች ዓላማ እንደነበረ፡ የሚያመለክት ነበር።

ገና የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ሊወድቅ እንዲያ ሲዋዥቅና ሲዋልል፥ በተማሪዎችም በኩል በተነሣሣው የተቃውሞ እንቅስቃሴ ምክንያት፡ በአገር ላይ፡ ያ ኹሉ ውዝግብና ትርምስ ሲፈጠር፡ እንዴት ዝም አሉ?

በለውጡ ዋዜማ፡ ቀደም ብሎ፡ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መካነ አእምሮ (University) ተማሪዎች፡ "የዓመፅ ተግባር ፈጽማችኋል!" በሚል ምክንያት፡ ከመካከላቸው፡ ቀንደኞች የነበሩት ታሥረው በመቆየታቸው፡ ነገሩ እየተባባሰ የመኼድ አዝማሚያ ስላሳየ፡ "እንዴት ዝም ብለን እንመለከታለን! ምን እስኪኾን ነው የምንጠብቀው!" በሚል ሥጋት፡ ኹኔታው፡ ሰላማዊ መንገድ እንዲይዝ ለማድረግ፡ በዚያን ጊዜ፡ ከአዲስ አበባ ምክር ቤት፡ የተመረጥን፡ ጥቂት አባሎች፡ ያደረግነው አስተዋጽዖ፡ ትዝ ይለኛል። ያም አስተዋጽዖ፡ እንዳጋጣሚ፡ ወቅቱ፡ የትንሣኤ በዓል መቃረቢያ የኾነው፡ የሕማማት ሳምንት ስለነበረ፡ በከንቲባው አማካይነት፡ ከአጼው ዙፋን በቀረብን ጊዜ፡ "ሰሞኑ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀሉ መከራ፡ የሰውን ልጅ፡ ከራሱ፥ ከወገኑና ከእግዚአብሔር ጋር ያስታረቀበት ስለኾነ፡ ለተማሪዎቹ ይቅርታ ተደርጎላቸው፡ ፋሲካን ከቤተ ሰቦቻቸው ጋር በደስታ ለማሳለፍ ይፈቀድላቸው!" ብለን አስታርቀን፡ ተማሪዎቹ ስለተፈቱ፡ በዓሉ በሰላም እንዲያልፍ ምክንያት መኾናችን ነበር።

ታዲያ፡ አሁን፡ በየካቲት ወር ፲፱፻፷፮ ዓ.ም. የተነሣሣው፡ የሕዝባዊ ዐመፅ እንቅስቃሴ እየከፋ መኼዱ ሲታይ፡ እጨጌውና ጳጳሳቱ፡ አዲስ በተቋቋመው የሰበካ ጉባዔ አማካይነት፡ ለመንጋቸው፡ ምን አደረጉ? የዓመፁን ምንነት፡ ለምን በቅድሚያ፡ ለቤተ ሕዝቡ በትክክል አላሳወቁም? ተገቢውን ጥንቃቄና ጥበቃስ እንዲያደርግ፡ ምን ዓይነት አመራር ሰጡ? የሰበካ ጉባዔ እንዲቋቋም የተደረገው እኮ፡ ይህን በመሰለው የችግር ጊዜ፡ እንዲያገለግል መኾኑ ይታወቃል። ሁከቱን፡ ወደሰላማዊነት ለመመለስ፡ ሌላው ቢቀር፡ ጸሎትና ምሕላ እንኳ እንዲካኼድ ለምን አልታዘዘም? ዐመፁን፡ ባግባቡ መቋቋም ይችል ዘንድ፡ ምእመናኑንና ካህናቱን የያዘው ቤተ ሕዝቡ፡ መንፈሳዊ ንቃትና ሃይማኖታዊ ብቅዓት እንዲያገኝ ተደረገን? ከዝምታ በስተቀር፡ ምንም የተደረገ ነገር አልነበረም። ከእርሳቸው በፊት የነበሩት፡ እጨጌ ባስልዮስ፡ በክብር ዘበኛ ሠራዊት ዓመፅ ምክንያት ተነሥቶ በነበረው፡ በታኅሣሡ፡ የ፶፫ ዓ.ም. ግርግር ጊዜ፡ ቃል ኪዳን ለገቡለት፡ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የነበራቸውን ታማኝነት በማጽናት፡ ራሳቸው፡ በሰልፉ መካከል እየተገኙ፥ ጳጳሶቻቸውንም፡ ወደደጋፊውና ወደተቃዋሚው ወገኖች እየላኩ፡ ወደእልቂት ያመራው ቁጣ፡ ወደውይይትና የዕርቅ ድርድር እንዲመለስ ለማድረግ፡ በመንፈሳዊ አባትነት የፈጸሙትን የማረጋጋትና የማስማማት በጎ ተግባር፡ እጨጌ ቴዎፍሎስ ያውቁታል።

ታዲያ፡ በእርሳቸው የሥልጣን ጊዜ፡ ዝምታው ለምን ነበር? ዐመፁን በሚመለከት፡ በእርሳቸው፡ በአባ ቴዎፍሎስ የኃላፊነት ደረጃ፡ አንዳችም ዓይነት የተቃውሞ ሙከራ አለመደረጉ፡ ከቶ ምክንያቱ ምን እንደኾነ ለማወቅ ያስቸግራል። ቤተ ሕዝቡም፡ እንዲያ ተደናግሮና ተደናግጦ በሚባዝንበት ጊዜ፡ ብሔራዊዉን አቋም ለማፈራረስ፡ ከብዶ የመጣው ዝናም፥ እያጕረመረመ የቀረበው ወጀብ፥ እያስገመገመ የሚፈስሰው የጎርፍ ማዕበል፡ ምን እንደኾነና ሕዝቡም ያን አጥለቅላቂ ኹኔታ፡ እንዴት ሊቋቋመው እንደሚገባ የተሰጠው መግለጫ አልነበረም፤ ለምን? ምክንያቱ፡ በድርጊታቸው፡ አጠቃላይ ውጤት እንደታየው፡ ለማንም ግልጽ ኾኖ ቀርቧል! እርሱም፡ አባ ቴዎፍሎስ፡ እንደዛሬው ያለ፥ ለሕዝብ ይፋ ያልወጣ፥ ከደርግ ጋር በምሥጢር የተደረገ፡ ልዩ የኾነ፡ የውስጥ ስምምነት እንደነበራቸው ያረጋገጠውና ከመነሻው እስከመድረሻው የታየው ድርጊታቸው ነው።

አባ ቴዎፍሎስ፡ ስለሥነ እውቀታዊው ኅብረተሰባዊነት (Scientific socialism) እና ስለጋርዮሽ ርእዮተ ዓለም፡ (Communism)፡ ስለኹለቱም ፍልስፍናዎች፥ ፍልስፍናዎቹም፡ ስለሚያስከትሉት መዘዝና ጠንቅ፡ ጥሩ አድርገው ያውቁ ነበር፤ ማለትም፡ እነዚህ፡ ባዕዳን ፍልስፍናዎች፡ ኢትዮጵያ ከቆመችበት፡ ከቅዱሱ ኪዳን አቋሟ ጋር፡ ከመሠረቱ እስከጕልላቱ ድረስ፡ ጨርሰው የማይጣጣሙ መኾናቸውን ያውቃሉ:: ታዲያ፡ ደርግ ያን ኹሉ አዋጅ ሲያወጣ፡ እንዴት ዝም አሉ? ቤተ ክርስቲያን ቀብታ፡ ለአጼነት ያበቃቻቸውን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን፡ ደርግ፡ ከዙፋናዊ ሥልጣናቸው ሲያወርድ፥ እርሳቸውን (አጼውን) እና ሹሞቻቸውንም፡ በየተራ ሲያሥርና በግፍ ሲገድል ለምን ዝም አሉ? እንዲያውም፡ ብሔራውያን በዓላትን ምክንያት በማድረግ፡ የመልካም ምኞት መልእክትን፡ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚያስተላልፉበት አጋጣሚ፡ "ኹለት ያለው፡ አንዱን፡ ለሌለው ይስጥ!" የሚለውን የወንጌልን ቃል በመጥቀስ፡ ቤተ ሕዝቡ፡ ከአዲሱ ሰይጣናዊ ሥርዓት ጋር ተስማምቶና አገዛዙን ተቀብሎ እንዲኖር አሳሰቡ!

እንግዴህ፡ ይህን በመሰለው ቀውጢ ጊዜ፡ መሪያቸው የኾነውን የኢየሱስ ክርስቶስንና የእናቱን የድንግል ማርያምን ፈቃድ እየተከተሉ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሥርዓተ መንግሥት፡ ቤተ ሕዝቡን፥ ቤተ ምልክናውንና ቤተ ክህነቱን እንዲያገለግሉ የተሠየሙት እጨጌና ጳጳሳት፡ ይህን ግዳጃቸውን መፈጸማቸው ቀርቶ፡ ተግባራቸው፡ በቀቢቻው፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴና በመንግሥታቸው ላይ ዓምፆ ከተነሣው የክህደት ኃይል ጋር መተባበርና ማበር፥ ለእርሱም መታዘዝና እርሱን ማገልገል ከኾነ፡ ለዚህ ከፍተኛ ክህነታዊ ኃላፊነትና አደራ መሠየማቸውና በመንበሩ ላይ መቀመጣቸው፡ ለእግዚአብሔር፥ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧም፡ ጥቅሙ፡ ከቶ ምንድር ነው?

አባ ቴዎፍሎስና እርሳቸውን የመሰሉት፡ የቤተ ክህነት ሰዎች፡ ምናልባት፡ ለዚህ አካኼዳቸውና ድርጊታቸው፡ ምክንያት የሚያደርጉት፡ "ሰው ኹሉ፡ በበላይ ላሉት ባለሥልጣኖች ይገዛ! ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር፡ ሥልጣን የለምና:: ያሉትም ባለሥልጣኖች፡ በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው::" የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስን መልእክት ከኾነ፡ ሐዋርያው፡ ይህንኑ መልእክቱን የተረጐመውና ያጠቃለለው እኮ፡ ያ ባለሥልጣን፡ ሠይፍ የታጠቀው፡ ክፉ አድራጊውን ሊበቀል፥ መልካም የሚያደርጉ እውነተኞችን ግን ሊጠብቅ የተሠየመ መኾኑን በግልጽ ካስረዳ በኋላ፡ "ለኹሉ የሚገባውን አስረክቡ! ግብር ለሚገባው ግብርን፥ ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን፥ መፈራት ለሚገባው መፈራትን፥ ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ!" በሚል ቃል እንጂ፡ "ሃይማኖታችሁን ክዳችሁ፥ ስለእግዚአብሔር እውነት በገሃድ ለመናገር፡ በምንኵስናችሁና በጵጵስናችሁ፡ ለእግዚአብሔርና ለመለኮታዊ መንግሥቱ የገባችሁትንም ቃል ኪዳን አፍርሳችሁ፡ የሰብአዊው አገዛዝ ሥርዓት አገልጋዮች ኹኑ!"[፲፫] የሚለውን፡ ተቃራኒ የኾነውን አሳብ እንኳ በማመልከት አይደለም::

እንዲያማ ካልኾነ፡ ታዲያ፡ ራሱ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለምን፡ ለሐዋርያቱና ለተከታዮቻቸው እንዲህ አለ? "እነሆ፡ እኔ፡ እንደበጎች፡ በተኵላዎች መካከል እልካችኋለሁ! ..ከሰዎች ተጠበቁ! ለእነርሱና ለአሕዛብ፡ ምስክር እንዲኾን፡ ስለእኔ ወደገዢዎች፥ ወደነገሥታትም ትወሰዳላችሁ! አሳልፈውም ሲሰጧችሁ፡ የምትናገሩት፡ በዚያች ሰዓት ይሰጣችኋልና፡ እንዴት ወይስ ምን እንድትናገሩ፡ አትጨነቁ! በእናንተ የሚናገር፡ የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ፡ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁምና::

የዓለሙ መፍረጃ!

"ወንድምም፡ ወንድሙን፥ አባትም፡ ልጁን፡ ለሞት አሳልፎ ይሰጣል! ልጆችም፡ በወላጆቻቸው ላይ ይነሣሉ! ይገድሏቸውማል፡፡ በኹሉም፡ ስለስሜ የተጠላችሁ ትኾናላችሁ! እስከመጨረሻው የሚጸና፡ እርሱ ይድናል! በአንዲቱ ከተማ፡ መከራ ቢያሳዩአችሁ፡ ወደሌላዪቱ ሽሹ!

"...ደቀ መዝሙር፡ ከመምህሩ፥ አገልጋይም፡ ከጌታው አይበልጥም! ደቀ መዝሙር፡ እንደመምህሩ፥ አገልጋይም፡ እንደጌታው መኾኑ ይበቃዋል፡፡ ባለቤቱን፡ ብዔል ዜቡል (የአጋንንት አለቃ) ካሉት፡ ቤተሰቡንማ፡ እንዴት አብዝተው አይሉአቸው!

"እንግዴህ አትፍሩአቸው! የማይገለጥ፡ የተከደነ፥ የማይታወቅም የተሠወረ ምንም የለምና፡፡ በጨለማ ያስማኋችሁን፡ በብርሃን ተናገሩ! በጆሮአችሁ የነገርኋችሁንም፡ በሰገነት ላይ ስበኩ! ሥጋን የሚገድሉትን፡ ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ! ይልቅስ፡ ነፍስንም፥ ሥጋንም፡ በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ! ኹለት ድንቢጦች፡ በኹለት ቤሳዎች ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም፡ አንዲቱ፡ ያለአባታችሁ ፈቃድ፡ በምድር ላይ አትወድቅም፡፡ የእናንተስ፡ የራሳችሁ ጠጉር ኹሉ እንኳ ተቆጥሮአል፡፡ እንግዴህ አትፍሩ! ከብዙ ድንቢጦች፡ እናንተ ትበልጣላችሁ፡፡ ስለዚህ፡ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ኹሉ፡ እኔ ደግሞ፡ በሰማያት ባለው አባቴ ፊት፡ ስለታማኝነቱ እመሰክርለታሁ! በሰው ፊት የሚክደኝንም ኹሉ፡ እኔ ደግሞ፡ በሰማያት ባለው አባቴ ፊት፡ ስለክህደቱ እመሰክርበታለሁ፡፡

"በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ! ሰይፍን እንጂ፡ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም! (ይህም ማለት) ወንድ ልጅን፡ ከአባቱ፥ ሴት ልጅንም፡ ከእናትዋ፥ ምራትንም፡ ከአማትዋ እለያይ ዘንድ መጥቻለሁና! ለሰውም፡ ቤተሰቦቹ ጠላቶች ይኾኑታል፡፡ ከእኔ ይልቅ፡ አባቱን፣ ወይም እናቱን፡ ወይም ወንድ ልጁን፡ ወይም ሴት ልጁን የሚወድድ፡ ለእኔ ሊኾን አይገባውም! መስቀሉንም የማይዝ፥ በኋላዬም የማይከተለኝ፡ ለእኔ ሊኾን አይገባውም! ነፍሱን ሊያድን የሚወድድ ኹሉ ያጠፋታል! ስለእኔ ግን፡ ነፍሱን የሚያጠፋ፡ ያገኛታል፡፡"

የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ፡ ቅዱስ ጳውሎስም፡ "በቀረውስ፡ በጌታና በኃይሉ ችሎት፡ የበረታችሁ ኹኑ! የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ፡ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ኹሉ ልበሱ! መጋደላችን፡ ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና! ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር፥ ከዚህም፡ ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር፥ በሰማያዊም ሥፍራ ካለ፡ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ፡፡ ስለዚህ፡ በክፉው ቀን ለመቃወም፥ ኹሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ፡ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ኹሉ አንሡ!

"እንግዴህ፡ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፥ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት፡ እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ! በኹሉም ላይ ጨምራችሁ፡ የሚንበለበሉትን፡ የክፉውን ፍላጻዎች ኹሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን፡ የእምነትን ጋሻ አንሡ! የመዳንንም ራስ ቍር፥ የመንፈስንም ሠይፍ ያዙ! እርሱም፡ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡" ያለው፡ ሕያው መመሪያ፡ በተግባር ላይ የሚውለውስ፡ ታዲያ መቼ ነው? እንደዛሬው ዘመን፡ በእግዚአብሔር የማያምንና በዲያብሎስ የሚመራ፡ ዓመፀኛ፥ ከሃዲና አመንዝራ መንግሥትና ትውልድ በሚነግሥበት ጊዜ ካልኾነ በቀር፡ ለሌላ፡ ለመቼ ሊኾን ነው?[፻፲፬]

## የኹለት ብልሆች ብልጠት ሲነጻጸር።

በዚህ ረገድ የነበረውን፡ የአባ ቴዎፍሎስንና የአጼ ኃይለ ሥላሴን፡ የብልህነት አሠራርና አካኼድ ለማመዛዘን፡ በአንድ ወገን፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ገና ንጉሥ ተፈሪ ተብለው፡ የኢትዮጵያን መንግሥት፡ በባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴነት በሚመሩበት ጊዜ፡ ከተፈጸሙት ድርጊቶች መካከል፡ እስቲ፡ ለምሳሌ ያህል፡ አንዲቱን ብቻ፡ ደረጃ በደረጃ እየተከተልን፡ ባጭሩ እንመልከታት! በዚያ፡ በቀደመው ዘመናቸው፡ ራስ ጉግሣ ወሌ፡ የኢትዮጵያን፡ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖትና ምግባር፡ በባዕዳን ሃይማኖትና ምግባር ለመለወጥ፡ በአዲስ አበባ፡ በሽፍንፍን መካኼድ የጀመረውን፡ ረቂቅ የጠላት ዕቅድ በመቃወማቸው፡ ከሥጋ ወደሙ ሚስታቸው፡ ከወይዘሮ ዘውዲቱ ምኒልክ ተለይተው፡ ወደበጌምድር ተላኩ፤ ኋላም፡ ወይዘሮ ዘውዲቱ፡ ዘውድ ጭነው፡ በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ፡ በንግሥትነት እንዲቀመጡ ሲወሰን፡ በቅድሚያ፡ እኚሁኑ ባላቸውን፡ ራስ ጉግሣን "ፈትቻለሁ! ወደፊትም፡ ባል አላገባም!" ብለው ቃለ መሐላ፡ በጽሑፍ ኪዳን ጭምር እንዲፈጽሙ ተደረገ። ያም አልበቃ ብሎ፡ "ራስ ጉግሣ፡ በዚያ ተቃውሞአቸው ጸንተዋልና፡ መወገድ አለባቸው" በሚል ምክንያት፡ ፈንጂ በምትጥል በአንዲት ጥያራ (airplane) ሳይቀር በመጠቀም፡ በታወጀባቸው ጦርነት፡ መጋቢት ፳፪ ቀን፥ ፲፱፻፳፪ ዓ. ም. ተገደሉ፤ የወንድማማች ደም በፈሰሰበት፡ በዚያ የሃይማኖት ጦርነት፡ በድንጋጤና በኃዘን ማዕበል የተጥለቀለቁት ባለቤታቸው፡ ንግሥት ዘውዲቱ፡ ደግሞ "ታምመዋል" ተብሎ፡ በተቀነባበረ የሕክምና ሽፋን፡ በሣልስቱ፡ መጋቢት ፳፬ ቀን፡ "ማረፋቸው" ተነግሮ፡ የቀብራቸው ሥርዓት፡ ወዲያው ተፈጸመ! በዚህ ጊዜ፡ Hanner (ሐነር) የሚል ስም ያለውን ፈረንጅ ሐኪም፡ አውሬ ድመት በኾነው በ"አነር" በመመሰል፡ *"ድሮም በቤታቸው፡ ድመት ነው ዕርማቸው፤ ንግሥት ዘውዲቱን አነር ገደላቸው!"* ተብሎ በሕዝቡ ተለቀሰላቸው።

እኒህን ከመሰሉት፡ "የማይፈለጉ እንቅፋቶች" የተረፉ ቢኖሩ፡ እውነተኛው ዳኛ እግዚአብሔር፡ ለዚህ ድርጊት፡ የሰጠውን የቅጣት ፍርድ ለመፈጸም በተላከው የፋሺስት ጣልያን የቁጣ ኃይል የተፈጁ ሲኾን፥ ከዚሁ ጠላት መባረር በኋላም፡ እነደጃዝማች በላይ ዘለቀን የመሰሉት አርበኞች፡ [፲፲፭] በወንጀልና በየምክንያቱ ሰለባዎች እየኾኑ መወገዳቸው ይታወሳል።

አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ወደዘመናቸው ፍጻሜ አቅራቢያ፡ ማለትም፡ በታኅሣሥ ወር፡ ፲፱፻፶፫ ዓ. ም. ወደብራዚል ካደረጉት ጕብኝታቸው በፊት፡ በአስተዳደራቸው ላይ ሊደርስ ስለተቃረበው፡ የመንግሥት ግልበጣ አደጋ፡ ከቅርብ ባለሥልጣኖቻቸውና ከምሥጢር ሠራተኞቻቸው የቀረበላቸውን ግልጽ መረጃ፡ ቸል በማለትና ለአደጋው መፍትሔ ባለመስጠት፡ ኾን ብለው ትተው፡ የጉብኝት ጕዟቸውን መቀጠላቸው ይታወሳል። ወዲያው፡ በክብር ዘበኛ ሠራዊታቸው ዋና አዛዥ፡ በጦር አዝማች (General) መንግሥቱ ንዋይ፥ በወንድሙ፡ ባቶ ገርማሜ ንዋይ፥ በብሔራዊው የጸጥታ ሹም፡ በእልፍለቃ (Colonel) ወርቅነህ ገበየሁና በሕግ ዘበኛው (Police) ዋና አዛዥ፡ በጦር አዝማች ጽጌ ዲቡ መሪነት በተካኼደው፡ የአልጋ ማፍረስ ሙከራ፡ በግፍ ግድያ ለተወገዱት፡ ለአያሌዎቹ ኅምቱ (ታላላቅ) ባለሥልጣኖቻቸውና በዚያ ምክንያት ለፈሰሰው የንጹሓን ሰዎች ደም፡ በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂው ማን ይኾናል ተብሎ ነው የሚታሰበው?

## የዓለሙ መፋረጃ!

አሁን ደግሞ፡ በእርግ(ጅ)ና ዕድሜያቸው ማብቂያ ላይ፡ በዚያው ልምድ፡ ከደርግ ጋር ተስማምተውና አገዛዛቸውን፡ ኮሚዩኒስቱ ጓደኞቸው፡ ቲቶ፡ በዩጎዝላቪያ ባደረገው ዓይነት አስተካክለው፡ በመሪነታቸው ለመቀጠል ሲሉ፡ እንዲታሠሩ የፈለጓቸውን፡ የረዥም ዘመን ታማኞች አገልጋዮቻቸውን ባለሥልጣኖች ኹሉ፡ አንድ በአንድ፡ በጽሑፍ እያስጠሩና እያስለቀሙ፡ ራሳቸው፡ ብቻቸውን እስኪቀሩ ድረስ፡ ለደርግ ሰለባ ይኾኑ ዘንድ አሳልፈው ሰጧቸው፤ በአንድ ሥፍራ አሰባስበውም አስፈጇቸው::

በሌላው ወገን ደግሞ፡ በዚህ ረገድ፡ እጨጌ ቴዎፍሎስ፡ ካካኼዷቸው መካከል፡ አንዷቱንና የመጨረሻዋን ብቻ እስቲ፡ በመጠኑም ቢኾን እንመልከት! በደርግ መሣሪያነት፡ *"ምእ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚለውን፡ መለኮታዊ ምልክትና ማኅተም፡ ጨምሮ በያዘው፡ በቅዱሱ ኪዳን ሥር የቆመችውን፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ ከተቀባው ተጠሪዋ፡ ከአጼ ኃይለ ሥላሴና ከዚሁ ምልክቷ ጋር፡ አስወግደው፡ ከቤተ ሕዝቡና ከቤተ ምልክናው፡ ተሣታፊነት፡ ነጻ የኾነና ራሱን የቻለ፡ የማናለብኝነት እንግዳ ሥርዓት አቋቁመው፡ ቤተ ክህነትን ለብቻቸው ሊመሩ እየተጣደፉ፡ ተገቢውን ዝግጅት አደረጉ:: የክህደቱና የዓመፁ አገዛዝ በሰፈነበት፡ በዚያው፡ በደርግ ዘመን፡ በእርሳቸው እጅ፡ የጵጵስናን ሹመት የተቀበሉት፡ አባ ጳውሎስም፡ ዛሬ እያደረጉ ያሉት፡ የእርሳቸውን ፈለግ ተከትለው ስለኾነ፡ ሊያስደንቅ አይችልም::

ከእርሳቸው በኋላ፡ በእርሳቸው መንበር ላይ የተቀመጡት፡ እጨጌዎችና ሌሎቹ ጳጳሳት ኹሉ፡ ዛሬ ያሉት ጭምር፡ *"ምእ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚለው፡ ይህ መለኮታዊ ቃልና ትእምርታዊ ማኅተም፡ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ወይም ከእርሳቸው በፊት ለነበሩት አጼዎች፡ ለማናቸውም የተሰጠ ሳይኾን፡ የራሱ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ የብቻ ገንዘቡ መኾኑን፥ ኢትዮጵያም፡ ጠብቃውና አጽንታው የኖረች መኾኑን እያወቁ፡ ከደርግ ጊዜ ጀምረው፡ በቤተ ክህነቱ ውስጥ ጭምር፡ እንዲወገድ ያደረጉት፡ ለዚሁ ዓላማቸው እንዲረዳቸው መኾኑን፡ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብና ቤተ ምልክና፥ ቤተ ክህነትም አጠንክረው ሊያውቁት፥ ነቅተውም፡ በጊዜው፡ ተገቢውን ሊፈጽሙ ይገባል::

በአጼ ኃይለ ሥላሴና በእጨጌ ቴዎፍሎስ በኩል፡ ይህ ኹሉ ሲኾን፡ ኹለቱም፡ እግዚአብሔርንና የቅዱሱን ኪዳን ሕዝብ ጨርሰው፡ ከአሳባቸው ቀርቶ፡ ከግምታቸው እንኳ አሳስገቧቸውም:: ኹለት ብልሆች፡ አንዱ ከሌላው፡ "እኔ እበልጣለሁ" በማለት፥ አንዱ፡ ሌላውን መሣሪያ አድርጎ፡ ለመጠቀም በመሞከርና "እኔ እበልጣ! እኔ እበልጣ!" በመባባል፡ እነርሱ ብቻ በየፊናቸው የሚያውቁትን፥ በእነርሱ ዘንድ ግን፡ "እግዚአብሔር አያውቅብንም!" ብለው በየልባቸው የደበቁትን፡ ሥውር ዓላማቸውን፡ ከግብ ለማድረስ ሲናውዙ ኖሩ!

አዬ የሰው ልጆች ከንቱነት! አዬ አላዋቂነታቸው! የተዘጋጀላቸውን ድግሥ አለማስተዋላቸው! በዚህ ጊዜ፡ እነርሱ የተዉት፡ *"በሰማይ የሚኖረው እርሱ እግዚአብሔር ግን፡ በእነርሱ ይስቃል፤ ይሣለቅባቸውማል::"* ቀጥሉም፡ *"በቍጣው ይናገራቸዋል፤ በመዓቱም ያውካቸዋል!"* የሚለው፡ የነቢዩ ቃል ተፈጸመ! ኹለቱም፡ እየራሳቸውን፡ በየወርቅ ዙፋናቸው ላይ ሳይኾን፡ በእሥር ቤት ወለል ላይ [XII] ባገኙት ጊዜም፡ ያ፡ "ብልጥ ለብልጥ!" የሚለው ሕዝባዊ አነጋገር ደረሰ!

እግዚአብሔርን ትቶ: የራስን ብልህነት: ወይም የሌላውን ጥበብ: ማለትም: የባዕዱን ወይም የዲያብሎስን መንገድ መከተል: ውጤቱ እንግዴህ ይህ ነው:: ይህም: የሚያይ ዓይን፥ የሚሰማም ጆሮ ላለው ኹሉ: በግልም ኾነ: በአገር ደረጃ: የመቀጣጫ ምሳሌነቱ እጅግ ጠቃሚ ነው::

ለቃል ኪዳኑ የታመነው: እግዚአብሔር ብቻ ሲኾን: ከእርሱ ይልቅ እምነታቸውን የጣሉበት ደርግ: በተለመደው ክሀደቱና ዓመፁ: ለአጼ ኃይለ ሥላሴና ለአጨጌ ቴዎፍሎስ የሰጠውን የሽንገላ ቃል: ጊዜም ሳይሰጠው: ወዲያው አፍርሶ: ኹለቱንም ለእሥራት ብቻ ሳይኾን: ለሞትም ዳርጓቸዋል::

## ከቤተ መንግሥት ወደቤተ ሞቅሕ::

እጨጌ ቴዎፍሎስ: "ይኾናል" ብለው ባልጠረጠሩት ጊዜና ኹኔታ: ደርግ: ድንገት: ከሥልጣን መንበራቸው ሲያወርዳቸው: ለእርሱ: ሥልጣን መያዝና መደላደል: የሰጡትን ጠቃሚ አገልግሎት: እግምቱ ውስጥ በማስገባት ይመስላል: ለእሥር ቤትነት አዘጋጅቶላቸው የነበረው ሥፍራ: የቤተ መንግሥት ምግብ እየቀረበላቸው: ከመዝናኛነት አልፎ: በሥጋዊ ምቾት: በተድላ ደስታ የሚቀመጡበት እንደነበረ ይታወሳል:: ያም ሥፍራ: ቀድሞ "ኢዮቤልዩ"፥ ኋላ: "ብሔራዊ" በተባለው ቤተ መንግሥት ግቢ ውስጥ ባለው: ልዩ: የልዑላን መሳፍንት መኖርያ ቤት ነበር::

ሰዎች: በበኩላቸው: ይህን የመሰለውን ችሮታ ሊያደርጉላቸው ቢፈልጉም: ፍርዱ: ጥንቱኑ: ከእግዚአብሔር ነውና: አባ ቴዎፍሎስ: በዚያ ምቾት: ብዙም ሊቆዩ አልቻሉም:: ከዚያ ከተዘጋና ዙርያውን: በወታደሮች ተከብቦ ከሚጠበቀው ቤት: ወጥተው ለማምለጥ የቻሉትም: ባላወቁት የመንፈስ ኃይል: ወድደው ሳይኾን: ተገድደው መኾኑን: ከዚህ በሚከተለው መልክ: እራሳቸው: በአንደበታቸው: የተናገሩት: የምስክርነት ቃል ያስረዳል::

አንድ ቀን: ወደምሽቱ ግድም: በባለመከዳ የምቾት ወንበር ላይ ተቀምጠው: ጥቂት ሸለብ አድርጓቸው ሣሉ: በዚያው ሸለብታ ውስጥ: "ና!" የሚል የጥሪ ድምፅ ይሰማሉ፤ ገርበብ ወዳለው: ወደፊት ለፊታቸው መስኮት ሲመለከቱም: የሚጠቅሳቸውን ምልክት ያያሉ፤ ደንግጠው ሲነቁ: ቅዠት ይመስላቸውና ተመልሰው: ሸለብታቸውን ይቀጥላሉ፤ አሁንም: ያው ድምፅና ምልክት እንደገና ይመጣባቸዋል፤ አሁንም: ደንግጠው ይነቃሉ፤ በዚህ ጊዜ ግን: "እስቲ ይህን ነገር: ተነሥቼ: ልረዳው!" ብለው: ከመቀመጫቸው ይነሡና ድምፁ ወደተሰማቸውና ምልክቱ ወደታያቸው: ወደመስኮቱ አግጣጫ ይኼዳሉ፤ የተዘጋውንም መስኮት: አንዱን ተካፋች: ገፋ ሲያደርጉት: አልተዘጋ ኖሮ: ወይም በተአምር: ወይም ለዘዴ ኾን ተብሎ ተከፍቶላቸው እንደኾነ አልታወቀም: ይንቀሳቀስላቸዋል::

በነገሩ ግራ ተጋብተው: እያመነቱ: ተቀምጠው ሣሉ: ሊገቱት ያልተቻላቸው: "ተነሥ! ውጣ!" የሚል የሚገፋፋ ኃይል በውስጣቸው ስለተሰማቸው: በድፍረት: ቀስ ብለው: በመስኮቱ በኩል ዘልለው ይወጡና: በኤለቄጥሩ የነፋስ መብራት (electric florecent light) በደመቀውና ጠባቂዎቻቸው ወታደሮች ቆመው እየተነጋገሩ በሚታዩበት ግቢ ውስጥ ወዳለው: ወደቤተ መንግሥቱ የጸሎት ቤት አመሩ::

የዓለሙ መፋረጃ!

በዚያ፡ ጥቂት ጸሎት አድርገው፡ አረፍ ካሉ በኋላ፡ አሁንም፡ ያው፡ "ተነሥ! ኺድ!" የሚለው መንፈስ ስላስገደዳቸው፡ ተነሥተው፡ በግዮን ቤተ ነግድ (Hotel) በኩል ወደሚያወጣው የአጥር በር መራመድ ጀመሩ:: ከበሩም ሲደርሱ፡ እያወኑ ያሉት፡ ዘበኞቹ ወታደሮች እያዩዋቸው፡ ቀጥ ብለው ኼደው፡ ገርበብ ብሎ በተከፈተው የቅጥሩ መዝጊያ መካከል አልፈው ወጡ፤ ከዋናው ጎዳና ሲገቡም፡ መንገዳቸውን፡ እርሳቸው ወደአሳነጹት፡ ወደጎፋ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አቅንተው ቀጠሉ::

እንደተውኔት የሚቆጠረው፡ ይህ አጠቃላይ ኹኔታ፡ አንድን ሰው፡ በወንጀል፡ እጅ ተፍንጅ ለመያዝ፡ ኾን ተብሎ፡ በዛሬው ዘመን፡ በቀላሉ፡ በፀጥታ ሠራተኞች ተቀነባብሮ፡ የሚጠመደውን፡ አሽከላንም ይመስላል፤ እግዚአብሔር ይወቅ!

ከዚያ ቤተ ክርስቲያናቸው ከደረሱ በኋላ የኾነው፡ እጅግ ያሳዝናል:: እንደተባለው፡ ከዐፀደ ቤተ ክርስቲያኑ ጋር የተያያዘ ቦታ ሰጥተውት፡ በእዚያ፡ ቤት ሠርቶ፡ ሲረዱት የኖረ ሰው፡ የእርሳቸውን በዚያ መገኘት፡ ለደርግ ጠቁሞ ኖሮ፡ በበነጋታው በደርግ ወታደሮች ተይዘውና ከፍተኛ መጒላላት ደርሶባቸው፡ እኛ ወደምንገኝበት፡ በታላቁ ቤተ መንግሥት ግቢ ውስጥ ወደነበረው እሥር ቤት አመጧቸው:: ሲያመጧቸውም፡ የምንኵስና ቆባቸው ወልቆ፡ ባዶ ራሳቸውን፥ እጆቻቸው፡ በአንድነት ታሥረውና እግሮቻቸው፡ ያለጫማ፡ ሹራብ ብቻ ለብሰው ነበር:: አምጥተውም፡ ከእሥረኞቹ ጋር እንዲቀላቀሉ አላደረጉም፤ ለብቻ በኾነች አንዲት ክፍል ውስጥ በተዘረጋ የሽቦ አልጋ ላይ፡ እጅና እግራቸው እንደታሠሩ፡ አስተኟቸው::

ይህ ኹሉ የደርግ የጭካኔ ድርጊት፡ "እኛ በክብርና በምቾት ቦታ፤ አቀማጥለን ብናስቀምጥዎ፡ እርስዎ፡ ያን በዓት ሰብረው፡ እንደሌባ ይጠፋሉን?" የሚል የበቀል ግፍ ያለበት ይመስላል:: ይኹን እንጂ፤ ከመለኮት ጻኝነት፡ ማንም ማምለጥ እንደማይችልና መቆያቸውም፡ በዚህ እሥር ቤት እንጂ፡ በቤተ መንግሥት እንዳይኾን፡ በእርሱ፡ በሾማቸው አምላክ እንደተወሰነ፤ ኹኔታው ያሳያል።

በዚህ ጽኑ እሥር ምክንያት፡ ምግብ ለመብላት ፈቃደኛ ካለመኾናቸው የተነሣ፡ የሥጋ አካላቸው ስለደከመ፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ፡ ከዚያች ክፍል አውጥተው፥ እጅና እግራቸውንም ፈትተው፡ ከሌላው እሥረኛ ጋር እንዲቀላቀሉ ፈቀዱላቸው:: "መነኵሴ ከመነኵሴ ጋር ቢኾን ይሻላል" ተብሎ ይመስለኛል፡ ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም የተባሉት መነኵሴ ወደነበሩበት፡ የምድር ቤት አካፋይ መደቧቸው፤ ይኹን እንጂ፡ በኹለቱ መነኵሳት መካከል የነበረው መቃቃር፡ በዚያ፡ የሞት ጥሪ በሚጠበቅበት፡ የንስሓ ቦታ እንኳ፡ ሊወገድ ባለመቻሉ፥ የእሥረኝነት ቅድሚያም፡ እንደመብት ተቆጥሮ፡ በእሥር የቀዩት መነኩሴ፡ አዲሱን እሥረኛ እጨጌ፡ "ወደእኔ አይምጡብኝ! አልቀበላቸውም!" ብለዋል ስለተባለ፡ የነበረው አማራጭ፡ እኔ ወዳለሁበት አካፋይ ምድር ቤት እንዲመጡ ማድረግ ብቻ ኾነ!

እዚህም ላይ፤ ሌላው፡ እንግዳ ኾኖ ያገኘሁት ነገር ቢኖር፡ ያን አማራጭ፡ ማስፈጸም ይቻል እንደኾነ፡ እኔ ደግሞ፡ በተራዬ እንድጠየቅ ማስፈለጉ ነበር፤ ይኹን እንጂ፡ ያ፡ ጥያቄ፡ ለእኔ ለእሥረኛው፡ እንዴት ሊቀርብልኝ እንደቻለ፡ ለራሴ ተገርሜ፡ ወዲያው "እሺ! ደስ ይለኛል!" ብዬ፡ ለጥያቄው መልስ ሰጠሁ::

በዚህ ጊዜ፡ የእሥር ቤቱ ኃላፊዎች፡ ያልጠበቁትን ምላሽ፡ ከእኔ በማግኘታቸው፡ ተደንቀውና አመስግነው፡ እሥረኛውን እጨጌ ቴዎፍሎስን፡ እኔ ወደነበርኩበት የእሥር ክፍል አመጧቸው። ሲያመጧቸውም፡ ማንነታቸውን መለየት እስከሚሳን ድረስ፡ ሰውነታቸው፡ እጅግ ከሥቶና ገርጥቶ ስለነበረ፡ ከሌሎቹ እሥረኞች ጋር፡ እኔም፡ በጥልቅ ኀዘኔታና እንባ ተቀበልኳቸው። ያ አቀባበሌ፡ በብዙዎቹ እሥረኞችና የደርግ ተጠሪዎች ዘንድ፡ ያልተጠበቀ ኖሮ፡ መደነቃቸውን ተመለከትሁ፤ ቀድሞውንም ቢኾን፡ ወደሌላው ክፍል ተመድበው የነበረው፡ እኔ የማላውቀው፥ እነርሱ ግን የሚያውቁት፡ እርሳቸው፡ በእኔ ላይ በፈጸሙት በደል ምክንያት፡ እኔ፡ ቂም ይዤ፡ አሁን የምበቀል መስሏቸው እንደነበረ፡ ኋላ ልገነዘብ ቻልኩ።

## በእሥር ቤት የተሰማው ተአምር።

በዚያ እሥር ቤት፡ አብረን ማሳለፍ በጀመርናቸው፡ ጥቂት ዓመታት መነሻ ላይ፡ ስለእግዚአብሔር ፍርድ፡ እርሳቸውንና እኔን በሚጠቅሰው ዳኝነቱ የተደነቅንበትን፡ አንዱን ሥራውን፡ እዚህ ላይ፡ በምስክርነት ቃሌ ልጠቅስ እወድዳለሁ። ይኸውም፡ ፊት፡ "አባ መልአኩ ወልደ ሚካኤል"፥ ኋላም፡ "አባ ተክለ ሃይማኖት" በተባሉት ባሕታዊ መነኵሴ ላይ የተፈጸመውን ተአምር የሚመለከት ነው።

በኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ውስጥ፡ አባ ቴዎፍሎስ፡ "እጨጌ"፥ እኔ፡ "ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ" ሣለን፡ ኃላፊነቴና ተግባሬ በኾነው የሥራ ድርሻዬ፡ አዘጋጅቼ፡ ለቤተ ክህነቱ ሲኖዶስና የአስተዳደር ጉባዔ ያቀረብኩት ረቂቅ፡ ከጸደቀ በኋላ፡ በቃለ ዐዋዲ የወጣውን፡ የሰበካ ጉባዔ ለማቋቋም፡ በአዲስ አበባና በመላ ኢትዮጵያ በምዘዋወርበት ጊዜ፡ አባ መልአኩ፡ በብሕትውና፡ ይኖሩበትና ያገለግሉበት ወደነበረው፡ ወደወላሞ ሶዶ ዋና ከተማ፡ ወደሆሣዕናም፡ ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር ኼጄ ነበረ። በዚያ፡ አስተዳዳሪው፡ ደጃዝማች ወልደ ሰማዕት መሪ ኾነው፡ በመላዋ አውራጃ ውስጥ፡ በዕቅድ ይካኼድ በነበረው የልማት ሥራ ጐን፡ ዐፅፍ ለባሹና በእግር ተጓዡ ባሕታዊ፡ አባ መልአኩ፡ ተባባሪና ተሣታፊ ኾነው፡ የቤተ ክህነቱን ድርሻ፡ በተመሰሳሳይ ዘመናዊነትና በተሳካ ይዞታ አከናውነውት አየሁ።

ደግሞም፡ በዚያ ከሚገኙት፡ የሰበካ አብያተ ክርስቲያናት ጋር፡ በደብረ ሊባኖስ ገዳም ሥር የሚተዳደረውን፡ የተክለ ሃይማኖትን ቤተ ክርስቲያን ጭምር ጐብኝቼ ስለነበረ፡ ያ ቤተ መቅደስ፡ ከዋናው እናት ገዳም በመራቁ፥ የገዳሙ ተጠሪ የኾነው ሹምም፡ ተመርጦ የሚላከው፡ ከዚያው ከገዳሙ ኾኖ፡ እርሱም፡ ብቅ የሚለው፡ የተሰበሰበውን ገቢ ለመውሰድ፡ በዓመት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ በመኾኑ፡ ባገልግሎቱም ኾነ፡ በአስተዳደሩ፥ በንብረት አያያዙም፡ የደረሰውን በደልና ጕሥቍልና በሚበቃ ተረድቼ ነበር።

ስለዚህ፡ ወደአዲስ አበባ እንደተመለስሁ፡ የጉብኝት ውጤቴን፡ እንደተለመደው፡ ለእጨጌ ቴዎፍሎስ ባቀረብሁበት ጊዜ፡ በሆሣዕና የተመለከትሁትን፡ የአባ መልአኩን፡ የሥራ ክንውን መሠረት በማድረግ፡ ቀጥሎ የተገለጸው የውሳኔ አሳቤ፡ በሥራ ላይ እንዲውል ፈቃዳቸውን ጠየቅሁ።

ያም፡ የውሳኔ አሳብ፡ “አባ መልአኩ፡ ለአውራጃው የልማት ዕቅድ መሳካት ሲባል፡ ማንም የበላይ ባለሥልጣን ሳይገባበት፡ በቀጥታ ከአጼው ጽሕፈት ቤት ጋር ብቻ እየተገናኘ፡ ራሱን ችሎ እንዲሠራ፡ ልዩ መብት ከተሰጠው፡ የአውራጃ አስተዳዳሪ ጋር እንዲህ ተግባብተው፥ ከዘመናዊው፡ የአውራጃ የልማት አሠራርም ጋር እንዲህ ተባብረው፡ በንቃት የመሥራትና እኩል የመራመድ ችሎታን ለማሳየት መብቃታቸውን ተመልክቻለሁ፤ ለዚህ የውሳኔ አሳብ አፈጻጸምም፡ እኝህ መነኩስ፡ 'አዲስ አበባ ድረስ መጥተው፡ እስካሁን አላመለከቱም፤ ወይም፡ ወደፊት፡ ራሳቸው መጥተው ሊያመለክቱ ይገባል፤ ወይም፡ በማናችንም ዘንድ፡ ይህን ያህል የሚታወቁ አይደሉም' የሚለው ምክንያት፡ አስፈላጊ አይመስለኝም፤ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ መሥርቷት፥ አቋቁሟትና ፈጽሟት ለሚያካኺዳት ቤተ ክርስቲያናችን፡ እኝህ ካህን፡ በዚህ አውራጃ ውስጥ፡ የአገልግሎት ተጠሪዋ ኾነው ለመመረጥና ለመሠየም፡ ዐፅፍ ለባሽና ባዶ እግራቸውን የሚኼዱ፡ ተራ ባሕታዊ መኾናቸው፡ መሥፈሪያ፡ ወይም መመዘኛ ሊኾን አይገባም:: ስለዚህ፡ አባ መልአኩ፡ የዚህ አውራጃ ቤተ ክህነት ሊቀ ካህናትና ሥራ አስኪያጅ ቢኾኑ፥ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ልጅ በመኾናቸውም፡ በሆሣዕና፡ የተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ተጠሪ ይኾኑ ዘንድ፡ በእጨጌነትዎ ቢፈቅዱላቸው ይጠቅማል፤” የሚል ነበር::

ይህ፡ የውሳኔ አሳብ ግን፡ ተቀባይነትን አግኝቶ፡ እንኳንስ ሊፈጸም ይቅርና፡ እኔን፡ “ይህን የመሰለ፡ ዝቅ ያለ አስተያየት ማቅረቡ፡ ምን ማለቱ ነው?” ከሚለው ትዝብት፡ ሊያድነኝ ሳይችል ቀርቶ፡ አልኾነ ግምት ላይ ወድቄ፡ ነገሩ በሣቅ ቆመ! እኔም፡ ግራ ገብቶኝ፡ በትካዜ፡ ወደጽሕፈት ቤቴ ተመለስኩ::

ከጥቂት ዓመታት በኋላ፡ አንድ ቀን፡ እጨጌ ቴዎፍሎስና እኔ፡ በዚያ እሥር ቤት ውስጥ ተቀምጠን፡ እንዳስለመድነው፡ በቀላል ጉዳዮች ላይ እየተወያየን ሣለን፡ እንዳጋጣሚ ያ ቀን፡ ጦማረ ሕዝብ፡ ለእሥረኞች እንዲገባላቸው የተፈቀደበት ዕለት ኖሮ፡ የአንዱን ጦማረ ሕዝብ ቅጂ ሰጥተውን ስንመለከት፡ የኹለታችንም ዓይኖች፡ በትላልቅ ፊደላት በተጻፈው ዋና ርእስ ላይ ዐረፉ:: ያም ርእስ፡ “አባ መልአኩ፡ ለኢትዮጵያ ፓትሪያርክነት ተመረጡ!” የሚል ነበር:: በዚያች አፍታ፡ ኹለታችንም ቀና ስንል፡ ዓይን ለዓይን ግጥም አልን! አንዳችም ቃል ሳንለዋወጥ፡ እንደገና፡ ወደጦማረ ሕዝቡ አቀርቅረን፡ ሌላውን ጎረፍ ጎረፍ አድርገን ተመልክተን፡ ተለያየን::

የእርሳቸውን፡ እንጃ እንጂ፡ በእኔ በኩል የእግዚአብሔርን፡ የአሳቡን አካሄድና የፍርድ ሥራውን በማድነቅ፡ “ወይ አንተ አምላክ! አባ መልአኩ፡ 'ለአንዲት አውራጃ፡ የተልእኮ መንበርና ለአንዲት፡ ገጠር ለኾነች ቤተ መቅደስ ተጠሪነት፡ አይበቃም!' ያሉትን ሰው፡ ከመንበራቸው አንሥተህ፡ 'አዎን፥ እኔም፡ ለአንዲት አውራጃ፡ የተልእኮ መንበርና ለአንዲት ገጠር ለኾነች ቤተ መቅደስ ተጠሪነት አልበቃም!' ብለው፡ ከባለሥልጣን ፊት በመቅረብ፡ ደጅ ከመጥናት ይልቅ፡ ለፈጣሪያቸው በቃል ኪዳን የገቡትን፡ የግል ተልእኮ፡ ዝም ብለው በመፈጸም፡ በትሕትና የሚኖሩትንና እንዲያ የተዘበተባቸውን፡ ምስኪን ባሕታዊ፡ ለኢትዮጵያ የእጨጌነት መንበር ማብቃትህ፡ ጥበብህና ተአምራትህ፡ ምን ይረቅ! ምን ይደንቅ!” ብዬ፡ ወደተመሥጦዬ ተመለስሁ::

ፍርድ ከእግዚአብሔር ስለኾነ፥ ፍርዱም፡ ስለኃጢአተኛው በንስሓ መመለስ ሲል፡ ቢዘገይም እንኳ፡ ኃጢአተኛው፡ በንስሓ ካልተመለሰ፡ በመጨረሻ ስለማይቀር፡ "ይህ ኹሉ፡ በአባ ቴዎፍሎስ ላይ ለምን ደረሰ?" ብለን ለምናቀርበው ጥያቄ፡ አሁንም የሚበቃ መልስ ያገኘን አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም፡ ኹላችንንም አንድ ከሚያደርገን፡ የተፈጥሮ ባሕርያችን የተነሣ፡ እንደማነኛችን ኹሉ፡ ስለእርሳቸውም የእምነት ሥራ፡ እግዚአብሔር ከሚያውቀው በላይ፡ "እኛ ያወቅነው፡ ይህን ያህሉን ነው" ብለን፡ በማብዛትም ኾነ በማሳነስ፡ ወስነን መናገር ስለማንችል ነው፡፡

ታዲያ! አባ ቴዎፍሎስ፡ ፍጻሜያቸው ይህን ሊመስል የቻለው፡ በዚህ፡ በይፋ በታወቀውና በገሃድ በፈጸሙት ግብራቸው ነው? ወይስ ሌላ ይኖር ይኾን? ወይስ፡ እኒያ፡ ሃይማኖታቸውን፡ በሰማዕትነት ምግባራቸው ስላስመሰከሩ፡ በእውነት፡ "ብፁዕ ወቅዱስ" ሊባሉ የሚገባቸው፡ አቡነ ጴጥሮስ፡ በፋሺስት ጣልያን መትረየስ፡ በግፍ ለተፈጸመባቸው ግድያ፡ ባበቃቸው ፍርድ ውስጥ፡ አባ ቴዎፍሎስ፡ ገና "አባ መልእክቱ" ይባሉ በነበረበት ዘመን፡ "ደጋፊነታቸውን የሚያረጋግጥ ጽሑፍ ተገኝቷል" የሚባለውን፡ የንጹሑን ሰማዕት ደም የመሰለ ኃጢአት፡ በእጃቸው ኖሮ ይኾን?

ወይስ፡ ኢትዮጵያ፡ በፋሺስት ጣልያን ተወርራ በነበረበት ዘመን፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ተጠሪ ኾነው፡ በአቡን አብርሃም መንበር ከተተኩት፡ አቡን ዮሐንስ ጋር፡ የሙሶሎኒ እንግዳ ኾነው፡ ወደሮማ ኼደው ሣለ፡ በአሳብ፥ በቃል፥ ወይም በድርጊት፡ የፈጸሙት በደል ይኖር ይኾን?

ወይስ፡ እርሳቸው፡ ገና፡ በእጬጌነት መንበራቸው እያሉ፡ በጊዜው፡ የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ከነበሩት፥ ለግል ጥቅምና ስም እንጂ፡ በእምነት ጽናትና በታማኝነት ረገድ፡ የምግባር ብቃት ካልታየባቸውም፡ ከአቶ መኰንን ዘውዴ ጋር በመመሣጠር፡ በደርግ እሥር ቤት ውስጥ፡ የሞት ጥሪውን ይጠባበቅ በነበረው፡ በዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ላይ፡ የመጨረሻው የፍርድ ውሳኔ እንዲፈጸምበት፡ ለደርግ፡ በጽሑፍ ያቀረቡት ማሳሰቢያ፡ እንደግፍ ተቆጥሮባቸው ይኾን?

ወይስ፡ ፀረ እግዚአብሔር በነበረው በደርግ አመራር ላይ ተቃዋሚነታቸውን በመግለጻቸው፡ ዙዋይ፡ በመኖርያ ቤታቸው እንዳሉ፡ (ራሳቸው አባ ቴዎፍሎስ በተገኙበት) በተገደሉት ጳጳስ፡ በብፁዕ አባ ሳሙኤል የአሟሟት ምሥጢር ውስጥ፡ የነበራቸው አግባብነት፡ ከእግዚአብሔር ፊት፡ ለአቤቱታ ቀርቦ ይኾን?

እኒያ ጳጳስ፡ አባ ሳሙኤል፡ የሞቱበትስ ምክንያት ምን እንደነበረ፡ በትክክል ተጣርቶ የታወቀ ነገር አለወይ? "ራሳቸውን ገደሉ!" የተባለውስ እንዴት እውነት ሊኾን ይችላል? ማንስ አረጋገጠው? ማናቸውም ጳጳስ ወይም መነኩሴ፡ እንኳንስ ሊያደርገው፡ "ያስበዋል" ተብሎ የማይገመተውን ይህን ኃጢአት ለመፈጸም፡ ከአዲስ አበባ ተነሥተው፡ ወደዚያ፡ የዙዋይ ሀገረ ስብከታቸውና በዓታቸው የሚያስኬዳቸው ምን ምክንያት ሊኖር፡ ከቶ ይችላል? ይልቅስ፡ በበዓታቸው መገኘታቸው፡ የገጠማቸውን ገድል፡ በመንፈሳዊው ኃይል ተቋቁመው፡ ድል ለማድረግ፥ ተዝቢውን የምንኵስናና የገዳማዊነት ሥርዓት ጠብቀው ለመኖር የተዘጋጁ መኾናቸውን አያረጋግጥምን?

የዓለሙ መፋረጃ!

የእግዚአብሔር እውነት: በጊዜው: ኹሉንም ትገላልጠዋለች! እጨጌ ቴዎፍሎስም: ለንስሓ ሞት በሚያበቃው: በዚያ እሥር ቤት ውስጥ በቆዩባቸው ዓመታት: ለእውነተኛዪቱ ንስሓ በቅተው እንዲገኙ: ያም ባይኾን: በደርግ የተፈጸመባቸውን: የግፍ አገዳደል: እንደንስሓ ቆጥሮላቸው: ነፍሳቸውን: በዘለዓለም መንግሥቱ: በሕይወተ ዕረፍት ይቀበልላቸው ዘንድ: የበኩሌን ጸሎት አደርግላቸዋለሁ።

ታዲያ: የዛሬዎቹ መነኩሳት፥ ጳጳሳትና እጨጌስ እንዴት ናቸው? ስለዚህ: ኹላችንም: ባለፈው ከደረሰውና ራሳቸውን: አጼ ኃይለ ሥላሴንና እጨጌ ቴዎፍሎስን ጭምር: አድብቶ ከከበባቸው አሳዛኝ ፍጻሜ ተምረን: ንስሓ እንግባ! አለዚያ: እኛንም የሚጠብቀን: ያንኑ የመሰለው: የመጨረሻው የፍርድ ቅጣት ይኾናል። እንግዲህ ወዲህ: ለንስሓ መግቢያ የሚኾን ሌላ ፋታ የሚገኝበት ዕድል ላይኖር ይችላልና!

ከቅዱሱ ኪዳን ጋር ካለን መተሣሠር የተነሣ: ዘወትር የማይለየን: የቃል ኪዳን አምላካችን: በሰፊ ቸርነቱ: የንስሓ ጊዜን በመስጠት: እስካሁን ባደረገልን ታዳጊነት: የዚያ ልዩ ጸጋው ተጠቃሚዎች ለመኾን አብቅቶናል።

\+ + +



ለቅዱሱ ኪዳን: ኢትዮጵያዊነት፥
በካቶሊካዊው: የጣልያን ጦር ፊት፥
በድፍረት መስከረው: የኾኑት መሥዋዕት፥
እኒህ እውነተኛ: አርበኛው ሰማዕት፥
ዛሬም ይጮኻሉ: ቆመው ላብነት፥
ብፁዕ አባ ጴጥሮስ: በቅዱስነት።

# ምዕራፍ ፭

## የቅዱሱ ኪዳን መለኮታዊ አማናዊነት: በእውን ያሳየው ትንግርት::

"*የእግዚአብሔር እውነት: ስለኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያዊነት: የምትሰጠው የምስክርነት ቃል*" በሚል አርእስት ተጽፎ: በእኔ በኩል ከደረሰዎ መልእክት: የዚህ መጽሐፍ: አንደኛ ክፍል: ገጽ ፷፮+ ከመጀመሪያው ዓቢይ ዐረፍተ ነገር ላይ ወስደው: እርስዎ (አቶ ናፍታሊ) የጠቀሱት ቃል: ከዚህ የሚከተሉትን: ኹለት ተነጻጻሪ ቁም ነገሮች አቅርቦ: በግልጽ ያሳያል:: እነርሱም: በአንድ ወገን: አጼ ምኒልክ: ለቅዱሱ ኪዳን የነበራቸውን ታማኝነትና አጼ ኃይለ ሥላሴ: በዚሁ ቅዱስ ኪዳን ላይ የፈጸሙትን ክህደት እያነጻጸረ ማመልከቱ ሲኾን+ በሌላ ወገን ደግሞ: ኹለቱም አጼዎች: ከእነዚያ ድርጊቶቻቸው: በየበኩላቸው የሰበሰቡት የፍሬ ዓይነት ምን እንደኾነ+ ይህም ማለት: አጼ ምኒልክ: ለታማኝነታቸው: ስለተቀበሉት ውለታና አጼ ኃይለ ሥላሴ: ለክህደታቸው: ስለከፈሉት ዋጋ: በበለጠ እያረጋገጠ ማብራራቱ ናቸው::

እርስዎ ባወሱት: በዚሁ መልእክት አማካይነት: ለኢትዮጵያውያንና ለቀረው ዓለም: እኔ: በገሃድ ያቀረብኋት *የእግዚአብሔር እውነት*: ከላይ: እርስዎ በጠቀሱት: በዚያው መልእክት ውስጥ በተጻፈው: በእኔው ቃል: "ድል ተመትታለች" ሲሉ: የራስዎን የፍርድ ውሳኔ በመስጠትና በእኔ ላይ የክስ ውቅስ ቃል በመሠንዘር: ትልቁን ጉዳይ: በደብዳቤዎ: ባጭሩ ሊዘጉት ሞክረዋል:: እንዲያውም: አንድ ቦታ ላይ: "የተቀባውን: የእርሱን አጼ: ለመዳኘት" እኔ: "እግዚአብሔር" ለመኾን እችል እንደኾነ በመጠየቅ: እንደቅዠት የሚቆጠረውን የፈጠራ አስተሳሰብዎን: ከመጨረሻው የገደል አፋፍ አድርሰው: አንከታኩተውታል::

ይህን የመሰለውን: በተንኰል የተመረዘ ትችት እንዲሠነዝሩ ያነሣሣዎ ምክንያት ምን እንደኾነ ይገባኛል:: የኢትዮጵያ ሠራዊት: ማይጨው ላይ: በፋሺስት ጣልያን ጦር: ድል የተመታው: አጼ ኃይለ ሥላሴ: ከፈጣሪያቸው: ከእግዚአብሔር ጋር: በመሓላ የተዋዋሉትን: ቅዱሱን ኪዳን ትተው: በጄኔቩ የመንግሥታት ማኅበር ቃል ኪዳን ላይ: ከመጠን ባለፈ ትውክልት በመማጸናቸው ስለመኾኑ በመግለጽ: ተገድጄ የሰጠሁት የትችት ዘገባ አይደለም? አዎን! ይኼው ነው::

ሰዎችን አማልክት በማድረግ: እነርሱን የማምለክ አባዜ የተጠናወተዎ ሰው መኾንዎ: ሳይታወቅዎ: ለእኔም የአምላክነትን ብቅዓት ሊሰጡኝ በመሞከር: ከሠነዘሩት: ከኋለኛው የክስ ውቅስዎ መገምገም ይቻላል:: እዚህ ላይ: ይህ አድራጎትዎ: ከቀድሞው የባሰ: ሌላ እጅግ የከፋ የስሕተት በደል መፈጸምዎ ቢኾንም: እንደእንግዳ ነገር ተቀጥሮ አያስደንቅ ይኾናል:: በእኔ በኩል ግን: ከላይ የተጠቀሰውን ስድ የኾነ አነጋገርዎን: የርኵሰት ብቻ ሳይኾን: በእግዚአብሔር ላይ እንደተቃጣ የስድብ ቃል አድርጌ በመቁጠር: ጊዜ ሳልሰጥ ወዲያው ያወገዝኩት መኾኔን በብርቱ ሳሳውቅዎ: በሃይማኖታዊ ቅንዓት ነው::

## የዓለሙ መፋረጃ!

በእርስዎ በኩል የተሠነዘረውን: ይህን የመሰለውን ወራዳ አስተያየት ወደጎን በመተው: በእኔ በኩል: ባጭሩ የምለው: ከዚህ የሚከተለውን ነው::- በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተብራርቶ እንደተገለጸው: በእግዚአብሔር የተቀቡትን: አጼ ኃይለ ሥላሴን የምትዳኘው: ራስዋ *የእግዚአብሔር እውነት* እንጂ: እርስዋን እንዳገለግል: የተጠራሁት እኔ ምስኪኑ፥ ደካማውና በፈጣሪ ፊት: ለምንም የማልረባው ኃጢአተኛ አይደለሁም::

አእምሮዎ ትክክለኛ ከኾነ: *የእግዚአብሔር እውነት*: "ራስዋን በራስዋ ድል *ታደርጋለች*" የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ: ከእንጉልዎ: እንዴት አሥርፀው ሊያፈልቁት እንደቻሉ: እስቲ: ከኹሉ አስቀድሞ ልጠይቅዎ? ወይስ፥ ይህች: እኔ: በመልእክተኛነት ያደረስኋት እውነት: የእግዚአብሔር "አይደለችም" ለማለት እየሞከሩ ነው? እርሷ: የእግዚአብሔርዋ እውነት ካልኾነች: *ታዲያ*: ሌላ ምን ልትኾን የምትችል ይመስልዎታል? በተዘዋዋሪ መንገድ: እኔኑ: "አንተው ፈጥረህ ያቀረብሃት ናት" ማለትዎ ይኾን? ምናልባት: እንደእርስዎ አስተሳሰብ: ይህች እውነት: ከእኔ ወይም የእኔ ብትኾን ኖሮ: በውኑ: በውስጤ ያለው: ደካማው ሰብአዊ ባሕርዬ: የእግዚአብሔር ስለኾነችው እውነት: ይህን ያህል ጨክኜና በራሴ ፈርጄ: ግልጹንና ትክክሉን: እንዲህ በድፍረት እናገር፥ እጽፍም ዘንድ: ዓቅም ኖሮት: ምንጊዜም ሊፈቅድልኝና ሊያበረታታኝ ይችል ይመስልዎታልን? አይችልም:: የዚህም ምክንያት ሌላ አይደለም፤ ይኸው ደካማው ሰብአዊው ባሕርዬ: ባሁኑ ጊዜ: በኅብረተሰቡ ዘንድ ይዞት የሚገኘውን: ከፍተኛ ሥጋዊ የክብር ሥፍራ "አጣለሁ" ብሎ ስለሚጨነቅና ሌሎቹ የተለያዩ ዓለማውያን ጥቅሞች እንዳይቀሩበት ስለሚያስብ፥ ከኅብረተሰቡም መካከል የመገለል ጠንቅ እንዳያገኘው ስለሚሠጋና ይኸው: አሁን: ከእርስዎ ሳይቀር: እየደረሰብኝ ያለውን የመሰለ: አያሌ የሰዎች የበቀል ጦር ተነሣሥቶ ከያግጣጫው እንዳይወረወርበት ስለሚፈራ ነው::

ምናልባት: እኛ እያንዳንዳችን: ስለእግዚአብሔር እውነት ለመመስከር "እምቢ" ብንል እንኳ፥ ወይም: ለእርሷ አፌ ቀላጤ ኾኖ በመናገር: ሊያገለግላት የሚፈቅድ አንድም ሰው ቢታጣ እንኳ: እርሷ ራስዋ: ስለራስዋ: የምትፈልገውን መግለጽ የምትችልበት ኃይልና ሥልጣን እንዳላት አያውቁምን? *የእግዚአብሔር እውነት*: "ሆሣዕና በአርያም!" በሚለው: በደቀ መዛሙርቱና በሕፃናት የምስጋና ቃል: በታላቅ የሕዝብ ጉባዔ መካከል: በከፍተኛ ድምፅ ስትወደስ: አይሁድ ፈሪሳውያን ሰምተው: *"መምህር ሆይ! እንዲህ እንዳይሉ: ደቀ መዛሙርትህን ገሥፃቸው እንጂ!"* ባሉት ጊዜ: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጣቸውን መልስ ያስታውሱ! ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ: አግባብ ያላቸውን ቃላት ከጠቀሰላቸው በኋላ: ራሱ *የእግዚአብሔር እውነት* የኾነው ጌታችን: የመለሰላቸው ቃል: *"እነዚህ ዝም ቢሉ: እላችኋለሁ: ድንጋዮች ይጮኻሉ!"* የሚል ነበር::[፲፰]

አሁን ደግሞ: ወደተነሣንበት: ወደራሳችን ጉዳይ መለስ ስንል: *የእግዚአብሔር እውነት*: እንደፀሐይ የሚያበሩት እውን ሥራዎቿ በተከሠቱባቸው: በአድዋና በማይጨው አውድማዎች: ራስዋ እንደተናገረች እንመለከታለን:: ይኸውም: የኢትዮጵያ ቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ: ዓድዋ ላይ በተጐናፀፈው ድልና የአጼ ኃይለ ሥላሴ ሠራዊት: ማይጨው ላይ በደረሰበት ሽንፈት አማካይነት ማለት ነው::

*ታዲያ*፥ በእግዚአብሔር የእውነት ብርሃን ካልኾነ በቀር፡ ያው አንዱ የቅዱሱ ኪዳን ቤተ ሕዝብ፡ ያንኑ፡ አንዱን ባዕድ ወራሪ "ድል አድራጊ ወይም በእርሱ ድል ተመቺ ኾነ!" ብሎ እንዴት አድርጎ በትክክል ማስረዳት ይቻላል?

እርስዎ፡ በእግዚአብሔር እውነት ላይ ባለዎ፡ ክህደት፥ ወይም አጼ ኃይለ ሥላሴን፡ ከተጠያቂነት ነጻ ለማድረግ በሚያካሂዱት ጥረት፥ ወይም በሌላ በማናቸውም ዓይነት የተንኰል ዘዴዎ፡ *የእግዚአብሔር እውነት* "ልትሸነፍ ትችላለች!" ብለው በአሳብዎ በማውጠንጠን የሚያደርጉት የማስመሰል ሙከራ ቢኖር፡ ይህ ሙከራዎ፡ ከንቱና ፍሬቢስ ብቻ ሳይኾን፡ ፍጻሜው፡ ለዘለዓለማዊ ኵነኔ የተዳረገ ነው። ከዚህ፡ እርስዎ ካሰቡት ግብ ለመድረስ፡ የእርስዎ ቀርቶ፡ እጅግ የበረታው፡ የዲያብሎስ የሓሰት ኃይል፡ ወይም፡ ሰይጣናዊ ዕቅዶቹ እንኳ፡ ምንጊዜም፡ ከዓቅመቢስነትና ተጨናግፎ ከመቅረት ያለፈ ዕድል አልነበራቸውም፤ አይኖራቸውምም።

*ለመኾኑ*፡ ባሁኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ ውስጥ፡ በእውን እየተካኼደ ባለው ኹኔታና በኢትዮጵያውያን ሕይወት ላይ እየተፈጸመ በሚታየው ድርጊት አማካይነት፡ *የእግዚአብሔር እውነት*፡ ያለማቋረጥ እየተናገረች መኾኗን እንዴት በማስተዋል መመልከት አቃተዎ?

የደብዳቤዎ አጠቃላይ ይዘት፡ ምሥጢራዊ ዓላማዎን ከግብ በማድረሱ ተግባር ላይ ፈጽሞ ያተኮረ መኾኑን ተገንዝቤዋለሁ። እርሱም፡ *የእግዚአብሔር እውነት*፡ ባላት መለኮታዊ ኃይል፡ የፈጸመችውንና የምታካኺደውን ድርጊት ኹሉ፡ ከንቱ ለማድረግና ዋጋ ለማሳጣት መሞከር፥ ከዚያ በኋላ፡ በአሁኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ ላይ የሚታየውን፡ ይህን ታላቅ ጥፋት ያስከተለውን፡ ያን፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ የወደቀ ሥርዓት፡ ቅሬቱን መልሶ ማቋቋም ነው።

ይህ ደግሞ፡ በእርስዎ በኩል፡ በጽኑ ሊያስቡበትና ተጸጽተው ንስሓ ሊገቡበት የሚገባ፡ ሌላው የተሳሳተ ግምትዎና ከባድ የወንጀል ድርጊትዎ ይኾናል፤ አለዚያ፡ ይኸው የእምቢተኝነት ድርጊትዎ፡ ከቀድሞው ይልቅ የሚበረታውን መለኮታዊ የቅጣት ቁጣ፡ እንደገና ቀስቅሶ በበለጠ እንዲቀጥል ሊያደርግ ይችላል።

## ኢትዮጵያ፡ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ስትፋረድ!

ኢትዮጵያ፡ ቀደም ብሎ፡ በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም.፥ እንደገና፡ ከዓርባ ዓመታት በኋላ ደግሞ፡ በ፲፱፻፷፰ ዓ. ም. ምን እንደደረሰባት፡ እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን፥ እንዲሁም፡ በዓለም የሚኖሩ አስተዋዮች የኾኑ ሕዝቦች ኹሉ፡ አንድ በአንድ በትክክል ያውቁታል። በእግዚአብሔር እውነት ተረጋግጦ የተገለጸውንም እውነታ መሠረት በማድረግ፡ ለእነዚያ ለደረሱትና እየደረሱ ላሉት ኹኔታዎች፡ መነሻ የነበሩት ምክንያቶችም፡ ምን እንደነበሩና ምን እንደኾኑ ተረድተውታል።

**የዓለሙ መፋረጃ!**

እርስዎ ግን፡ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. የተፈጸመውን ጥፋት ያደረሱትን ወገኖች፡ "ከበደሉ ነጻ አደርጋቸዋለሁ!" ብለው በሚሞክሩበት ጊዜ፡ ዛሬ እየተካኼዱ የሚገኙትን፡ ተጨባጭ ኹነታዎች ለመመልከት የተሣነዎ መኾኑን ዘንግተውታል። እነዚህም ኹነታዎች፡ የእግዚአብሔርን እውነት ለመቀበል፡ ራስዎን በራስዎ፡ ለማሳመን ባለመቻልዎ፡ ራስዎን እንዲወቅሱ የሚያስገድዱዎት እውነታዎች ናቸው። እነርሱም፡ እኒሁልዎ!

አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ለጀኔቫው የመንግሥታት ማኀበር ቃል ኪዳን ቢታማኝነት በመገዛት፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ የፈጸሙትን፡ ያንኑ የክህደትና የርኵሰት በደል፡ የኋላ ኋላ ቆይተው፡ በኒው ዮርኩ፡ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፥ እንዲሁም፡ የዚሁ ድርጅት፡ የበላይ ጠባቂና የዓለም ኃያል መንግሥት በኾነው፡ በአሜሪካ ላይ በመታመን፥ ይህንኑም፡ በቃል ኪዳን በማጽናት፡ እንዴት አድርገው፡ በተመሳሳይ መልኩ፡ ባሁኑ ዘመን፡ እንደገና እንደደገሙት፡ እስቲ፡ ራስዎ ይመልከቱት!

ከዚህ፡ ከምንነጋገርበት አጠቃላይ አርእስተ ጉዳይ ጋር ተያይዘው በተወሱት፡ በኹሉም ዓይነት ኹኔታዎች ውስጥ፡ በይበልጥ፡ ቁምነገር ኾኖ የተነሣው ነጥብ፡ በድርጊት የመፈጸማቸው ነገር ሳይኾን፡ የእነርሱ መነሻ የኾነው፡ የሕሊናዊው ውሳኔ ነገር ነው። በዚህ መሠረት፡ ከላይ በተጠቀሱት፡ በኹለቱም ጊዜያት የተገኘው ውጤት አረጋግጦ እንዳሳየው፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ፡ የኒው ዮርኩን ድርጅት በሚመለከት የነበራቸው ሕሊናዊ ውሳኔ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ እምነት ከማጣታቸው የተነሣ፡ ቀደም ብለው ከፈጸሙት፡ ከጀኔቫው ድርጊት ጋር፡ ፍጹም ተመሳሳይ እንጂ፡ ከዚያ የተለየ አልነበረም።

ይህም፡ ባጭሩ፡ ኢትዮጵያውያን፡ በዘመኑ፡ አጼያቸው በኾኑት፡ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መሪነት፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ የነበራቸውን ፍጹም እምነትና ሙሉ ትውክልት የማጣት አቋማቸውን፡ ለኹለተኛ ጊዜ አጽንተው ቀጠሉበት ማለት ነው።

የኢትዮጵያ የቃል ኪዳን አምላኳ የኾነው እግዚአብሔር ደግሞ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ተቀበልነውም፡ አልተቀበልነውም፥ ወደድንም፡ ጠላንም፡ ከቅዱሱ ኪዳን የተነሣ፡ እነዚህ፡ የዘለዓለማዊው ውል፡ ዋና አካል የኾኑት፡ ኹለቱ መንፈሳውያን ኃይላት፡ ማለትም፡ *በእርሱ ላይ ፍጹም እምነትንና ሙሉ ትውክልትን አጽንቶ የመኖርን አቋም፡* በሕይወት ካለው አጼና እርሱ፡ በተጠሪነት ከሚያስተዳድረው ትውልድ፡ ምንጊዜም የሚጠይቀው ተቀዳሚ ግዳጅ ነው። ይህም ግዳጅ፡ አምላካዊ ጸጋ ኾኖ፡ ከፈጣሪው የነጻነት አስተዳደር በቀር፡ በአንድም ሰብአዊ ሥልጣን ሥር ካልተገዛው፡ ከቅዱሱ ኪዳን ሕዝቧ ጋር፡ የማይገሠሠውንና በሉዓላዊነት የከበረውን፡ የኢትዮጵያን፡ ኹለንተናዊ ህልውና፡ በመለኮታዊው ኃይል፡ ከማናቸውም ዓይነት፡ የጠላት ተንኰል፡ በምንም ሳይነካ፡ እንዳለ ተጠብቆ ይኖር ዘንድ አስችሏል።

እስቲ ራስዎ ልዩነቱን ይመልከቱት! በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመን፡ ኢትዮጵያ፡ የማናቸውም ዓለም አቀፍ ድርጅት፡ ወይም የመንግሥታት ማኅበር አባል አልነበረችም። በተለይ፡ በአድዋው ጦርነት ጊዜ፡ በልማድ የቀድሞ ወዳጆቿ ይባሉ የነበሩት፡ ጥቂቶቹ የአውሮጳ አገሮች እንኳ፡ ጨርሰው ርቀዋት እንደነበረ ይታወቃል። የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ረድኤት ከሚያስገኝላት፡ ከቅዱሱ ኪዳን በቀር፡ የምትታመንበትና የምትደገፍበት፡ ምንም ዓይነት አለኝታ አልነበራትም።

ወራሪ ጠላቷን፡ ጣልያንን፡ ተከላክላ ለመመለስ፡ በቂ የኾነ የጦር መሣሪያ ሳይኖራት፡ ከዘመኑ፡ የምድር ልዕለ ኃያላን መካከል አንዱ የነበረውን፡ ያን፡ ወራሪ ሠራዊት፡ ተቋቁማና ድል መትታ፡ የነጻነት ህልውናዋን ለመቀጠል በቃታለች።

ታዲያ! ይህ፡ እንዴት ሊኾን ቻለ? አዎን! ራስዋ፡ ቅድስት እናቱ፡ ድንግል ማርያም የኾነችው ኢትዮጵያ፡ ከልጆቿ ጋር፡ ራሱ፡ ልጇ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ባወቀውና በተቀበለው፡ በፍጹም እምነትና በሙሉ ትውክልት ኾና፡ የእርሱን፡ የቃል ኪዳን አምላኳን እርዳታ ስለጠየቀች፡ የልዕለ ኃያላን ርእሰ ኃያል የኾነው፡ ስማያዊው አሸናፊ ጌታ እግዚአብሔር፡ በቅዱሱ ኪዳን የተመዘገበውን መለኮታዊ ግዳጁን በመከተል፡ ወዲያው ፈጥኖ ደረሰላት! በማያወላውል ይዞታም፡ ለእርሷ ጋሻና ጦር ኾኖ፡ የትድግና ተግባሩን፡ በኢትዮጵያና በልጆቿ ድል አድራጊነት ፈጸመ!

አንድ አገር፡ በተወረረ ጊዜ፡ ወይም አንዳች ችግር በደረሰበት ጊዜ፡ አባል የኾነበት ድርጅት ካልደረሰለት፡ ያ አገር፡ በማናቸውም ዓይነት በይነመንግሥታት (international ኢንተርናሽናል) ድርጅት ውስጥ አባል መኾኑ፡ ከቶ ምን ይረባዋል? ምን ይጠቅመዋል? የውሉ ግዴታ፡ በሚፈለግበት ጊዜ፡ በሥራ ላይ ውሎ የሚፈጸም ካልኾነ በቀር፤ የጽሑፍ ኪዳን ተዋዋይ መኾን፡ ከቶ ምን ዋጋ አለው?

ጣልያን፡ በዚያን ጊዜ ጸንቶ የነበረውን የቃል ኪዳን ውል፡ ገሃድ በኾነ ንቀትና ድፍረት፡ አፍርሳ፡ በኢትዮጵያ ላይ የዕብሪት ወረራዋን ስታካኼድ፡ ያ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በፍጹም አለኝታነቱ፡ ፍጹም እምነታቸውን ጥለውበት የነበረው፡ የጀኔቡ የመንግሥታት ማኅበር የት ነበር?

## ኢትዮጵያ፡<br>ያሴሩባትን የዓለም መንግሥታት<br>ስትፋረድ!

አሁን በዘመናችን ደግሞ፡ በባዕዳን ኃያላን መንግሥታት ቀስቃሽነትና ተገንነት፡ የክህደትና የዓመፅ እንቅስቃሴ፡ ኢትዮጵያን እንደማዕበል ባጥለቀለቃት ጊዜ፥ ራሳቸው፡ አጼ ኃይለ ሥላሴም፡ የበይነመንግሥታቱ ሴራ፡ ሰለባ ኾነው በወደቁ ጊዜ፡ እርሳቸው፡ በከፍተኛ ታማኝነትና ባልተቋረጠ ጽናት፡ ያን ያህል የተማጸኑትና ያመኑበት፡ የኒው ዮርኩ፡ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፡ ከቃል ኪዳኑ ጋር ወዴት ነበር?

ተደጋግሞ ለደረሰው፡ ለኢትዮጵያ ውድቀት፥ መከፋፈልና በመካሄድ ላይ ላለው መገነጣጠል፥ እንዲሁም፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴና የዘመናቸው የሥልጣን ተካፋዮች በነበሩት ኢትዮጵያውያን ላይ ለተፈጸመው፡ አረመኔያዊ አያያዝና አገዳደል፡ የቀድሞው፡ የመንግሥታት ማኅበርና ዛሬ ያለው፡ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፡ መሣሪያ አልኾኑምወይ? ኹለቱም አቋሞች፡ በምሥጢር፡ ከኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር ወግነውና ግብረአበር ኾነው ለመሥራት አላሴሩባትምን? ከኋላዋስ ሸምቀው፡ ጀርባዋን በተሳለ ሠይፍ አልወጓትምን?

## የዓለሙ መፋረጃ!

ለዚህም፡ ቀደም ብሉ፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለተፈጸመው ድርጊት፡ የሚቀርበውን ማብራሪያ፡ ለመጽሐፉ የመጨረሻ ምዕራፍ አቀይቼ፡ ከላይ ለተሰጠው አጠቃላይ አስተያየት፡ መግለጫና ማጠናከሪያ የሚኾኑ፡ በቅርቡ ደርሶ የነበረ፡ አንድ እውነታ፥ ዛሬም እየተካኼደ የሚገኝ፡ ሌላ ትንግርት እነሆ!

በቅድሚያ፡ እስቲ፡ በቅርቡ ደርሶ ስለነበረው እውነታ፡ እናውጋ! የአሜሪካ ዩናይትድ ስቴትስ እና የተባበሩት መንግሥታት ማኅበር፡ ኢትዮጵያ የምትገኝበትን፡ አደገኛና አሥጊ ኹኔታ እያወቁና እያዩ፡ ኸን ብለው፡ እርሷን አግልለው በራቋትና ለጠላቶቿም አጋልጠውና አሳልፈው በሰጧት ጊዜ፡ ጎረቤቷ ሶማሌ፡ በአጋጣሚው በመጠቀም፡ በ፲፱፻፷፱ ዓ. ም. በኢትዮጵያ ላይ ግልጽ የኾነ ሰፊ ወረራን ማካኼድ ጀመረች፡፡ እነርሱም፡ ከወራሪዋ ሱማሌና ከቃል ኪዳን ተባባሪዎቿ የእስልምና አገሮች ጋር ወገኑ፡፡ በዚህ ጊዜ፡ የኀያላን ኀያል የኾነው፡ የኢትዮጵያ አምላክ፡ እግዚአብሔር፡ ከቅዱሱ ኪዳን የተነሣ፡ ሕዝቧን ለመጠበቅ ሲል፡ ጣልቃ ገብቶ፡ የፈጸመውን የትድግና (የማዳን) ሥራውን እንመልከት!

በመጀመሪያ፡ የኢትዮጵያ ዋና ቀንደኛ ጠላት የኾነውንና ሶቪዬት ዩኒየን ይባል የነበረውን የመስኮብን እግዚአብሔር-አልባ የጋርዮሽ (communist ኮሚዩኒስት) መንግሥት ኃይል፡ ለወደፊት የመስፋፋት ዕቅዱና ስልቱ፡ ቁልፍ የጦር መደቡ አድርጓት ከነበረችው ከሶማሌ ምድር አስገድዶ አወጣው! ቀጥሉ፡ ወደኢትዮጵያ ምድር ጎትቶ አግብቶ፡ ቀድሞ፡ የቃል ኪዳን ጦር ጓደኛው የነበረችውን፥ ዛሬ ግን ጠላቱ የኾነችውን፥ እርሱ ራሱ፡ በጦር መሣሪያ፡ ከእግር ጥፍርዋ እስከራስ ጠጉርዋ ያስታጠቃትን ሶማሌን፡ መልሶ እንዲወጋት አደረገው!

በመለኮታዊው ዳኝነትና ኃይል፡ የኢትዮጵያ፡ ኹለንተናዊ የልዕልና ህልውናዋ፡ በምንም ሳይነካ፡ እንዲህ ተጠብቆ ሲቀጥል፥ ሶማሌና ሶቪዬት ዩኒየን ግን፡ መላው ዓለም በዓይኖቹ ብሌን፡ በገሃድ እያየ፡ ተንኮታኩተው ሲወዳድቁና ሲፈራርሱ ተመለከተ!

ታዲያ! በዚህ ድንቅ በኾነው መለኮታዊ ድርጊት፡ ከዚህ የሚከተለውና እንዲህ የሚለው የትንቢት ቃል ተፈጸመ አይደለምን? "ጌታ እግዚአብሔር፡ እንዲህ ይላል፡- 'የምሳሕና የቶቤል ዋነኛ አለቃ፡ ጎግ ሆይ! እነሆ እኔ፡ በአንተ ላይ ነኝ! እመልስሃማለሁ፤ በመንጋጋህም፡ ልጓም አገባብሃለሁ፤ አንተንና ሠራዊትህንም ኹሉ፥ ፈረሰኞችንና ፈረሰኞችን፥ የጦር ልብስ የለበሱትን ኹሉ፥ ጋሻና ራስ ቍር፥ ሰይፍንም የያዙትን ኹሉ፤ ታላቁን ወገን አወጣለሁ! ፋርስንና ኢትዮጵያን፥ ፉጥንም፥ ከእነርሱ ጋር፡ ጋሻና የራስ ቍርን የለበሱትን ኹሉ፥ ጋሜርንና ጭፍሮቹን ኹሉ፥ በሰሜን ዳርቻም ያለውን፡ የቴርጋማን ቤትና ጭፍሮቹን ኹሉ፥ ብዙዎቹንም ሕዝቦች ከአንተ ጋር አወጣለሁ!' ...ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- 'ዋይ በሉ! ለቀኑ ወዮ! ቀኑ ቅርብ ነው፤ የእግዚአብሔር ቀን ቅርብ ነው፤ የደመና ቀን፥ የአሕዛብም ጊዜ ይኾናል፡፡ ሠይፍ በግብፅ ላይ ይመጣል! ሁከትም በኢትዮጵያ ይኾናል! የተገደሉትም፥ በግብፅ ውስጥ ይወድቃሉ፤ ብዛትዋንም ይወስዳሉ፤ መሠረትዋም ይፈርሳል፡፡ ኢትዮጵያና ፉጥ፥ ሉድም፥ የተደባለቀም ሕዝብ ኹሉ፥ ኩብም፥ ቃል ኪዳን የገባችው ምድር ልጆች፡ ከእነርሱ ጋር በሠይፍ ይወድቃሉ፡፡'"[፲፫]

መለኮታዊ ዳኝነቱንና ፍርዱን፡ እንዲህ፡ በሶቪዬት ዩኒየንና በሶማሌ ላይ ያሳየው፡ የኢትዮጵያ የቃል ኪዳን አምላክ፡ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው፡ ኢትዮጵያን ክደው፡ በውድቀቷ በተባበሩት፡ በሌሎቹ ላይ ደግሞ፡ በእውነተኛ ዳኝነቱ የሚሰጠውን ፍርድ፡ ኢትዮጵያና እውነተኞች ልጆቿ፡ በሃይማኖታዊ ተስፋና ትሕትና ይጠብቃሉ።

## ኢትዮጵያ፡ ኤርትራን በሚመለከት፡ ደመኞቿን መንግሥታትና የትግራይ ልጆቿን ስትፋረድ!

አሁን ደግሞ፡ ዛሬ እየተካኼደ ስላለው ትንግርት እንነጋገር! የዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ዕትም በኾነው በእንግሊዝኛው ዝግጅት ውስጥ ሠፍሮ የነበረው፡ ከዚህ በላይ የተገለጸውና በመንፈሳዊ ትሕትና ሲጠበቅ የቆየው፡ ሃይማኖታዊ ተስፋ፡ ደርሶ የታየበት ኹኔታ፡ እነሆ፡ ተፈጥሮ ተገኘ። ይህም፡ የባዕዳኑ ዕቅድ ውጤት የኾነው፡ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል የተካኼደው ጦርነት ነው። ይኸው አሳዛኝና አሠቃቂ ድርጊት ተጀምሮ በተፈጸመበት ጊዜ፡ ይህ፡ ኢትዮጵያኛው ዕትም ሊጠናቀቅ ስለቻለ፡ የኢትዮጵያ የቃል ኪዳን አምላክ፡ በቅዱሱ ኪዳን ውለታው መሠረት፡ አሁን ደግሞ እንደገና የከሠተውን፡ ይህንኑ የትድግናውን ተአምር እዚህ ላይ ማሥፈር ግድ ኾኗል።

ይኸውም፡ *"እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን፡ ሰው አይለየው!"* የሚለውን አምላካዊ ቃል፡ በድፍረት በመተላለፍ፡ የተባበሩት መንግሥታት ማኅበር፥ የአሜሪካ ዩናይትድ ስቴትስና አውሮጳውያን ግብረአበሮቿ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታቸውን ክደው፡ በዓመፅ በተነሡ የኢትዮጵያ ልጆች መሣሪያነት፡ የኢትዮጵያን አንድነት ለማፈራረስ በመሞከር የፈጸሙትን ገሃድ የኾነ አሳዛኝና የነውር ሥራ የሚመለከተው ነው። ይህንኑም፡ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይኾኑ፡ መላው የዓለም ሕዝቦች ጭምር፡ በይፋ ያውቁታል።

እስቲ! በዚህ ረገድ ያለውን ዝክረ ነገር ባጭር አገላለጽ ለማጠቃለል ልሞክር! ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፡ በቅኝ ገዢዎች፡ "ኤርትራ" የሚል ስም የወጣላቸው፡ የኢትዮጵያ ባሕር ነጋሽ ክልል ነዋሪዎች የኾኑት ኢትዮጵያውያን፡ በእነዚሁ ቅኝ ገዢዎች ወረራ፡ ከእናት አገራቸውና ወገኖቻቸው ተነጥለው፡ ለአያሌ ዓመታት በባርነት እንዲኖሩ መደረጉ ይታወሳል። ከዚህ በኋላ፡ የኢትዮጵያውያን የቃል ኪዳን አምላክ የኾነው እግዚአብሔር፡ በትክክለኛ ዳኝነቱ ፈርዶ፡ በዘመኑ ዕብሪተኞች፥ አጥቂዎችና ግፈኞች ላይ በቅጣት መልክ ያወረደው፡ የኹለተኛው የዓለም ጦርነት መዓት፡ የቁጣ ተልእኮውን በሚገባ ካከናወነ በኋላ፡ የጦርነቱ ፍጻሜና ውጤቱ አስገድዷቸው፡ ራሳቸው፡ የተባበሩት መንግሥታት ማኅበር፥ የአሜሪካ ዩናይትድ ስቴትስና አውሮጳውያን ግብረአበሮቿ፡ ራሳቸው፡ የነገሩ ባለቤቶችና ዳኞች፥ ተከራካሪዎችና መርማሪዎች፥ አጥኚዎችና ነገረ ሠሪዎች፥ ወሳኞችና አስፈጻሚዎች ኾነው፡ የኤርትራን ጉዳይ ቀሰቀሱት።

የዓለሙ መፋረጃ!

እኒሁ፡ ኤርትራውያን የተባሉት፡ የባሕር ነጋሽ ነዋሪዎች የኾኑት ኢትዮጵያውያን፡ አንድ ሕዝብ ሊቋቋመው የማይቻለውን፡ የባዕዳንን ፈተናና ወጥመድ፡ በሃይማኖታዊ ታማኝነትና ጀግንነት ተቋቁመውና አልፈው፡ በተንኰል ከቀረቡላቸው ጥያቄዎች መካከል፡ "እኛ፡ ከእናት አገራችን፡ ከኢትዮጵያና ከወገኖቻችን ኢትዮጵያውያን ጋር መዋሃድ እንፈልጋለን" የሚለውን የምርጫ ቃል፡ በቆራጥነት፡ በተደጋጋሚ ሰጡ።

እንግዲህ፡ በዚህ ሕዝባዊ ውሳኔ መሠረት፡ ይህን የኤርትራን፡ ከኢትዮጵያ ጋር የመዋሀድ ሥርዓት፡ ከውጥኑ አንሥቶ እስከፍጻሜው ድረስ፡ በሰላማዊ መንገድ መርተው ያደረሱት፡ እኒሁ፡ የተባበሩት መንግሥታት ማኅበር፥ የአሜሪካ ዩናይትድ ስቴትስና ግብረአበሮቿ መኾናቸው፡ በግልጽ የታወቀ እውነታ ነው። ታዲያ፥ በዚህ መልክ የፈጸሙትን የራሳቸውን ሥራ፡ ዕድሜው አጭር በኾነ ጊዜ ውስጥ፡ እንደምን አድርገው፡ መልሰው ሊያፈራርሱት ፈለጉ? ማለትም፡ ልጅቱ ኤርትራ፡ ለአያሌ ዓመታት የቆየ ናፍቆቷን እንኳ ተወጥታ፡ የእናቷን ፍቅር ገና ሳትጠግብ፡ እንደአንድ አካል ከሚቆጠረው፡ ከእናቷ ዕቅፍ እንደገና ተገንጥላ፡ እንዴት እንድትለይ ያደርጋሉ? ይህ አድራጎታቸው፡ በኢትዮጵያ ላይ ብቻ ሳይኾን፡ ከቅዱሱ ኪዳን የተነሣ፡ በእግዚአብሔርም ላይ እንደተፈጸመ ታላቅ ኃጢአት የሚቆጠር ኾኖባቸዋል።

በሌላ መልኩ ደግሞ፡ የኢትዮጵያንና የኤርትራን ውህደት፡ በገንዘባቸው፥ በኃይላቸውና በጥበባቸው የሚመኩትን፡ የዓለም ኃያላንን፡ ሽንገላ፥ ጦርና ተንኰል በመቋቋም፡ አንዲት ጥይት ሳትተኰስ፡ እንዲህ በሰላም እንዲፈጸም ለማድረግ መቻል፡ የቅዱሱ ኪዳን ፍሬ እንጂ፡ የሌላ የምንም ዓይነት ግብር ውጤት ነው ሊባል ከቶ አይቻልም።

ነገር ግን፡ ከውህደቱ በኋላ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ አመራር፥ በተለይም፡ ይባስ፡ በደርግ ዘመን፡ በዚህ በኩል ይካኼድና ይፈጸም የነበረው፡ የኃይል ድርጊት ኹሉ፡ ኢትዮጵያ የቆመችበትን፡ የቅዱሱን ኪዳን ምግባር የሚጻረር ስለነበረ፡ የኤርትራ ጉዳይ፡ ያን ከመሰለ አሳዛኝ የውድቀት ፍጻሜ ላይ መድረሱ አያስደንቅም። ለዚያም ድርጊት፡ አጼ ኃይለ ሥላሴና ተባባሪዎቻቸው፡ ከነአመራራቸው፡ የደረሰባቸውንና የከፈሉትን ዋጋ፡ በዚህ ድርሰት ውስጥ፡ በየቦታው እንደታተተው፡ ይህ፡ የኢትዮጵያ ትውልድና የዓለም ሕዝብ፡ የዓይን ምስክር በመኾን ተመልክቶታል።

የኢትዮጵያና የኤርትራ ውህደት፡ ያን በመሰለ መልክ፡ በሰላማዊ መንገድ መፈጸሙ፡ መለኮታዊው እጅ በመላው የጉዳዩ ኺደት ውስጥ ያልተለየ መኾኑን ያመለክታል። ይህም፡ ከቅዱሱ ኪዳን የተነሣ መኾኑ ሊታበል አይቻልም። እንግዲህ፡ እግዚአብሔር፡ ኢትዮጵያንና ኤርትራን አንድ ያደረጋቸው፡ ቀድሞ፡ በመልከ ጼዴቅ፥ ኋላም፡ በመጨረሻ፡ በአማናዊው መልከ ጼዴቅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ታትሞ በጸናው፡ በቅዱሱ ቃል ኪዳን ስለኾነ፡ ይህን አንድነት፡ ከቶ ማን ሊያፈርሰው ይችላል? ይህም ቃል ኪዳን፡ እግዚአብሔር፡ በአንዲት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩትን ጐሣዎችና ብሔሮች ብቻ ሳይኾን፡ በአጠቃላይ፡ በመላዋ ዓለም፡ በምድር ላይ የሚርመሰመሱትን፡ የሴምን፥ የካምንና የያፌትን ነገዶች፡ እንደገና መልሶ አዋህዶ፡ አንድ የሚያደርግበት፡ የቸርነቱ ሥራ ነው።

እግዚአብሔር: በዚች ምድር ላይ ይኖሩ ዘንድ ለፈጠራቸው የሰው ልጆች: መልካም ሕይወት እንዲኾንላቸው: በቅዱሱ ኪዳን መሥርቶ፥ አቁሞና ደምድሞ: ለምርጫ ያቀረበላቸው: ይህ: እውነተኛው ኢትዮጵያዊነት: ዛሬ "ኢትዮጵያ" ተብላ በምትታወቀው አገር ተወስነው: ከየብሔሩና ከየጐሣው፥ ከየቋንቋውና ከየአኀ ኰቱ ወጥተውና ተዋህደው: የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ለመኾን ለበቁት: "ዐምሐራ" ወይም "ኢትዮጵያውያን" ለተባሉት ወገኖች ብቻ ሳይኾን: በምድር ላይ: በየአገሩ የሚኖሩት: የተለያየ ነገድና ዘር፥ ሃይማኖትና ባህል ያላቸው: የመላው ዓለም ሕዝቦች ኹሉ: አንድ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲኾኑበት የተሰጠ የመጨረሻው ጸጋ ስለኾነ: ወደዚህ ግብ የሚያደርሰው: መለኮታዊው ዕቅድ: በዚህ መልክ: በሥራ ላይ የመዋሉ ኺደት: እንዲህ እያለ ይቀጥላል እንጂ አይቆምም::

በዚህ መሠረት: እግዚአብሔር: በቅዱሱ ኪዳን አማካይነት: መልሶ አንድ ያደረጋቸውን እናትና ልጅ: ማለትም: ኢትዮጵያንና ኤርትራን: እንደገና ለመለያየት የተደረገው ሙከራ: ያደረሰውን ጥፋትና ያስገኘውን ውጤት እስቲ: እንመልከት! ይህም: *የእግዚአብሔር እውነት*: በትክክለኛ ዳኝነቷ የሰጠችውና ያስፈጸመችው ፍርድ ነው::

አንደኛ:- የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታቸውን ክደውና በዓመፅ ተነሣሥተው: ለተባበሩት መንግሥታት ማኅበር፥ ለአሜሪካ ዩናይትድ ስቴትስና ለአውሮጳ ግብረአበሮቿ፥ የኢትዮጵያ ደመኛ ጠላት ለኾነችው ለጣልያን ሳይቀር: መሣሪያ በመኾን: በወዳጅነትና በስምምነት አንድ ኾነው: ያን መለያየትና መከፋፈል: የፈጸሙትና ያስፈጸሙት: እኒያው: የኢትዮጵያ ልጆች: መልሰው: ብዛቱ: በመቶ ሺሆች የሚቆጠር የወንድማማችና የእህትማማች ሰላማዊ ሕይወት የወደመበትን፥ ነፍሳዊ ህልውናውም የተወገደበትን: የእርስ በርስ ጦርነት ለማካኼድ: ራሳቸው ምክንያት ኾኑ:: ይህም: በአገርና በመንግሥት ደረጃ: በገንዘብና በንብረት፥ በጊዜና በጉልበት፥ በእውቀትና በዝምድናው በኩል የደረሰው ታላቅ ጉዳት: ከሒሳብ ውስጥ ሳይገባ: ወደጐን ተትቶ ሲገመገም ነው:: ለጦርነቱ መነሣት ምክንያት የኾኑት: እኒሁ የኢትዮጵያ ልጆች: ያለውልውል ይሰሟቸውና በጭፍን ይከተሏቸው የነበሩትን: የነዚያን ባዕዳን ጌቶች መመሪያ፥ ምክርና ሽምግልና ሳይቀር: "አንቀበልም!" ብለው: እልቂቱ እንዲቀጥል ያደረጉት: ነገሩ: ቅዱሱን ኪዳን በመፃረር: ለፈጸሙት: የክህደታቸውና የዓመፃቸው ዋጋ ኾኖ: በኢትዮጵያውያን ላይ ለቅጣት: ከእግዚአብሔር ታዝዞ የመጣ በመኾኑና ሊመልሱት ባለመቻላቸው መኾኑን መገንዘብ: ለማንም አያዳግትም::

በዚህ ረገድ ስለደረሰው አሠቃቂ እልቂት: በኀዘን ተውጠው የሚያለቅሱት: ዛሬ: በሕይወተ ሥጋ ያሉት: እውነተኞች ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይኾኑ: በሕይወተ ነፍስ ኾነው: ይህን ኹሉ የመርገም ውጤት የሚመለከቱት: ጭምር መኾናቸው: ግልጽ ነው:: ከእነዚህ መካከል: የእነአጼ ዮሐንስ፥ የእነራስ አሉላ፥ የእነዘርዓይ ድረስ፥ የእነራስ ኪዳነ ማርያም ገብረ መስቀል፥ የእነደጃዝማች በየነ ባራኪ፥ የእነብላቴን ጌታ ሎሬንሶ ታእዛዝ፥ የእነብላቴን ጌታ ኤፍሬም ተወልደ መድኅን፥ የእነደጃዝማች ተድላ ባይሩ፥ የእነንቡረ እድ ድሜጥሮስ ገብረማርያም፥ የእነደጃዝማች ሓረጎት ዓባይ፥ የእነቢትወደድ አስፍሓ ወልደ ሚካኤል፥ የእነከንቲባ ስምዖን፥ የእነሼህ አል ዐሚን ስም ጐልቶ ይታያል::

የዓለሙ መፋረጃ!

እኒህ ነበሩ፡ በሕዝባዊ አደባባይ ላይ ባሳዩት ተውኔታዊ ዝግጅት፡ ከጥገቷ እናቷ፡ በግድ ተነጥላ፡ የምትጮኽውን ጥጃ፡ የታሠረችበትን ገመድ በመቁረጥ፡ ወደምትጮኸው እናቷ ሮጣ ኼዳ፡ ጡቷን እንድትጠባ ያደረጉት:: ይህም የኾነው፡ በባዕዳን ቅኝ ገዢዎች ሸርና ግፍ፡ ከእናቷ አካል ተገንጥላ እንድትኖር የተገደደችው ኤርትራ፡ ወደነበረችበት ኹለንተናዋ፡ በውህደት እንድትመለስ፡ "የተፈጥሮ ግዴታም ነው" የሚለውን፡ መልእክት፡ ለዚሁ ጉዳይ ለተላኩት፡ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መርማሪዎች፡ ያለምንም ተጨማሪ ቃል፡ በቀላሉ በሚያሳምን መንገድ ለማስተላለፍ ሲሉ እንደነበረ ይታወሳል::

ከእነርሱም ጋር፡ በሰልፉ ትግል ላይ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታቸው፡ አገራዊና ወገናዊ የፍቅር እሳት፡ ነበልባሉ፡ በውስጣቸው እየነደደ፥ ብርሃኑም እየመራቸው፡ ሕይወታቸውን፡ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ አንድነት ሳይቀር፡ መሥዋዕት አድርገው የተጋደሉትን፡ እነጸሓፌ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድንና እነጦር አዝማች ነጋ ኃይለ ሥላሴን የመሰሉት ጀግኖች ስም፡ እዚህ ላይ አብሮ በመልካም ምሳሌነት ሊዘከር፡ አግባብ ይኾናል:: ይኹን እንጂ፡ በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ምሉክነታቸው፡ ከጣልያንና ግብረ አበሮቿ ከነበሩት አገሮች ጋር፡ እንዲያ፡ በባዕዳን ምድር፡ በተባበሩት መንግሥታት ሸንጎና በሥነ መንግሥታዊው አውድማ ላይ፥ በያለበትና በያጋጣሚው፡ ደም መፋሰስ ብቻ የቀረውን ትንንቅና የጨበጣ ውጊያ አድርገው፡ ኤርትራን፡ ከነጣቂው አውሬ መንጋጋ መንጥቀው አውጥተው፡ ለእናቷ እቅፍ እስከማብቃት በደረሰ ጀግንነት፡ ጠላቶቻቸውን ድል ያደረጉት፡ እኒያ ኢትዮጵያዊ ጉበዝ፡ ጸሓፌ ትእዛዝ አክሊሉ፡ የኋላ ኋላ፡ ጠላቶቻቸው፡ በኢትዮጵያ ላይ፡ በእጅ አዙር ባካኼዱት ሥውር ጦርነት፡ በደርግ ዘመን፡ በራሳቸው አገር፡ የፊጥኝ ታሥረውና የፀረ ኢትዮጵያ ኤርትራውያን የውስጥ አርበኞች በነበሩት፡ እነአቶ በረከት ሀብተ ሥላሴን በመሰሉ፡ የጠላት መሣሪያዎች ሰብሳቢነት ይመራ በነበረው መርማሪ "ባለአደራ ምርፋቅ" (Commission ኮሚሽን) ፊት ቀርበው፥ ተፈርደባቸውና በጥይት ተደብድበው መውደቃቸው፡ ቀሪውን ኢትዮጵያዊ ኹሉ፡ እጅግ የሚያሳዝን ብቻ ሳይኾን[iii]፡ ስለአጠቃላዩ የሰው ልጅ ፍጻሜ፡ በትካዜ ሲያሳስብ የሚኖር ነው::

ኹለተኛ፡- "ደባ ራሱን፥ ስለት ድጉሱን" እንደሚባለው፡ የተባበሩት መንግሥታት ማኅበር፥ የአሜሪካ ዩናይትድ ስቴትስና አውሮጳውያን ግብረአበሮቿ፡ ሊያፈርሱ የሞከሩትን የቅዱሱን ኪዳን ሥራ፡ መልሰው ራሳቸው እንዲያስተካክሉት፡ ይኸው፡ ራሳቸው በቆፈሩት ጉድጓድ ራሳቸው እየገቡበት መኾኑን፡ በአንክሮ መመልከት ነው:: አዎን! እግዚአብሔር አንድ ካደረገው አንድነታቸው እንዲለዩና በመለያየታቸው ምክንያት፡ እንዲተላለቁ ባደረጓቸው ኹለት ወንድማማች ወገኖች፡ ማለትም፡ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል፡ እንደገና በአስታራቂነት ገብተው፡ ያን፡ በመለኮታዊ ግብር፡ የተፈጸመውንና እነርሱ ሊያፈርሱት የሞከሩትን አንድነት፡ በዚያው፡ በሚመኩበት፡ በራሳቸው የሰውና የገንዘብ፥ የጉልበትና የእውቀት ኃይል፡ ወደነበረበት ቦታው እንዲመልሱ ተገድደው፡ ይህንኑ ግዳጃቸውን ለማከናወን ሲጣደፉ፡ እነሆ እንመለከታለን:: የዚህን ውጥን ተግባራዊነት፡ ጅምሩን እንዳየን፡ ፍጻሜውንና ውጤቱንም፡ በታወቀው ሃይማኖታዊ ተስፋ እንጠብቃለን::

እኒህን ከመሰሉ ተጨባጭ ማስረጃዎች፡ የሚገኘው ግንዛቤ ምንድር ነው? የቀድሞው፡ የመንግሥታት ማኅበርና የዛሬው፡ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፡ ኹለቱም ተቋሞች፡ "አባል አገር የኾነችውን፡ ኢትዮጵያን፡ ኹለንተናዊ ልዕልናዋና የሕዝቧ ደኅንነት ሳይነካ፡ ተከብሮ እንዲቀጥል፡ እንጠብቃታለን" ሲሉ፡ እንያን፡ በከፍተኛ ደረጃ የተወደሱትንና እየተወደሱ የሚገኙትን፡ መሠረታውያን መመሪያዎችና የጋራ ግዴታዎች በያዙት ቃል ኪዳኖቻቸው አማካይነት፡ አስፈላጊ የኾኑትን ማረጋገጫዎችና ዋስትናዎች በይፋ ሰጥተው ነበር።

ይኹን እንጂ፡ "መጽደቁ ቀርቶ፡ በወጉ በኰነነኝ" እንደሚባለው፡ የኹለቱም ተቋሞች ግዳጅ፡ ይህን የመሰለውን ጥበቃ ማበርከት መኾኑ ቀረና፡ ወይም፡ ያም ቢቀር እንኳ፡ ዐርፈውና ዝም ብለው፥ እጆቻቸውንም ሰብስበው፡ በገለልተኝነት ቢቀመጡ የተሻለ ሲኾን፡ ይባስ ብለው፡ ዓላማቸው፡ እነዚያን መመሪያዎቻቸውንና ግዳጆቻቸውን በሚያፈርስ ይዘት፡ የኢትዮጵያን ኹለንተናዊ ልዕልናና የሕዝቧን ደኅንነት የሚፃረር ተግባር ማካኼድ ኾኖ ተገኘ!

ይኸውም፡ የኢትዮጵያ ጠላቶች፡ በአገሪቱ ብሔራዊ ጉዳዮችና ቤተሰባዊ ገመናዎች ውስጥ በቀላሉ ዘልቀውና ጠልቀው በመግባት፥ ሰላሟንና ደኅንነቷንም በማመስ፡ የየራሳቸውን የከፋት ዕቅዶች፡ ከግብ ለማድረስ የሚችሉበትን መንገድ፡ በምሥጢራዊ ስልት ማመቻቸት ነው። ዳሩ ግን፡ ይህ የወዳጅ ጠላትነት ዓላማና ድርጊት፡ ይሠምርላቸው ዘንድ፡ ምንም እንኳ፡ በእነርሱ በኩል፡ በተለያየ አካኼድ፡ ጥረታቸውንና ትግላቸውን መቀጠላቸው ባይቀርም፡ የእግዚአብሔር እውነት፡ አሁንም፡ ለኢትዮጵያ ካላት ብቸኛ አለኝታ፡ ማለትም፡ ከቅዱሱ ኪዳን ጋሻነት የተነሣ፡ ሙከራቸው ኹሉ እየከሸፈባቸው ይታያል።

እንግዲህ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በሃይማኖት ውለታ ለተሣሠሩበት፡ ለቅዱሱ ኪዳን ግዳጃቸው፡ ፍጹም ታማኝ ኾነው ተገኝተው ቢኾን ኖሮ፡ ከዚህ በላይ ተዘርዝሮ እንደተገለጸው፡ በአሁኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያና በቅዱሱ ኪዳን ሕዝቧ ላይ የደረሰውና እየደረሰ ያለው መከራና ችግር፡ ይደርስ ነበርን? የለም፥ እንዴት ሊደርስ ይችላል? አይችልም። ምናልባት፡ እርስዎ፡ "ሊደርስ ይችላል" ብለው ያስቡ ይኾናል። እኔ ግን፡ እንዲህ አላስብም።

ኢትዮጵያ፡ ካለፉት ቅርብ ዓመታት ወዲህ ለገጠሟት፡ ለእነዚያ ኹሉ አሳዛኝ ኹኔታዎች ከመዳረግ የደረሰችው፡ ከእግዚአብሔር ጋር በተካየደችው፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ፡ ይህ፡ የዛሬው ትውልዷ፡ በአጼ ኃይለሥላሴ መሪነት ከፈጸመው የክህደትና የርኵሰት ኃጢአት የተነሣ መኾኑን እኔ አምንበታለሁ። ይህ እምነቴ ትክክልና እርግጥ መኾኑን፡ እስካሁን፡ በዚህ መጽሐፋዊ መልእክት ውስጥ ከተሰጡት ማብራሪያዎች በላይ፡ በተጨማሪ፡ በሚቀጥሉት ገጾች የሚቀርቡት ማስረጃዎች በበለጠ ያስገነዝባሉ።

\+ + +